# ማውጫ


**መልዕክት**

ብልፅግና በሃገር ውስጥ በአሉ ችግሮች ትንታኔ ላይ ተንተርሶ የተፈጠረ ፓርቲ ነው .............. 3

*መልዕክት*

ብዙ ሆነን እንደ አንድ አንድ ሆነን እንደ ብዙ .................................................... 8

*እንግዳችን*

የብልፅግና ፓርቲ ለአገራችን የፖለቲካ ችግሮች መፍትሄ የመስጠት ጠንካራ አቅም አለው! ........................................................................................ 14

*አብይ ርዕስ*

ለተጠና ችግር መፍትሄ የፀና አገልጋይ! ...................................................... 26

*ዓውደ ሃሣብ*

ለለውጡ ውስጥ ግጭቶች መፍትሔዎች እንሁን ............................................ 41

*ድርና ማግ*

ከቅርብ ያልመለሰ እረኛ ሲሮጥ ይውላል! ...................................................... 54

*ጥንቅር*

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ....................................................................... 68


# ዓውደ ለውጥ

## በአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እየታተመች የምትወጣ ልዩ ልዩ ጥንቅሮችን፣ ትንታኔና፣ መዝናኛ ይዛ የምትወጣ ልዩ መፅሔት


አዘጋጅ፡- የአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህዝብ ግንኙነት ዘርፍ

አሳታሚ፡- አዲስ አበባ ብልፅግና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አድራሻ፡- 0116 67 43 94

ኢ.ሜይል፡- awdelewt@gmail.com

1ኛ ዓመት ቅፅ 1 ቁ.2 2012

ዋና አዘጋጅ፡- ዘሪሁን ገ/መድህን 011 6 67 43 94

አዘጋጆች፡-

ታደሰ በቀለ 011 6 67 44 13

ዮሐንስ ለገሠ

ብርሃኑ አምሳ

ቴዎድሮስ ተሻለ

ዲዛይነር፡- ደኗ ግዛው

ሬ/ዲዛይነር፡- እሪታች ቀኑብህ

ሽፋን ገፅ፡- ያሬድ መርሻ

ካርቱኒስት፡- አወቀ ንጉሴ

ህትመት ክትትል፡- ቤተልሔም ገ/ስላሴ

ህትመት ስርጭት፡- ትዕግስት አለሙ




'ማርን ሸጦ ምን ይገዟል' እንዲሉ ተፈላልጎ ተማምኖ ውህድ መሆንን የመሰለ ማለፊያ ነገር በተለይ በዚህ ጊዜ ምን ይኖራል?! ቀዬን ቀበሌን በጭፍን መንዳት፣ አንድም ተጠቀምኩ የሚል በሌለበት በአራቱም ማዕዘን ወደ የራስ ገመዱን መሳብና መንተት፤ ይህን የፈረደበትን ሰፊው ህዝብ በስሙ እየማሉና እየተገዘቱ የራስን ፖለቲካዊ ፍላጎት ከሻሞው ለማግኘት መሯሯጥ፣ መላላጥ፤ በእርግጥም ከዚህ ሁሉ የአትርሱኝ ወዘተረፈ የሀይል አሰላለፍ በዓላማና አመለካከት አንድነት ሰብሰብ ሰብሰብ ብሎ እንደ አንድ መቆም ሰናይ እንጂ ብላሽ አይሆንም፡፡

ዋናው እና ትልቁ ጉዳይ የትኛዎቹም የፖለቲካ ቡድኖች በመሰረታዊ የፖለቲካ አቋማቸው አንድነት የአላቸው፣ ሰብሰብ ለማለትም ይሁን እንደ ብልፅግና የውሁድ ፓርቲው አካል ለመሆን በአመለካከትም በተግባርም ፅኑ ፍላጎትና ቁርጠኝነት ከፈቃደኝነት ጋር የአላቸው መሆኑ ላይ ነው፡፡ እንዲያ ካልሆነ ዕጣ ፈንታው የእምቧይ ካብነት ነው ና!

ከዚህ መሰረታዊ እውነታ ተነስተን ወደ ብልፅግና የተደረገውን ጉዞ ስንፈትሽ የሚከተሉትን ቱባ ሃቆች እናገኛለን፡፡ ውህደት በዘመነ ለውጡ ከየት መጣ ሳይባል አገሩን አየሩን የሞላ አሸን አይደለም፡፡ ቢያንስ በአምስት ጉባዔዎች የእንዋሃድ ጥያቄ አጀንዳ ሆኖ ተገቢነቱ እየተሰመረበት የመጣ ነው፡፡ እኔ ነኝ የአለ ሁለት የአመራር ትውልድ ከፍ የአደረገው አጀንዳ ነው፡፡ ሌላኛው ሃቅ በድርጅታችን ጥልቅም ሆነ ጥብቅ ግምገማ ብቻ አስፈላጊነቱና ተገቢነቱ የተገለጠ አይደለም፡፡ የምሁራን የሁለት ዓመት ጥናት ውጤትም ነው፡፡ "ኢህአዴግ በድንቅ ገድሎቹ ብቻ የመቆም ቁመና አጥቷል፣ በአመራር ድክመት የፈጠራቸው ገደሎችንም በእንዲህ ሁኔታ ተሻግሮ ማሻገር አይችልም፡፡" ሲል ጥናቱ አረጋገጠ፡፡ የመድረኩን ጥያቄ ሊመልስ በሚችል ቁመና መደራጀት አሊያም መጃጃቱን ለመኳል ማገዶ መፍጀት? ብልፅግና የዚህ ጥያቄ መልስ ነው፡፡

ባለድርሻ አካላቱ በተዋረድ ጥናቱን አስፈላጊነቱን ፕሮግራሙን መተዳደሪያ ደንቡን መክረውበታል፡፡ ውይይት ሲጀመር ሁሉም አንድ እና ያው የሆነ ግንዛቤና አመለካከት ይዞ ባይገባም ሃሣብ ለሃሣብ ተፋጭተውበት አብዛኛው ለውህደቱ የቆረጠ ሌላው ከውህደቱ ራሱን የቆረጠ ሆኗል፡፡ በየደረጃው በተካሄደ ድርጅታዊ መድረክ የታየው እውነታም ይህ ነው - ፍላጎት! የፈለገው ወደ ውህደቱ መጥቷል፤ ያልፈለገው ያለመፈለግ መብቱን አረጋግጧል፡፡ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት የብልፅግና ፓርቲ እንኳንስ ለተቃውሞ ለሀሜትም በማይመች ነፃና ግልፅ አካሄድ፣ ያለ ጠፍጣፊ እና ተጠፍጣፊ፣ በከፍተኛ ደረጃ በሰፋ ማህበራዊ መሰረት ወደ መሪነት እንዲመጣ ሆኗል፡፡ የኢህአዴግን ሰናይና ምርጥ መርሆዎችንና እሴቶችን አቅፎ፣ ድክመቶቹን ተፀይፎ ወደ መድረኩ የመጣው ብልፅግና ስሙና ምግባሩ አንድ ይሆኑ ዘንድ አመራሩና አባሉ ከወዲሁ በተገቢው ንቃት በተገቢው ብቃት ይረባረቡ ዘንድ የአውደ ለውጥ መልዕክት ይሁን፡፡

# ብልፅግና በሃገር ውስጥ በአሉ ችግሮች ትንታኔ ላይ ተንተርሶ የተፈጠረ ፓርቲ ነው



የብልፅግና ራዕይ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ለውጥ ሁለንተናዊ እድገት ማምጣት ነው፡፡ ይህንን ሁለንተናዊ እድገት ሰርቶ የማደር ፍላጎት የሚመልስ በሰላም ወጥቶ መመለስን የሚያረጋግጥ በኢትዮጵያ ጥላ ስር ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተከባብረው ተዋድደው በአንድነት እንዲኖሩ በራሳቸው እንዲኮሩ በብሔራቸው የሚኮሩ በኢትዮጵያ የሚኮሩ በዓለም መድረክ ተወዳድረው ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ከፍ የሚያደርጉ እንዲሆኑ በድምሩ ብልፅግና ብለነዋል፡፡

ብልፅግና “clarity of thought” የአስተሳሰብ ጥራት እና “purity of heart” የልብ ቀናነት ያለው እሳቤ ነው፡፡ በጣም clarity አለው፡፡ ለእኛ ሰፈር ልጆች አይልም፣ አጭበርብረው ስልጣን ላይ መቆየት፣ መስረቅ ምናምን የሚል ሳይሆን “ይች አገር እንዴት ተደምራ ትበለፅጋለች” የሚል ግልጥ ያለ ሃሳብ ያለው ነው፡፡ ደግሞም ደፋር ነው፡፡ ሳይመሰረት ሃሳቡን በመጽሀፍ መልኩ እንካችሁ እንዳሻችሁ ተቹ ያለ የመጀመሪያው ፓርቲ ነው፡፡ “clarity of thought” ስላለው ብልፅግና ለትውልድ (Genaration) እንጅ ለምርጫ አይሰራም፡፡ የምንሰራው ለትውልድ እንጅ ለምርጫ አይደለም፡፡

የብልፅግናን ሃሳብ የብልፅግናን የአሰራር ስርዓት በፍፁም ለሚቀጥሉት ሃምሳና ስልሳ አመታት ማሸነፍ አይቻልም፡፡ እንዳትሳሳቱ አብይን ማሸነፍ ይቻላል፡፡ ማንም እኔን ቢያሸንፍ ከእንግዲህ ከብልፅግና ሃሳብ እና ቀን ከሌት ከመስራት ውጭ ኢትዮጵያን ለስድስት ወርም ማስተዳደር አይችልም፡፡ ስለዚህ የእኛ ሃሳብ “clarity of thought እና purity of heart” ስላለው ኢትዮጵያ ውስጥ ማንም ቢመጣ ከዚያ ውጭ እነቃነቃለሁ ቢል እራሱን እንደመግደል ስለሚታሰብ ውጭ ሆነንም በሃሳብ እንደምንመራ ውስጥ ብንሆንም ተጨማሪ እዳ እንደሆነ ስለምናውቅ ሁሌም

አሸናፊዎች ነን ብለን እናስባለን፡፡

ለታዋቂው ፈላስፋ ሶቅራጠስ ጓደኛው ስለአንድ የጋራ ጓደኛቸው “አንድ የምነግርህ ነገር አለኝ” ይለዋል፡፡ ሶቅራጠስም “ስለጓደኛችን ሳትነግረኝ በፊት ሶስት ጥያቄዎችን ልትመልስልኝ ይገባል” አለው፡፡ ጓደኛውም “ጠይቀኝ ከጥያቄህ በኋላ እነግርሀለሁ” ይለዋል፡፡ ሶቅራጠስም “የመጀመሪያው ጥያቄ ስለጓደኛችን የምትነግረኝ ነገር ምን ያህል እውነት ነው?” በማለት ይጠይቀዋል፡፡ ተናጋሪውም “እውነት መሆኑን እንኳ መቶ በመቶ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ምን አልባት ሃምሳ በመቶ እርግጠኛ ሊሆን ይችላል” ይለዋል፡፡ “ሁለተኛ ጥያቄ ይህ የምትነግረኝ ነገር ስለወዳጃችን መልካምነት የሚናገር ነው ወይ?” ይለዋል፡፡ ጓደኛውም “በፍጹም ስለእርሱ መጥፎነትና ክፋት ነው ልነግርህ የፈለኩት” ሲል ይመልስለታል፡፡ “ሶስተኛው ጥያቄዬ ይህ የምትነግረኝ ነገር ምን ያህል ለእኔ ይጠቅመኛል” በማለት ጥያቄውን ያጠቃልላል፡፡ ጓደኛውም “ለአንተማ የሚጠቅምህ ነገር የለም፡፡ ስለእርሱ መጥፎነትና ክፋት እንድታውቅ ነው እንጂ” በሚል ይመልስለታል፡፡ ሶቅራጠስም እውነት ከሌለው፣ ስለወዳጃችንም መልካምነት የማትነግረኝና ለእኔም የማይጠቅመኝ ከሆነ አትንገረኝ አለው፡፡

“ብልጽግና የብሄር ብሄረሰቦችን መብት የሚያከብር አይደለም” የሚል ንግግር ሳይሆን የሚያስፈልገው የብሄር ብሄረሰቦችን መብት እንዴት ማክበር እንደሚቻል የተጻፈ እውነተኛ አማራጭ ሀሳብ ይዞ መቅረብ ነው ለሀገርም ለህዝቡም የሚጠቅመው፡፡ ሀሳቡ ሲቀርብ የትኛው ይበልጥ የፌዴራል ስርዓትን ያጠናክራል? የትኛው ይበልጥ በአብሮነት ያኖረናል? የትኛው ይበልጥ ሰላማችንን ያረጋግጣል? የሚለውን በግልጽ በማስቀመጥ ህዝቡ ለማስተዋል አይቸገርም፡፡ የሀሳብ አማራጭ ሳናቀርብ ግን የቀረበውን ሀሳብ ካለስሙና ካለማንነቱ የምንተች ከሆነ ሰዎች አማራጭ ሀሳብ ስለማያገኙ ያ የሚተቸውን የሚሰደበውን ይበልጥ ለማወቅ ይገደዳሉ፡፡ የሚቃወሙ ሰዎች ሳያውቁ ከእኛ በላይ ስለኛ ይሰብካሉ፡፡ ምክንያቱም ፈረንጆቹ recognition starts from the negative energy ይላሉ፡፡ ብልፅግናን በመስደብ እና በማጥላላት ጊዜ የሚያጠፉ ሰዎች ብልፅግና ጠንከር ያለ መሆኑንና የሚያሻግር መሆኑን በደንብ አምነዋል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው ለማይረባ ነገር በስድብም ቢሆን ጊዜ አያባክንም፡፡ ለሚናቅ ነገር ጊዜ ማባከን አያስፈልግም፡፡ ብልፅግናን የምትንቁ ካላችሁ ስለኛ በመናገር ጊዜ አታባክኑ፡፡ ብልፅግናን በመክሰስ ሳይሆን ከብልፅግና በመማርና የብልፅግናን እሳቤዎች በማሻሻል የሚመጣ ብቻ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ከእንግዲህ ቦታ ያለው፡፡ የበዛ ብልጣብልጥነት ከእንግዲህ አያዋጣም፡፡ ከመስረቅ ራስን ነፃ በማውጣት በቅንነት በአገልጋይነት የሚሰራ ብቻ ነው መቆየት የሚችለው፡፡

የአዲስ አበባ አመራሮችና የአዲስ አበባ ወጣቶች ለአዲስ አበባ መትጋት ተገቢ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ መስረቅ ግን አሳፋሪ ነው፡፡ የምትሰርቁ ከሆነ ከዚህ ቆሻሻ፣ አበባ ማየት ብርቅ ከሆነበት፣ በደሳሳ ጎጆ ሰዎች የሚሰቃዩበት፣ በሽዎች የሚቆጠሩ ህፃናትና ሴቶች በረንዳ ከሚያድሩበት ከተማ ከምትሰርቁ አዲስ አበቤ ባትባሉ ይሻላችኋል፡፡ ስለዚህ ሲበዛ ብልጣብልጥ መሆንና ያያችሁትን ላፍ ላፍ ማድረግ በኋላ እዳ ስለሚሆን ማገልገል ላይ ብቻ አተኩሩ፡፡

መስራት፣ ከሌብነት መጠበቅ በቅንነት ሁሉን ማገልገል ብቻ ነው ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራው፡፡ የተሸወድንበት ዘመን ዳግም ሊመጣ አይችልም፡፡ ማንም ኢትዮጵያዊ በምርጫ የኢትዮጵያ መሪ መሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ሁላችንም ልባችንና አእምሮአችን ክፍት መሆን አለበት፡፡

ፓርቲያችን ለምን ብልፅግና ተባለ? ብልፅግና ለሚወደው የሚተጋ እንጅ የሚጠላውን በተደጋጋሚ በመናገር የሚኖር ፓርቲ አይደለም፡፡ ድህነትን አጥብቀን እንጠላለን፡፡ የምናወራው ግን ስለ ብልፅግና፣ የምንሰራው ስለብልፅግና፣ የምናልመው ስለብልፅግና ሲሆን በዚያ ህልም

ውስጥ ድህነት ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ይሞታል።

በተቃራኒው የምንጠላውን ድህነት አሁንም አሁንም አሁንም ድህነት ድህነት ብንል እንወዳጃዋለን። እንለማመደዋለን። ጓደኛሞች እንሆናለን። ብዙ ጊዜ ብየዋለሁ ሰዎች ጥሩ ለብሰው ጭቃ ውስጥ ወይም አቧራ ውስጥ ሲሄዱ መጀመሪያ ይጠነቀቃሉ ቦታ ይመርጣሉ። ቀስ እያሉ ጫማው ሲቆሽሽ፣ ሱሪው ሲቆሽሽ ግን ምርጫ ይቀራል ጭቃ እያንቦጫረቁ ይሄዳሉ። ድህነት እንደሱ ነው ሲለማመዱት።

እኛ ብልፅግናዎች ድህነትን እንጠየፈዋለን እንጠላዋለን። ግን ንግግራችን፣ ፅሁፋችን፣ ስራችን ድህነት ሳይሆን ብልፅግና ነው። ድህነትን የሚያጠፋው ስለሱ አብዝቶ በመናገር ሳይሆን ስለብልፅግና አብዝቶ ማለም ስለሆነ። ብልፅግና ያልነው በሱ ነው።

ቻይናዎች አንድ አበባል አላቸው ድመቷ ጥቁር ወይም ነጭ መሆኗ ሳይሆን አይጥ መያዟነው ይላሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ የድመቷ እግር ስንት ጥፍር አለው በሚል፣ ድመቷ ጋር ሳንደርስ የድመቷን ጥፍር በሚመለከት ስንከራከር ሁለት አብዮቶች አልፈዋል። አሁን ተሎ ብለን ድመቷን በመፍጠር ድህነትን ማጥፋት ያስፈልጋል። ከዛ ውጪ ያለው እሳቤ ውጤት እስካላመጣ ድረስ ወደ እውነት እስካላስጠጋን ድረስ ፋይዳ የለውም እውነት ደግሞ የሚለካው በሚሰጠው ጥቅም ነው።

አብስትራክት (ስውር) እውነት የለም፤ እውነት ራሱ ሰጪ ነው። እውነት ራሱ ንፁህ ነው። የሚለካውም በሚያስገኘው ውጤት ነው።

ወደ እውነት ተጠግቶ የከሰረ ወይም የሚከስር ስለሌለ እውነት የሚለካበትን መነፅር ለማምጣት የድመት ከለር እና ጥፍር ላይ የምናጠፋውን ጊዜ ትተን በመደመር እሳቤ ብልፅግናን እውን ማድርግ ይኖርብናል። ይህንን ማድረግ ደግሞ እንችላለን።

ብልፅግና አሁን ባለው ሁኔታ ምን ሊያደረግ ይችላል። የብሔር ጥበት በዝቶ፣ የሀይማኖት አክራሪነት በዝቶ ድህነት፣ የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ንረት በሰፋበት ቦታ ብልፅግና ምን ያደርጋል የሚል ጥያቄ ይነሳል። ይሄ ሁሉ ችግር ባይኖርማ ብልፅግናን ምን አመጣው?! ብልፅግና በሀገር ውስጥ በአሉ ችግሮች ትንታኔ ላይ ተንተርሶ የተፈጠረ ፓርቲ ነው። አሁን ያለብን ችግር በምንድን ነው የሚፈታው ብሎ በችግር ትንታኔ ላይ የተፈጠረ ፓርቲ ነው።

ስራ አጥነት ባይኖር ኖሮ፣ ዘረኝነት ባይስፋፋ ኖሮ፣ ኢኮኖሚያችን ቢያድግና ከላይ እስከ ታች ሁሉም ተግቶ ቢሰራ ኖሮ፣ በሁሉም ብሔሮችና ብሔረሰቦች እኩል እይታና እሳቤ ቢኖር ኖሮ ብልፅግናን ምን አመጣው? ብልፅግና የመጣው እኮ የሀገራችን ጉዞ ከአንድነት ወደ መለያየት ያተኮረ፣ ስራ አጥነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ፣ ልማቱ ሀብታም ያደረጋቸውን ሰዎች ያክል ድህነትን ያላጠፋ በመሆኑ፣ በእየአንዳንዱ ሴክተር ያሉ ችግሮች ተተንትነው ይህንን ችግር በምን እንፍታ ስንል በብልፅግና በሚል የመጣ ስለሆነ የችግሮቻችን ሁሉ መፍቻው የብልፅግና መፈጠር ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የድህነት ችግር የቁስ ብቻ አይደለም የሀሳብም ነው። ብልፅግና የሶስት ነገሮች ጋብቻ ውጤት ነው። አንደኛው ነዋይ፣ ነዋይ ብቻውን ብልፅግና መሆን አይችልም። ሁለተኛው እውቀት ነው፤ ያንን ነዋይ የምናባዛበትና የበለጠ ነዋይ የምንፈጥርበት መሰረት ነው። ሶስተኛ የማድረግ አቅም ነው። ሶስቱ ሲጋቡ ነው ብልፅግና እውን የሚሆነው። የማድረግ

**“ደሀ ሆኖ በድህነት ለመኖር መፍቀድ ነው ስህተት። ደሀ ሆኖ ወደ ብልፅግና ለመሻገር ማድረግና ለዚያ መትጋት ነውር አይደለም።”**

አቅም ያለው ወጣቶች ጋር ነው፡፡ ብልግፅና ከሁሉም እንደ አቅሙ ይሰበስባል፡፡ እውቀት፣ ጥበብ ከውስጥም ከውጪም ይገበያል፡፡ ሶስቱ ሲጋቡ ብልፅግና እውን ይሆናል፡፡ ይህንን ታሳቢ ያላደረገ፣ እውቀት አልባ፣ ነዋይ አልባ፣ የማድረግ አቅም ያለውን ወጣት የዘነጋ ከሆነ ብልፅግና እውን አይሆንም ከሚል ከነባራዊ ሁኔታና ከተጨባጨ ችግር ትንታኔ የተወለደ ፓርቲ ነው፡፡

ይህንን ማድረግ እንደምንችል በተፈጠረ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወይም በመፈጠር ሂደት ላይ እያለ Home grown economic Reform (ሃገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም) አጀንዳ የብልፅግና እሳቤ ያለው አጀንዳ በአገር ውስጥ ምሁራን በተቃዋሚ ፓርቲዎች አጋዥ ድርጅቶችን ካወያየን በኋላ አለም ላይ ለማስተዋወቅ ባደረግነው ሙከራ እስካሁን ባለው እውነት ኢትዮጵያ ውስጥ አይተን የማናውቀውን እርዳታ አግኝተናል፡፡ እስካሁን 10 ቢሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ማለት IMF ብቻ እስካሁን ከሚሰጠን ኮታ 700 ፐርሰንት የበለጠ በጀት ሰጥቶናል፡፡ ብልፅግና እሳቤውና ጎዳናው ኢትዮጵያን ትራንስፎርም ማድረግ ይችላል የሚል እምነት በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ዓቀፍ ማህበረሰብ ዘንድም መፈጠር ጀምሯል፡፡ ነገር ግን ይህ ያመጣነው ገንዘብ ነዋይ የሚባለው ነው፡፡ የማድረግ አቅም ያለው ከወጣቶች ጋር ነው፡፡ ካልተጋቡ ብለፅግና የለም፡፡ ሌቦች የስራ ሀላፊዎች ሌቦች ሹማምንቶች ካሉ ብልፅግና የለም፡፡


ሌቦችን ማጥፋት ከቻልን ቀን ከሌት ተግተን መስራት ከቻልን ያ የምናመጣው ሀብት ብዙ ሀብት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ያ እንዲሆን ጋብቻው እንዳይበላሽ ከወጣቶች የሚጠበቀው በየአንዳንዱ የልማት ኮሪደር በፍፁም ፈቃደኝነት መሳተፍ ነው፡፡

በሀዋሳው ጉባኤ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን ብለን ቃል ከገባን በኋላ የተጀመሩ ስራዎች ለኛ ካሰብነው በላይ እርካታ እየሰጡን ያሉ ናቸው፡፡

ብልፅግናን ከማሰብ ባሻገር ማድረግ ይቻላል ወይ የሚለው ሙከራ በአዲስ አበባ ላይ ተጀምሯል፡፡ አዲስ አበባችን በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት አሁን ከአለችበት ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ልቃ ለሌሎች የክልል ከተሞች እና ለአፍሪካ አገራት የብልፅግና ምልክት ትሆናለች፡፡ አንድ ቦታ ጀምረን በተግባር አይተን ያልተለማመድነውን ሀሳብ 10 ቦታ ብንወስደው አስሩም ሳይከናወን እንዳይቀር ለእኛም የልምምድ የመደመር የማድረግ አቅማችን መለኪያ እንዲሆን እንጅ አዳዲስ ከተሞችም ሆነ ነባር ከተሞችን የማስዋብና ለኑሮ ምቹ ማድረግ የብልፅግና አንዱ ዋነኛ ምሰሶ በመሆኑ በአዲስ አበባ የጀመርነውን በሁሉም ከተሞች ናስቀጥላለን፡፡ ብልፅግና መጀመሪያ የሚታይ የሚጨበጥ ነገር በከተማችን ጀምሮ ይህንን ልምድ አደረጃጀት ብቃት በሌሎች ከተሞችም የሚያሰፋ እንጅ ሁሉም ጋ ሣይጨርስ የሚቀር አይደለም፡፡ እስከሚቀጥለው ሰኔ ድረስ ቢያንስ እንጦጦን፣ ሴንትራል ፓርኩን፣ ዩኒቲፓርክን እና የአዲስ አበባን መንገድ እናገኛለን፡፡ ይሄ በከተማታችን ገፅታ ላይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ ያመጣል፡፡

በ1966፣ 1983 ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት አብዮቶች ተካሂደዋል፡፡ አሁን 2010 በሌላ መልክ እራሱን ይዞ መጥቷል፡፡ ከእንግዲህ በኋላ እያንዳንዳችን መወሰን ያለብን የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ አብዮት ሳይኖር ስለ ድመቷ ጥፍር ሳንከራከር ወደ ብልፅግና በሀሳብና በእውቀት የምንሄድበት፣ ሰው የሚመርጥበት እንጂ የማይሞትባትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር የሁላችን ትብብር በእጅጉ የሚያስፈልግ መሆኑን አምነን በተግባር መመንዘር አለብን፡፡

ኢትዮጵያ ከ25 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ከድህነት ወለል በታች የሚኖርባት አገር ናት፡፡ መቆጨት አለብን፣ መስራት አለብን፣ መትጋት አለብን፣ በዚያም ብልጽግናን ማረጋገጥ አለብን በመስራታችን በመድከማችን ከእድሜያችን አንድ ሰዓት አይቀንስም፣ከክብደታችን አንድ ግራም አይቀንስም፣ ጎንበስ ብለን ሰርተን ሀገርን ብናቀና ልጆቻችን ትውልድ የሚያከብሩት ይሆናልና እጅ ለእጅ ተያይዘን ከብልጽግና ጋር በህብር ኢትዮጵያን ወደ ሚገባት ማማ እናውጣት!!


ዘንድሮም
ወደ ብልፅግና

# “ብዙ ሆነን እንደ አንድ አንድ ሆነን እንደ ብዙ”



በመሰረቱ ስለ ውህደትና ስለ ለውጥ ስለ አዲስ ፓርቲና እሳቤ መነሻ ሲደረግ ካለፉት ጉዟችን በጥንካሬ የሚታዩትን አሁንም ቢሆን ይዞ የመጓዝና የማስፋት፣ በተሃድሶ እንቅስቃሴያችን የገመገምናቸውንና ደጋግመን ቃል የገባንባቸውን፣ አሁንም የሚፈታተኑንን ችግሮች ያለ ምህረት የማረምና የማስተካከል ቁርጠኝነትን በማንገብና አሁን በደረስንበት ደረጃ ለመጪው ዘመን የሚያታግለንንና ውጤታማ የሚያደርገንን አስተሳሰብ በመታጠቅ ነው፡፡

በአገራችን የፖለቲካ ልምድና አተያይ ቀድሞ የነበረውን በሙሉ የማጣጣል አካሄድ በብልፅግና ፓርቲ ውስጥ ተገቢነት የለውም፡፡ አገርም አይጠቅምም፡፡ አፍርሶ መስራት በተደጋጋሚ እንደሚባለው የትም አላደረሰንም፡፡ በፍርስራሽ ላይ መገንባት ወይም ነቅሎ መትከል አይጠቅም፡፡ በአለፉት አመታት የነበሩ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ለይቶ በመውሰድ እነሱን ማብዛት ያሻል፤ እንደ በጎ እሴት ስንቅ ሆነው ወደ ፊት ሊያገለግሉ ይገባል፡፡

የትኛውንም ምክንያት ብንደረድር አገርን የጎዱ፣ ህዝብን ያማረሩ፣ ኢህአዴግም ጉድለቴ ናቸው ብሎ የቆጠራቸው ችግሮች አሁንም ቢሆን በመሰረቱ ሊፈቱ ይገባል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት እየተጠጋ ባለው የለውጥ እንቅስቃሴ ብዙ ጉዳዮችን ለማረምና ለማስተካከል ተሞክሯል፡፡ አሁንም ችግሮች አሉ፡፡ ህዝቡን ያረካ ስራ አሟልተን ሰርተናል

ብለን አናምንምና መልካሙን ነገር ይዞ የተበላሸውን አርሞ ለመጪው ዘመን ያን የሚመጥን እሳቤ ይዘን መጓዝ አለብን፤ ስለ ውህደት፣ ስለብልፅግና ፓርቲ ስናወሳና ስንናገር መርሁና ማጠንጠኛው ይህ ነው፡፡

በዚህ አግባብ ይህ ውህድት ለምን የሚለውን ነገር ስናይ አገራችን በሁለት ፅንፎች የተወጠረች ናት፡፡ በአንድ በኩል ከብሔርተኝነቱ ጋር ተያይዞ ወደ ፅንፈኛ ብሔርተኝነት ያመሩ እጅግ የከረሩ አተያዮች አሰላለፎች አሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአገራዊ አንድነት ስም ለቡድን መብቶችና ለሌሎች የብዝሀነት ጉዳዮች ተገቢውን ግምት ባለመስጠት የሚገለፁ አተያዮች እና አሰላለፎች አሉ፡፡

ይህንን በሁለት ጫፍ ላይ የተወጠረ ፖለቲካዊ ምህዳር በማርገብ ብልፅግና ሁለቱን በማጣጣም ብሔራዊ ማንነትንና አገራዊ አንድነትን ተደጋጋፊና ተመጋጋቢ የአደረገ መካከለኛ አማራጭ ይዞ፣ ተጨባጭ መፍትሔ ይዞ፣ ወደፊት ጉዞ ጀምሯል፡፡

ይህች አገር የብዝሀነት አገር ናት፤ ብዝሀነት ጌጣችን ነው፤ ብዝሀ ባህል፣ ብዝሃ ሀይማኖት፣ ብዝሀ ልሳን፣ ቋንቋ እጅግ በጣም ብዙ ብዝሀነታችንን የሚገልፁ መገለጫዎች አሉን፡፡ እነዚህን ማክበር፣ ለእነዚህ ተገቢውን ቦታ መስጠት፣ ለቡድን መብትም ተገቢ ቦታ መስጠትና እያጠናከሩ መሄድ ያስፈልጋል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ በዚህ እይታ ውስጥ ብቻ ታጥሮ የአገራዊ አስተሳሰብን እና የብሔራዊ መግባባትን ትኩረት ማሳነስ እንዲሁም በሚፈለገው ደረጃ ለውጥ እንዳይመጣ ማድረግ መዳረሻውን ያጎድለዋል፡፡ ጠንካራ አገራዊ አስተሳሰብ ያስፈልጋል፡፡ ለብዝሀነት ተገቢ ቦታ መስጠት ይገባል፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ብልፅግና ፓርቲ መካከለኛ አማራጭ ሆኖ ሲመጣ ህብረ-ብሔራዊ አንድነት አገራዊ አንድነት አንድ ወሳኝ የትኩረት አጀንዳችን ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል የሚል ጭብጥ በመያዝ ነው፡፡

ከዚህ ጋር አያይዘን የለውጡን ስርዓት በተደራጀ ተቋማዊ አሰራር መምራት፣ የችግር ፈችነት አቅማችንን ማሳደግ፣ በተለወጠና በላቀ እሳቤ ውስጥ መጓዝ ይጠይቃል ማለት ነው፡፡

አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ግንባታ እጅግ በጣም ጥልቅ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ ትውልድ እና ሌሎች የፖለቲካ ተዋናዮች አዎንታዊ ሚናቸውንም ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤ ብልፅግና ፓርቲያችን እንደ መሪ ድርጅት በዚህ ዙሪያ የበለጠውን ሀላፊነት ወስዶ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ መገንባትን ማጠንጠኛ ማዕከል አድርጎ መስራት፣ አመራር ማረጋገጥ እና ሀይል ማሰባሰብ ይኖርበታል፡፡

በህገ-መንግስቱና በየደረጃው ባሉት አቅጣጫዎች አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ የመገንባት ጉዳይ የተቀመጠ ቢሆንም፣ ለመነሻ የሚሆኑ፣ እዚያም እዚም የተሰሩ ነገሮች ቢኖሩም በመሰረታዊነት ግን ብዙ ጥረትና ብዙ ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ያንን በእጅጉ የሚፈታተኑ ሁኔታዎችም እያጋጠሙ ይገኛሉ እና ውህዱ የብልፅግና ፓርቲ በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ለመታገልና ለማታገል የቀረበ ፓርቲ ነው፡፡

ሌላው ጉዳይ የውህደቱ ምሰሶዎች ምን ምን ናቸው የሚለው ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ የተለያዩ ብዥታዎችና የተለያዩ ሀሳቦችም በህብረተሰቡ ውስጥ ይራመዳሉ፡፡ ስለዚህ የውህደቱ ምሰሶዎችን ማስመር ያስፈልጋል፡፡

የመጀመሪያው በዚህ ሃገር ህብረብሔራዊ ፌደራሊዝም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ይህ ደግሞ የውህደቱ ማጠንጠኛ ማዕከል ነው፡፡ ህብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲባል የቡድንና የግለሰብ መብት ሚዛናቸው ተጣጥሞ እንዲዘልቁ መደረግ አለበት፡፡ የብሔር ማንነትና ሐገራዊ አንድነትም አንዱን አንዱ ሳይጠልፍ ተመጋግበው የሚገነቡበትና

የሚዘልቁበትን ሁኔታ መኖር አለበት፡፡ የብዝሃነት ብዝኃ ቋንቋ/ልሳን፣ የባህል ብዝኃነት እና የተለያዩ የማንነት አጀንዳዎች ከዚህ አኳያ ሊጠናከሩ ይገባል፡፡ እነዚህን ማስተናገድና መገንባት ይገባል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደግሞ ህዝባችን በየአካባቢው የተለያዩ ጥያቄዎች፤ የተለያዩ ጉዳዮችን ያነሳል፡፡

ፈርጀ ብዙ የሆኑ መገለጫ ያላቸው የህዝብ ጥያቄዎች በየደረጃው በራሱ በህዝቡ ተሳትፎ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ሊፈቱ ይገባቸዋል፡፡ ይህም አንዱ የህዝብ እርካታን ለማምጣት የህዝብን አካታችነት እውን ለማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የህዝብ ጥያቄዎች እንደዚሁ ችላ ሊባሉና ሊድበሰበሱ የሚችሉ አይደሉምና በምንገነባው ስርዓት ውስጥ እነዚህን ጥያቄዎች በሰላማዊ ሁኔታ የህዝቦችን ግንኙነት አብሮነትና ሰላማዊ ግንኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎችን እንሰራለን፡፡ እነዚህና ተያያዥ ጉዳዮች ናቸው ምሰሶዎቹ፡፡ ፓርቲያችን እነዚህንና ሌሎችን በመያዝ ዋና ግቡ አገርን ወደ ብልፅግና ማሻገር ነው፡፡

በውህደቱ ዙሪያ የሚነሱ የተለያዩ የተሳሳቱ አመለካከቶች አሉ፡፡ አንዱ ይሄ ውህደት አሃዳዊ ስርዓትን ለማምጣት ነው፤ ለመመለስ ነው የሚል ይነሳል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የፌዴራል ስርዓቱን ለማፍረስ እንደሆነ፣ የተደበቀ አጀንዳ ያላቸው ሃይሎች የሚዘውሩትና የሚመሩት እንደሆነ፣ የብሔር ብሔረሰቦችና የህዝቦች መብትን ለመጨፍለቅ ታስቦ እየተሰራበት እንደሆነ ይተረታል፡፡

ይሔ በመሰረቱ ስህተት ነው፡፡ አገርን ያህል ለመምራት፣ ድርጅትን ያህል አደራጅቶና ፕሮግራም ሰንዶ ለመምራት ምን አይነት ድብብቆሽ ይኖራል የሚለው ነገር በደንብ በአፅንኦት መመልከት ያስፈልጋል፡፡

አገሪቱን ወደ ብልፅግና ለማሻገር የተከናወነው የውህደት አጀንዳ ዋና ዋና መሰረታዊ ምሰሶዎቹ የፌዴራሊዝም ስርአቱን የማጠናከር፣ ማንኛውንም ጉዳይ በህገ-መንግስታዊ ስርዓት የመምራት፣ ብዝሃነትን ከአገራዊ አንድነት ጋር አጣጥሞ የማስኀዝና መድረኩ የሚመጥነውን ሃሳብ በሃሳብ ልዕልና የህብረተሰቡን ንቅናቄ የመምራት ኃላፊነትን ይዞ መኀዝ ነው፤ ከዚህ በተቃራኒው የሚወራው ህብረተሰቡን ወደ ተለያየ አቅጣጫ ለማምራትና ውዥንብር ለመፍጠር ነው፡፡

የብልፅግና ፓርቲ Prosperity party ለአሁኒቷ፣ ለነገይቷ ኢትዮጵያ የሚመጥን የለውጥ እሳቤ የለውጥ ማዕቀፍ በመያዝ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ የተዘጋጀ ፕሮግራም የአለው ነው፡፡ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ለአመታት ኢህአዴግ በመራበት በጥንካሬና በአወንታ ያያቸውን በመውሰድ ይሔ ውህድ የብልፅግና ፓርቲ ሊያታግለው ያሰበውን ዓላማ ለማሳካት ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከህዝቦቿ ፍላጎትና ከሚያታግለው አጀንዳ ጋር አገናዝቦ የተዘጋጀ የፓርቲ ፕሮግራም አለው፡፡

የብልፅግና ፓርቲ የዓላማዎቹ ማጠንጠኛ የበለፀገች ኢትዮጵያን መገንባት ነው፡፡ እንግዲህ በዚህ አገር በህልውና ደረጃ የሚታይ እጅግ የከፋ ችግር አለ፡፡ ከዚህ ችግር ለመውጣት የተጀመሩ ጥረቶች እና የተመዘገበ እድገት ልማት አለ፡፡ የበለፀገች ሐገር፣ የምንኮራባት፣ የታፈረች፣ የኋላ ቀርነትና የድህነት እና የሌሎች የፖለቲካ ችግሮች ማጣቀሻ ያልሆነች፣ ታሪኳን የሚመጥኑ ጠንካራ ጠንካራ ሌሎች አገሮች የሚማሩበትና የሚገበዩበት የታላቅነት ራዕይ እና ወደ ክብር ያጎናፀፉን ውጤቶች ጅምሮች አሉ፡፡ ነገር ግን የተሟላ ብልፅግና እስካልተገነባ ድረስ ይሔ ሙሉ ሊሆን አይችልምና ፓርቲያችን የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ዓላማ ነው የአለው፡፡

የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የፖለቲካ ዝርዝር ዓላማ አለን፣ የኢኮኖሚ ዝርዝር ዓላማ አለን፣ የማህበራዊ ልማት ዝርዝር ዓላማ አለን፡፡ የፖለቲካ ዝርዝር ዓላማ የሚያጠነጥነው የዳበረ ዴሞክራሲን መገንባት አሳታፊ አስተማማኝ የዴሞክራሲ ባህልና በተቋም በህብረተሰብ

ውስጥ የመገንባትና ዴሞክራሲን በዚያ ደረጃ የዳበረ እንዲሆን ማድረግን ማዕከል ያደረጉ የተለያዩ የፖለቲካ ጭብጦችን የያዘ ነው። አሳታፊነት እዚያ ላይ ትልቅ ቦታ እንዲይዝ ተደርጓል።

ሁለተኛው የኢኮኖሚ ልማት ፕሮግራምን ባለፉት ዓመታት የነበሩ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን በመያዝ የነበሩ ጉድለቶችን በማረም ይሄ ልማት ጥራት ያለው፣ ዘላቂነቱን የጠበቀ፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ በእድገት ብቻ የሚመነዘር ሳይሆን በእያንዳንዱ ደሃ ኑሮ ላይ ለውጥ የሚያመጣ የልማት እንቅስቃሴ እውን ማድረግ ነው። ከዚህ አኳያ ባለው ስርዓት ውስጥ ካለፉት ዓመታት ትምህርት በመውሰድ አሁንም መንግስት በተመረጠ ሁኔታ በልማቱ ላይ የሚኖረው ተሳትፎ እንዲቀጥል የሚያደርግና የግሉ ተሳትፎ ተጠናክሮ የለውጡ ተዋናይ የሚሆንበትን ስርዓት እውን የሚያደርግ ነው።

ከማህበራዊ ልማት አኳያ እንደዚሁ ጥራት ያለውና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እሴቶችን፣ ባህልን በማበልፀግ የሚገለፅ ፈርጀ ብዙ የማህበራዊ ልማት ፕሮግራምን የያዘ ነው።

የብልፅግና ፓርቲ በጣም አጠር ያሉና ጎላ ጎላ ያሉ እሴቶችንም እንደዚሁ አስቀምጧል። የእሴቶቹ ማጠንጠኛዎች አንደኛው የዜጎችና የህዝቦችን ክብር መጠበቅ ነው። ሁለተኛው ፍትህ የሁሉም ሀብት ነውና ፍትሕን ማንገስ ነው። ፍትህ በምንገነባው ስርዓት ውስጥ አንድ ቁልፍ ማጠንጠኛ ሆኖ እንዲታይ የሚያደርግ፣ ፍትህን አንድ ትልቅ እሴት አድርጎ መያዝ ነው። ሌላው ደግሞ ህብረ ብሔራዊ አንድነት አንዱ የለውጥ አጀንዳችን የብልፅግና ፓርቲያችን እሴት ነው። እሴቶች በሁሉም ዜጋ በማህበረሰብ ተቆጥረው ተይዘው እውን ለማድረግ የሚያስችል፣ በዚህ ዙሪያ ላይ እሳቤያችንንና እንቅስቃሴያችንን ቃኝተን የምንረባረብበትና እውን እንዲሆን ሚናችንን የምንጫወትበት ሁኔታ መዳበር አለበት።

ብልፅግና ፓርቲ በውህደቱ ውስጥ ሁኔታዎች እና ሂደቱ ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ አንደኛ በቂ እና ሳይንሳዊ ጥናት የተካሔደበት ውህደት ነው። ሁለተኛ በጉባኤ የተደገፈ እንዴት እንደሚፈፀም አቅጣጫ ውክልናና ውሳኔ የተቀመጠበት ነው። ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው የመከሩበት ሂደት ነው። ያሉትን ህጎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንቅስቃሴው ህጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ የተከናወነም ነው።

በውህደቱ ውስጥ አግላይነት ተገልሏል፤ ኢህአዴግና አጋሮች በዚህ ታሪካዊ ምዕራፍ እንደ አንድ ውህድ አካል ሆነው ለህብረ ብሄራዊው ውህድ የብልፅግና ፓርቲ ዕውንነት ታግለው ተዋህደዋል።

በብዝሃነት ማዕቀፍ ውስጥ ብዙ ሆነን እንደ አንድ፣ አንድ ሆነን እንደ ብዙ እንተያይ፣ እንንቀሳቀስ የሚል ዕሳቤ አለ። በዚህ አገር አንዱ አንደኛ ሌላው ሁለተኛ የሚሆንበት አካሄድና ስርዓት አይኖርም። ለሁላችንም አገራችን የእኩል ቤታችን እኩል ክብራችን እንዲሁም የምናከብራት የምንኮራባት ናት። በዚህ ወቅት ለአሁኑና ለመጪው ዘመን የተሻለ መፍትሔ ሆኖ የሚመጣውን በሙሉ በሀሳብ ልዕልናና በአማራጭ የሀሳብ ሚዛንና ብስለት ነገሮች ሊታዩ ይገባል። አንዳንድ ጊዜ አተያያችን በኛ በፖለቲከኞች ዕይታ ብቻ መሆን የለበትም። መሆን ያለበት የመጪው ትውልድን እጣ ፈንታና የአለፈውን ትውልድ የአደራ ቃል የመጠበቅ ሀላፊነትን መውሰድ ያስፈልጋል ማለት ነው። ለዚህ ዘመንና ለዚህ ለውጥ ብዙ ዋጋ ተከፍሏል። ብዙ ወጣት ወድቋል። እጅግ የተጠራቀሙ መስዋዕትነቶች ተከፍለዋል። ብልፅግና ፓርቲ ይህንንና ስለ ወደ ፊት የምናስበውን የምንደርስበትን ፍትህ እኩልነትና ልማት የነገሰባት የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚያስችል መሪ ፓርቲ ሆኖ ቀርቧል።

ስለዚህ ለመጭው ዘመን፣ ለመጭው ትውልድ የምናወርሰው ምንድን ነው? ዋጋ ለከፈሉት ዜጎችስ፣ በተለያዩ ቦታዎች ለውደቁት ቃል የመጠበቅ ጉዳይስ እንዴት ነው? የሚለውን ነገር

ከስሜትና ከሁሉም ነገር ነፃ ሆኖ ማየት ያስፈልጋል፡፡ አንደኛው ጉዳይ ይሄ ነው፡፡

ሁለተኛ ይሄ ለውጥ በብልጽግና ፓርቲ አካሄድ እሳቤ ፖለቲካ ብቻውን ዳቦ አይሆንም የሚል መነሻ አለው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ ገንዘብና ሀብት ከሰው ሊበልጥ አይገባም የሚልም መነሻ አለ፡፡ የለውጡ አተያይ ሰው ተኮር እና ሰው መር መሆን አለበት፡፡ ይሄ ዕውን ሲሆን ሁለንተናዊ ብልፅግና እውን ይሆናል፡፡ ለውጡ ብዝሀነት ተኮርና የብዝሃ ቋንቋ፣ የብዝሀ ባህልን ሁሉንም ማንነቶች ተገቢ ቦታና ለዜጎች ክብር የሰጠ እና በዚህ ዙሪያ ሁሉን አቀፍ ብልፅግና ሊረጋገጥ ይገባል ብሎ ያምናል፡፡

በዘረዘርናቸው እሴቶች ውስጥ የዜግነት ክብር፣ የህዝቦች ክብር፣ ዋናው ማጠንጠኛ ከሆነ፤ ህብረ ብሔራዊ አንድነት ብዝሃነትንም አገራዊ አንድትንም እሳቤ ውስጥ አስገብቶ የተሰለፈ ከሆነ፣ ሂደቱም በዚህ ደረጃ አሳታፊ ሆኖ ስለመጣ አላማው ኢትዮጵያን የማበልፀግ እይታ ላይ የቆመ ከሆነ የሚያለያየን ምንድን ነው የሚለው ነገር በደንብ መመልከት እንደሚያስፈልገን አመላካች ነው፡፡


በመሰረቱ በውህደቱ ሆነ በመጭው የለውጥ ዘመን የለውጥ እሳቤ ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡ አሁን የዘረጋነው እና በህዝባችን ውስጥ የተጀመረው እና ተገቢውን ቦታ ሊይዝ የሚገባው ማንኛውንም ነገር በሀሳብ ልህቀትና ልዕልና መመዘን ይገባል፡፡ ልዩነት ቢያጋጥም ልዩነቱ አገርን ወደ ተለያዩ ጥፋቶች የሚመራ፣ ድሮ በለመድነው የተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚያስገባ ሳይሆን በዚህ ሰልፍ ውስጥ የሀሳብ ልዩነቶችና አማራጮችን ለህዝብ እያቀረቡ ህዝቡ እንዲዳኛቸው ማድረግ ነው የሚያስፈልገው፡፡

ይሄ ትውልድ መዘመንን ዕውን ማድረግ ካለበት በዚህ አካሄድ መጓዝ ግድ ይላል፡፡ በመሸናነፍ አንዱ አንዱን ጥሎ በመሄድ ሊሆን አይገባም፡፡ ሙሉ ሆኖ ወደዚህ የውህድ ፓርቲ መሻገር እጅግ ክብር የሚያጎናፅፍና ለሁሉም ጌጥ ነው፡፡ የተለየ ቢኖር እንኳ በመደማመጥ በጊዜ ሂደት ነገሮችን እየፈቱ መሄድ ብልህነት ነው፡፡ ይህንን አቅጣጫ ማስመርና መያዝ ይገባል፡፡

ከዚህ ውጭ የትኛውም አካሄድ ድርጅታችንን ሆነ ህዝባችንን አይጠቅምም፡፡ ምክንያቱም ለረጅም ዘመናት ሀገሪቷን ብዙ ዋጋ ሲያስከፍላት ቆይቷል፡፡ በዚህ በተለመደ አካሄድ ማንም አሸናፊ ስለማይሆን የተሻለ ሃሳብ የሆነውና የተሻለ ተመራጭ የሆነውን ተከባብሮ ተደማምጦ የሃሳብ ልዕልናን ይዞ ወደ ብልፅግናው ዓለም መጓዝ ያስፈልጋል፡፡

**“በቅርቡ አንዲት እህት ስትነግረኝ እናትዋ ታምመው ሆስፒታል ተኝተው ልትጠይቃቸው ሂዳ ብዙ መናገር የማይችሉት እናት ቀስ በአስ ድምፅ ልጀ ሆይ ምግብ በልተሻል ብላ ጠየቀችኝ አለች፡፡ እናት ታምማ ተኝታ መናገር ባትችልም የአስጨነቃት የልጅዋ መመገብ ነው፡፡ ይህ ነው መደመር ማለት፤ ይህ ነው መሰጠት ማለት፤ ይህ ነው መውደድ ማፍቀር ማለት፤ እንደ እናት ከወደድን እንደ እናት ከተቆራኘን የኢትዮጵያችን ብልፅግና ለኛ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም አስተማማኝ መሰረት ሆኖ ብዙ ድህነትን የሚቀንስ ብዙ ጥላቻን የሚቀንስ፣ ብዙ ችግርን የሚቀንስ፣ ለመሆኑ ቅንጣት ጥርጥር የለውም፡፡”**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ




★ ልጅትዋ በቅርፅ በመጠንም ሆነ ገፃቸው ላይ በተሳለ ምስል አንድ አይነት መንትያ የሆኑ አራት ዕቃዎችን ለመግዛት እየመረጠች ነው፡፡ አራት በቅርፅ በመጠንም ሆነ በምስል መንትያ የሆነው ዕቃ የትኛው እንደሆነ በመለየት ያግዟት ዘንድ ተጋብዘዋል፡፡ የምስሎቹን ቁጥር በመግለፅ?

**የዚህ ዕትም ጥያቄዎችን መልስም በawdelewt@gmail.com ኢሚይል አድርጉልን።**

# የአሳማ ጦርነት

አሜሪካና ብሪታኒያን የይገባኛል ጥያቄ በነበራቸው ሳንጂዋን ደሴት ላይ የተፈጠረ ግጭት ነው፡፡ የሁለቱም ዜጎች አስቀድሞ ሰፍሮ ይዞታን ማስከበር በጀመሩበት በዚህ ደሴት ላይ ጁን 15/1859 የአሜሪካዊውን ገበሬ ሊማን ከትሊር ድንችን የአየርላንዳዊው ታርልስ ግሪፊን አሳማ በመብላቱ የተነሳ ሁከት ውጤትም ነው፡፡ ሊማን አሳማውን ተኩሶ ገደለው፡፡ ግሪፍም ምነው አሳማዬን ገደልከው

"ድንቼን በላብኛ!"

"ዝቃጭ ድንችህን ከአሳማዬ ማራቅ ነበረብህ"

ይህ ምልልስ 3 የጦር መርከቦችን፣ 84 መድፎችን፣ 2600 ወታደሮችን ሊማግድ የዳዳው ምክንያትም ሆነ፡፡

# “የብልፅግና ፓርቲ ለአገራችን የፖለቲካ ችግሮች መፍትሄ የመስጠት ጠንካራ አቅም አለው!”



የብልፅግና ጽህፈት ቤት ምክትል ሀላፊ አቶ መለሰ ዓለሙ

**የኢትዮጵያ የከፍታ ዘመን ጉዞ በብልፅግና የውሁድ ህብረ ብሄራዊ አመራር እውን ሲሆን፣ ቃልም ከመድረክ ፍጆታነት ወደ ተግባር መቀየሩ እውን ይሆን ዘንድ ብልፅግና ፓርቲ ውልደቱ ተበስሯል።**

**ብልፅግና መሰረት ነው ከታሳላቆቹ አገራት ተርታ የምንሰለፍበት፤ ትውልድን የምናሻግርበት፤ የድህነትን ማቅ አውልቀን የስኬትን ካባ የምንደርብበት መሪ ሃይል ነው። ይህ እውን ይሆን ዘንድ ግን የመሪዎች ቅን አሳቢነት፣ የህዝቦችን ተባባሪነት ያሻል። በእዚህ ረገድ ደግሞ ብልፅግና “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” እንዲሉ የተበታተነ አቅሙን ሰብሰብ አድርጎ ኢትዮጵያን ወደ ብልፅግና ለማሸጋገር በተደራጀ አቅም ጠንካራ አመራር ሲሰጥ ተዘጋጅቷል። ይህ ብልፅግናን የፈጠረው ውህደትን በተመለከተ ሂደቱንና ተጓዳኝ ጉዳዮችን በተመለከተ ከብልፅግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ምክትል ሃሳፊ ከጓድ መለሰ ዓለሙ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገናል።**

*አውደ ለውጥ፡- ድርጅታችንን ወደ አንድ ውሁድ አገራዊ ፓርቲ ለመቀየር ያነሳሱ መሰረታዊ ነጥቦች ምንድን ናቸው?*

*ጓድ መለሰ፡-* በዋናነት የድርጅታችንን ዓላማ ከማሳካት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በድርጅታችን ውስጥ ያሉ ድክመቶችና ችግሮችን በመቅረፍና በማስወገድ ዓላማውን እንዴት ማሳካት እንችላለን የሚለውን ለመመለስ ይቻል ዘንድ ከአደረጃጀት ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ችግሮች መፈታት አለባቸው የሚል ነው፡፡ እንደ ማሳያ ሊወሰድ የሚችለው ኢህአዴግ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን ማጠናከር ያለበት መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የአደረጃጀት ለውጡ ይህን ሊያረጋግጥ ይችላል የሚል

*“ብልፅግና የህዝቡን የመልማት አቅምን የበለጠ ለማጠናከር ያግዛል፡፡”*

መነሻ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት አገራዊ ራዕይን ዕውን ለማድረግ የፓርቲው ውህደት የበለጠ የሚያግዝ በመሆኑም ነው፡፡ ይህ ደግሞ የኢህአዴግ ወደ አንድ ውሁድ አገራዊ ፓርቲ መምጣት ለተጀመረው አገራዊ የህዳሴ ጉዞ የበለጠ ጉልበት ስለሚሆነው የፓርቲው ውህደት ቢካሄድ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል የሚል መነሻ መያዙን የሚያሳይ ነው፡፡

በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል የነበረው መነሻ የመጀመሪያው የፓርቲውን ወይም ደግሞ የግንባሩን የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን የማጠናከር፣ የአባላትንና የአመራሩን የሃሳብ ነፃነትን፤ አዳዲስ ሃሳቦች እንዲፈልቁ ማድረግና ድርጅቱ ተራማጅ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን በማስፋት እየገጠሙት ያሉ ችግሮች በሂደት ይቀረፋሉ የሚል እምነት የተያዘበት ነው፡፡

ለረጅም አመታት ፓርቲው አገር የመምራት እድል ያገኘ እንደመሆኑ መጠን የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲው በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በህዝቡ ውስጥ የሚካሄደው ዴሞክራሲ ላይ አዎንታዊም አሉታዊም ተፅእኖ የማሳረፍ እድል አለው፡፡ ስለዚህ በህዝቡ ውስጥ የሚካሄደውንም ዴሞክራሲ የበለጠ ለማስፋት የድርጅቱ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ መጠናከር አለበት፡፡ ይሄም ብቻ ሳይሆን ግንባር እንደመሆኑ መጠን በግንባሩ ውስጥ የሚተላለፉ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች እንደዚሁም እቅዶች በየደረጃው ተፈፅመው ውጤታማ ሆነው ህዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆንና ለሃገር የሚበጅ ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል በመሆኑም ነው፡፡

የድርጅቱ ዓላማና በድርጅቱ የሚመራው መንግስት የሚያወጣቸው ፓሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ተተግብረው ስኬታማ በማድረግ ሂደት ከአፈፃፀም ጋር የተያያዙ የዲሲፕሊን ጉዳዮችም እንደ አንድ ችግር ይነሱ ነበር፡፡ ስለዚህ ያልተማከለ አሰራር መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በመርህ ደረጃ ተግባራዊ ያለመሆን ችግሮች ነበሩ፡፡ እነዚህን ችግሮችም በመቅረፍ ድርጅቱ የተሻለ ውጤታማ ይሆናል፡፡ የድርጅቱ ዓላማም ይሳካል የሚል መነሻ ተይዞ ነው ውህደቱ ሲጀመር፡፡ ከዚህ ጋርም ተያይዞ በዋናነት ሲነሳ የነበረው ድርጅቱ መሪ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን በመንግስት ተቋም ውስጥ ያሉ ችግሮችንና ጉድለቶችን ነቅሶ ለማውጣትና በጋራ ለመፍታት ይረዳል፡፡ የጋራ አቅምንም አሰባስቦ የተሻለ ሁኔታ ለመፍጠርም አስፈላጊ እንደነበርም በመነሻነት ይወሰድ ነበር፡፡

አጋር ስለ ነበሩ ፓርቲዎች ስናነሳም በዋናነት ከተሳትፎ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ይሄም ከሀገር ግንባታ ሂደት ጋር የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲኖር ከማድረግ አንፃርና በወሳኝ የሃገሪቱ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች እንዲሁም ለእነዚህ እድል በሚሰጥ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የበኩላቸውን ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በአጋር ፓርቲዎች በኩል ረጅም ጊዜ ሲነሳ የነበረ ጥያቄ ነው፡፡ ከዚያም በላይ ከፍትሃዊ ተጠቃሚነትም ጋር ተያይዞ በሃገራዊ ጉዳይ ላይ ተሳትፏን ድምፃችንን አሰምተን በዚህም ልማታችን እንዲፋጠን በመሳተፍ በኩል ጉድለቶች አሉ ከሚል ፍትሃዊ ተጠቃሚነትም ጋር የሚነሱ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ ከተሳትፎም በላይ ይሄን ሁኔታም በማስተናገድ በሀገሪቱ ህዝቦች መካከል መተማመን በመፍጠር በአጠቃላይ የሃገር ግንባታው በተሻለ መንገድ እንዲጓዝ በመነሻነት እነዚህና የመሳሰሉ ምክንያቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

*አውደ ለውጥ፡- ከአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁነቶች አኳያ ውህደቱ ምን እንድምታና ፋይዳ ይኖረዋል?*

***“ከድርጅቱ ዓላማና ፕሮግራም ጋር ለብሮ መስራት የሚፈልጉ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ግለሰቦች ላሉ የብልፅግና በር ዝግ ለይደለም፡፡”***

*ጓድ መለሰ፦* የመጀመሪያው አሁን በአገራችን ውስጥ እየታየ ያለውን ወቅታዊ የፖለቲካ አዝማሚያ እንደ አንድ መነሻ መውሰድ ይቻላል፡፡ በአገራችንም ባለፉት ዓመታት የተለያዩ ችግሮች ተከስተዋል፡፡ ችግሮቹን ከመቅረፍም አንጻር ኢህአዴግ በእራሱ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ለመፍታት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በሂደትም የለውጥ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ አሁን ባለንበት የለውጥ ሂደት ውስጥ ተስፋም ስጋትም ይስተዋላል፡፡ በአገራችን ውስጥ ያለው የፖለቲካ ችግር ምንድን ነው የሚለውን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በርካታ ጉዳዮችን ማንሳት ቢቻልም አንዱና ዋነኛው ጽንፈኛ ብሔርተኝነት ነው፡፡ በመሆኑም ይህንንና ከእዚህ ጋር የሚያያዙ ችግሮችን ለመቅረፍ በውህደቱ የብልፅግና ፓርቲ እውንነት ከመነሻው አስፈላጊ ካደረጉ ምክንያቶች በተጨማሪ መፍትሄም የሚሰጥም ነው፡፡

እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ቁልፍ ጉዳይ ግን የአገራችንን የፖለቲካ ችግሮች በዋናነት ሊፈቱ የሚችሉት የአገራችን ህዝቦች መሆናቸውን ነው፡፡ የብልፅግና ፓርቲ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት የአካሄደው የፖለቲካ ሪፎርም ውጤት ነው፡፡ ከእዚህ አንጻር የፖለቲካ ፓርቲ ውህደቱ ለአገራችን የፖለቲካ ችግሮች መፍትሄ የመስጠት ጠንካራ አቅም አለው፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ አንዱ በአገራችን ራሱን እየለወጠ ለውጥን የመምራት ልምድ ያለው ፓርቲ በመሆኑና ይህም ትልቅ ሚና የነበረው በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው ድርጅቱ መሪ ፓርቲ ነው፡፡ ስለዚህ የብልፅግና ፓርቲም የመንግስትንም ኃላፊነት ይዞ የሚሰራ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን የአገሪቱን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ በመታመኑ የተፈፀመ ውህደት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ከእዚህ አኳያ የኢህአዴግን ውህደት ጉዳይ ወስደን ያየን እንደሆነ እንደ አንድ ፓርቲ ሳይሆን እንደ መሪ ፓርቲ በውስጡ የአደረገው ሪፎርም በድርጅቱ ውስጥ የሚቀር ብቻ ሳይሆን በህዝቡ ውስጥ የሚታየውን የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ በማገዝና ለስርዓቱ ግንባታ የተመቸ ሁኔታ ለመፍጠር የእራሱ አዎንታዊ ሚና ስለ አለው ውህደቱ ያግዛል ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ፋይዳ የአለውም ነው፡፡

ኢህአዴግ በአለፉት 28 ዓመታት አገሪቱንና ህዝቦቿን ወደ መጠነ ሰፊ እድገትና መሻሻል የመራ ቢሆንም በብሄራዊ ማንነት ላይ ትኩረት አድርጎ የሰራውን ያህል ለአገራዊና ለኢትዮጵያዊ ማንነት የሰራው ስራ ዝቅተኛ ነው፡፡ በእዚህ ምክንያት ደግሞ በብሄራዊ ማንነትና በአገራዊ (በኢትዮጵያዊ) ማንነት መካከል ያለው ሚዛን የጠበቀ አልነበረም፡፡ ይህ ሚዛን ባለመጠበቁ ምክንያት ደግሞ በዜጎችም ሆነ በሀገሪቱ አጠቃላይ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ አሳርፏል፡፡ በውህደት የብልፅግና ፓርቲ እውን መሆን ይህንን ሁኔታ በመቀየር በብሄራዊና በኢትዮጵያዊ ማንነት መካከል ያለውን ችግር ሚዛናዊ የማድረግ ፋይዳ አለው፤ ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ሁሉም በባለቤትነት ስሜት በአገሩ ባይተዋርነት ሳይሰማው የሚገነባት ኢትዮጵያን ይፈጥራል፡፡ በአራቱም አቅጣጫዎች ያሉ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች በነጻነት የሚንቀሳቀሱባትና አገሬ ብለው የቀደሙት አባቶቻችን የከፈሉትን ዋጋ እነርሱም የድርሻቸውን በመወጣት የሀገር ግንባታ በጠንካራ ህብረ ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚፈጥሩበትን መድላድል ያበጃል፡፡ እንዲሁም የአገርን ክብር ለመጠበቅ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ከዚህ አንጻር ውህደቱ ትልቅ ፋይዳ ያለውና ከለውጡ ጋርም ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡

## "ብልፅግና ፓርቲ 'የህብረተሰብን ዕድገት የሚመጥን የርዕዮተ ዓለም ግንባታ፣ አደረጃጀትና አሰራር ይኑረን' የሚለው አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡"

*አውደ ለውጥ፦ ውህደቱ ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ እንቅስቃሴዎች አንጻር ምን ፋይዳ ይኖረዋል?*

*ጓድ መለሰ፦* አገራችን ለመልማት የሚያስችል እምቅ ሀብት አላት፡፡ ስለዚህ ሪፎርሙ ወይንም ውህደቱ የህዝቡን የመልማት አቅምን የበለጠ ለማጠናከር ያግዛል፡፡ ይሄም ብቻ ሳይሆን በአራቱም አቅጣጫዎች የሚካሄዱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ይሳለጣሉ፡፡ ዜጎች በነጻነት ተዘዋውረው እንዲሰሩ፣ በዕውቀት፣ በጉልበት፣ በቴክኖሎጂ፣ በግብአትና በመሰረተ ልማት የመተሳሰር እድሉም ሰፊ ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁሉ ተደምረው የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ደረጃ ያሳድጉታል፡፡ ይህንን ማስፈጸም የሚያስችል አመራርና ምቹ ሁኔታን የመፍጠር እድልም አለው፡፡ በአጠቃላይ ለተጀመረው ሀገር በቀል ኢኮኖሚያዊ ሪፎርም መፋጠን ትልቅ አቅም ይሆናል ማለት ይቻላል፡፡ ከማህበራዊ ልማት አንጻር ካየን የመጀመሪያውና ከሁሉ በላይ በህብረተሰቡ ውስጥ ለዘመናት ሳይሸረሸር የቆየውን የአብሮነት ዕሴት የበለጠ ለማጎልበትና ማህበራዊ ትስስሩን ለማጠናከር ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

*አውደ ለውጥ፦ ብልፅግና ፓርቲ ውህደቱ በዚህ የሚያቆም ነው ወይ፡፡ ከአጋርና ሌሎች ፓርቲዎች ውጭ ያሉ የፖለቲካ ሃይሎች በሩ ዝግ ነው?*

*ጓድ መለሰ፦* የመጀመሪያው ሁለት ነገሮች መቀላቀል የለባቸውም፡፡ ፓርቲዎቹ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አቅማቸውን አጎልብተው የአገሪቱ ህዝቦችን ፍላጎት፣ ጥቅምና መብቶች ላይ ተመስርተው አማራጭ ፖሊሲዎችን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ይዘው በሚመጡዋቸው ፖሊሲዎች ላይም የሃሳብ ክርክር በማድረግ በዴሞክራሲ ስርዓት ወደ ስልጣን እየመጡ ተግባራዊ የሚያደርጉበት ሁኔታን ከመፍጠር አንፃር ሰብሰብ ማለቱ ጠቃሚ ነው፡፡

የቀድሞው ኢህአዴግም በእራሱ ይህንን ጥሪ ከለውጡ ጋር አያይዞ ሲያስተላልፍ ቆይቷል፡፡ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ተመሳሳይ ጥሪ እያስተላለፉ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ ከእዚህም አለፍ ሲል ተጨባጭ እርምጃዎችም ሲወሰዱ እንመለከታለን፡፡

ፓርቲዎች መሰባሰብ ጀምረዋል፡፡ ይህ የሚበረታታና መቀጠልም ያለበት ነው፡፡ የፓርቲዎች ጥሪና ውህደት በብልፅግና ደረጃም በተመሳሳይ መንገድ የሚታይ ነው፡፡ ከእዚህ አንፃር የመጀመሪያው ሰብሰብ ብሎ ከመታገል አኳያ በብልፅግና በሩን አይዘጋም፡፡ ተመሳሳይ ዓላማና ፕሮግራም ካላቸው አካላት ጋር አብሮ ለመስራት ዝግጁ ነው፡፡ ከድርጅቱ ዓላማና ፕሮግራም ጋር አብሮ መስራት የሚፈልጉ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ግለሰቦች ካሉ የብልፅግና በር ዝግ አይደለም፡፡ ይህን እንዲያደርግ የሚያስገድደው የተራማጅነት ባህሪውና የፖለቲካ አስተሳሰቡ ከህብረተሰቡ የአስተሳሰብ እድገት ጋር አብሮ የሚጓዝ በመሆኑ ነው፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ዘላቂ ልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት በእዚህች አገር እንዲሰፍን የሚታገል ፓርቲ እስከሆነ ድረስ፣ አላማው፣ መርሆዎቹና እሴቶቹ ማዕከላቸው ህዝብ ነው፡፡ ከማንኛውም ለህዝብ ከሚሰራ ፓርቲ ጋር ደግሞ አብሮ ለመስራት ይገደዳል፡፡ የብልፅግና ፓርቲ አመለካከትና ርዕዮቱ፤ ድርጅታዊ አሰራሩም ሆነ አደረጃጀቱ የራሱ ብቻ ንብረት ሳይሆን ህዝባዊ ነው፡፡ ይህን ዘመን ተሻጋሪ አስተሳሰብ የሚቀበሉ ዜጎችም ከድርጅቱ ጋር ሊታገሉ ይችላሉ፡፡

ሁለተኛው ውህደትን የሚመለከት ነው፡፡ ይህን በሚመለከት የብልፅግና ፓርቲ ውህደት የአደረገው በፓርቲው ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ በፓርቲው ውስጥ ብሔራዊ ድርጅቶች አሉ፡፡ ከዚህም

*"ከድርጅታችን ፕሮግራም ጋር ተያይዞ ለውጥ ሲኖር ለውጡ የሚወሰነው ትልቁ የስልጣን አካል በሆነው ጉባዔ ነው፡፡"*

ባሻገር ደግሞ በአላማና በፕሮግራም ደረጃ የሚቀራረቡ አጋር ድርጅቶችም አሉ። በመሆኑም ውህደቱ በእነዚህም መካከል ያለው የአላማና የፕሮግራም መቀራረብና ከትግሉ ዓላማና ጉዞአችን ካለው ፋይዳ አንፃር የተከናወነ ነው። ከእዚህ ባሻገርም ብልፅግና አመራር ከሚሰጥባቸው አካባቢዎች ጋር በተያያዘ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አመራር ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ ቢፈጠር የተጀመረው አገራዊ የለውጥ ጉዞ የበለጠ ውጤታማና ስኬታማ ይሆናል የሚል መነሻ በመኖሩ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የብሔራዊ ድርጅቶቹ ጽኑ ፍላጎትና የአጋር ፓርቲዎች የረዥም ጊዜ ጥያቄ በመሆኑም ጭምር ነው። ይህ ደግሞ የኢህአዴግም ፍላጎት ነው።

*አውደ ለውጥ፦ ውህደቱ ከድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ጋር አልተጣረሰም ማለት ይቻላል ወይ? ወይንስ የፕሮግራም ለውጥ ተደርጓል?*

*ጓድ መለሰ፦* ከድርጅታችን ፕሮግራም ጋር ተያይዞ ለውጥ ሲኖር ለውጡ የሚወሰነው ትልቁ የስልጣን አካል በሆነው ጉባኤ ነው። ከእዚህ አንጻር በ11ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ላይ የፕሮግራም ለውጥ አልተደረገም። በጥልቅ ተሀድሶአችን ውይይት ወቅት ከፕሮግራም ጋር ተያይዞ ያሉ የማሻሻያ ሃሳቦች ካሉ እነዚያ ሃሳቦች በፖሊሲ ደረጃና በማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ደረጃ የሚታዩ መሻሻሎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ይህ በጥናትና ተከታታይነት ባለው ውይይት እየታየ የሚሔድ ቀጣይ ስራ ነው። መያዝ ያለበት ቁም ነገር በአሁኑ ሰዓት ምንም አይነት የፕሮግራም ለውጥ አለመደረጉን ነው። ይህ ማለት ግን በፖለቲካ ፕሮግራም ውስጥ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች በቀጣይ አይሻሻሉም ማለት አይደለም።

የፖለቲካ ሪፎርም አውጀናል። ይህም የፖለቲካ ሪፎርም አካል ይሆናል ማለት ነው። ምንም ዓይነት ሃሳብ በማሻሻያነት ሊመጣ ይችላል፤ ሲመጣም ውይይት መደረግ አለበት። አሁን ካለንበት የህብረተሰቡ የእድገት ደረጃና ከፓርቲው ተራማጅነት አኳያ የርዕዮተ አለም ግንባታውን በቀጣይነት ያካሄዳል። ይህን ለማሳካት የሚያግዙ አደረጃጀቶችንም እንደዚሁ እያስተካከለ ይሄዳል። የአመራር ሪፎርሞችም በተከታታይነት የሚደረጉ ይሆናሉ። ከእዚህ አንጻር አሰራሮችን ሪፎርም ማድረግ ተጀምሯል። ይህም በፕሮግራም ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ሃሳቦችን በመለወጥ አሁን ያለውን አገራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ለውጥ የሚደረግ ለመሆኑ ያለፉት የፓርቲው ልምዶች ያሳያሉ።

ለምሳሌ ኢህአዴግ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም አስተሳሰብ ወደ ካፒታሊዝም ስርዓት ለውጥ አድርጓል። አሁን የሚታዩ ለውጦችም ከእዚህ በላይ አይደሉም። ኢህአዴግ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ላይ የደረሰው ከህብረተሰቡ እድገት ጋር የሚስማማ የፖለቲካ አስተሳሰቦችን እየቃኘ፤ እየለወጠና እየተለወጠ ስለመጣ ነው። ከእዚህ ተነስተን ልንናገር የምንችለው ዶግማቲክ የሆነ አስተሳስብ በብልፅግና ውስጥ የሚሰራ አለመሆኑን ነው። ብልፅግና ፓርቲ ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለነፃነት የቆመ ፓርቲ ነው። የፓርቲው ዓላማና ፕሮግራም የሚገዛው ለሀገራችን ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ነው። ይህ የድርጅቱ መሰረታዊ ባህሪ በአግባቡ መታወቅ አለበት። ስለዚህ አሁንም የፕሮግራም ጉዳይ የሚታየው በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ነው።

በ11ኛ ጉባኤያችንም ፕሮግራምን በሚመለከት ለወጣቱ ትውልድ ፕሮግራሞቻችንን እና አቅጣጫዎቻችንን ሳቢ እና ወጣቶችን ሊያሳትፍ በሚችል መንገድ፣ አገሪቱ ከደረሰችበት አንፃር የአገር ግንባታውን ወደፊት በሚያስቀጥል እና ኢኮኖሚያችን ከደረሰበት ደረጃ አንፃር እያሻሻልን እንደምንሄድ በግልፅ አቅጣጫ ተቀምጧል።

ውህደት መፈፀም አለበት የሚል አቅጣጫ ሲቀመጥ ለምሳሌ የፕሮግራም ማሻሻል ካስፈለገ ደንቡ ውስጥ ማሻሻልን የሚፈቅድ ከሆነ በቂ ዝግጅት ተደርጎ በፓርቲው አካሄድ መሰረት

የማይሻሻልበት ምክንያት የለም፡፡ ይህን ማለት ግን ተሻሽሏል ማለት አይደለም፡፡ ፕሮግራሙ አልተነካም፡፡ ውህደቱ ላይ ስንሄድ ማሻሻያ ጉዳዮች ከተነሱ የፓርቲውን የማሻሻል አሰራር ተከትሎ ነው የሄደው፡፡ ስለዚህ ጉባኤው ይህንንና ደንቡን ይወስናል ማለት ነው፡፡ እንዴትና በምን አግባብ ይሆናል ለሚለው በዕቅድና በጋራ የሚታይ ነው፡፡ በፓርቲውም ውስጥ የሚደረግ ውሳኔ ነው፡፡ ጉዳዩ በስራ አስፈጻሚውና በምክር ቤቱ አጀንዳ መሆን አለበት፡፡ ጉባኤውምጋ መድረስ አለበት፡፡ እነዚህ አካላትጋ ሳይደርስ ፕሮግራም ሊሻሻል አይችልም፡፡ ስለዚህ በፓርቲያችን ውስጥ የፕሮግራም ማሻሻያን በሚመለከት ተካሂዷል የሚባለው ትክክል አይደለም፡፡ ስህተት ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ብልፅግና ፓርቲ የሚገነባው የልማት እና የዴሞክራሲ መስመር ነው የሚለውን ጉዳይ በግልፅ ያስቀመጠ በመሆኑ አላማውና ፕሮግራሙ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የድርጅቱ አመራሮችና አባላት የፕሮግራም ለውጥ ጉዳይን በዚህ ማዕቀፍ ማየትና የፕሮግራም ለውጥ አለመደረጉን፤ የተደረጉ ተወሰኑ ማሻሻያዎችም በፓርቲው አሰራር መሰረት መሆኑን የፕሮግራም ለውጥ ካስፈለገም ለሚቀጥለው ጉባኤ በአጀንዳነት የሚዘጋጅ መሆኑን መገንዘብና ለሌሎችም ማሳወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚያ መለስ ግን የፕሮግራም ሀሳቦች በጥናት ላይ የተመሰረቱ በፓርቲው ውሳኔ የፕሮግራም ማዕቀፍ ፕሮግራሙን ሊመግብ የሚችል፣ ስትራቴጅውን ሊደግፍ የሚችል ታክቲካል እርምጃዎችን ፓርቲው እየወሰደ የሚሄድና የፖለቲካ ሪፎርም መጀመሩን ተገንዝቦ በዚህ ደረጃ ማየት ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

*አውደ ለውጥ፦ ከውህደቱ ጋር ተያይዞ የመደመር እሳቤ የፓርቲውን ፕሮግራም የተካበት ሁኔታ ይኖር ይሆን?*

*ጓድ መለሱ፦* መደመር የድርጅቱን ፕሮግራም አይተካም፡፡ የመደመር እሳቤ አነሳሽ በሆኑት በድርጅታችን ሊቀመንበርና የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶክተር አብይ አህመድ እሳቤው ቀርቧል፤ በብዙ ሺህዎች ታትሞ በየሰው እጅ ገብቷል፤ ስልጠናዎችም በስፋት እየተሰጡ ነው፤ እንዲሁም ምሁራንም ወስደው የበለጠ ምርምር የሚያደርጉበት አጀንዳ እስከመሆን ደርሷል፡፡ የተጀመረው ሀገራዊ ለውጥ የመጣበት እሳቤ እንዲሆን የተዘጋጀ በመሆኑ ኢህአዴግም እንደ አንድ የለውጥ ሃይል ለጀመረው የፖለቲካ ሪፎርም ይጠቅመዋል፡፡

ስለዚህ የመደመር እሳቤ የሚመዘነው ከዚህ አንጻር ነው፡፡ አገርን የማዳን ስራው፣ ህዝብ ከደህንነት ስጋት መውጣቱ፣ ስርዓቱ መቀጠሉ፣ ከስጋት ውስጥ ለመውጣት ያለን እድል በእነዚህ በእነዚህ እየተመዘነ የበለጠ ወደሚፈለገው ደረጃ መሄድ የሚችል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የመደመር እሳቤ ቢያንስ ይቺ ሀገር ከጥፋት ጎዳና እንድትመለስ የራሱ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው ማለት ነው፡፡

በአገር ውስጥም ከአገር ውጭም ያሉ የአገራችን ዜጎች የመደመር እሳቤ ይፋ ሆኖ ኃይል አሰባስቧል፡፡ ስለዚህ በሀገር ውስጥም በውጭም የሚኖሩ ዜጎቻችን ቢያንስ ተስፋ እንዲሰንቁ አድርጓል፡፡ ብዙ ውጤቶችም ተገኝተውበታል፡፡ ይሄ እሳቤ በ11ኛው ድርጅታዊ ጉባዔ ላይ መርህ ሆኖ ወጥቷል፡፡ ስለዚህ ድርጅቱ ገዝቶታል ማለት ነው፡፡ መደመርም የጉባዔው ውሳኔ ሆነ ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ የመደመር እሳቤ ሀገራዊ ለውጡ የሚመራበትና የለውጡ ማዕቀፍ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም ለውጡ ብዙ ፍላጎቶች ያሉበት በመሆኑና ከሪፎርም በመጀመሩ የተለያዩ የለውጥ ፍልስፍና የተለያዩ ተዋንያን የሚሳተፉበትና አንዳንዶች ፍላጎቶችም

*“አንድ ፓርቲ የራሱን ውህደት ስለፈፀመ የመንግስት ስርዓት፣ ህገ መንግስታዊ ስርዓት ይጨፈለቃል ማለት አይደለም፤ ስርዓቱም አይፈቅድም፤ ሊሆንም አይችልም፡፡”*

ፅንፍ የወጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይሄ ዓይነቱ የበዛ የለውጥ ፍላጎት እንዴት ነው የሚስተናገደው? ሀገሪቷስ ሁልጊዜ በአብዮት መናጥ አለባት ወይ? ሲባል ቢያንስ አገራዊ አጀንዳና አገሪቱ የምትመራበት የጋራ የሆነ መነሻ መኖር አለበት በሚል የለውጡ ፍኖተ ካርታ ሆኖ የመደመር እሳቤው ቀርቧል ብዬ አስባለሁ፡፡

ከዚህ በመነሳት ይህን ፍኖተ ካርታ፣ ወይም ለውጡ የሚመራበትን ማዕቀፍ ወይንም እሳቤ ብልፅግናም ሊገዛው ይችላል፤ ደግሞም ጀምሯል፡፡ ለጀመረው የፖለቲካና የፓርቲው ሪፎርም ማለት ነው፡፡ መንግስትም ለመንግስት ሪፎርም ይጠቀምበታል ማለት ነው፡፡ ተስፋ አደርጋለሁ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ይጠቀሙበታል ብየ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ የለውጡ ፍኖተ ካርታ የሆነው መደመር ዴሞክራሲያችን የሚሰፋበትን እድል የሚሰጥ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይሄ ማለት በባለፈው የዴሞክራሲው መንገድ ጠብቧል ብለን የገመገምነው ሲሆን ለውጥ መምጣት ካለበትም በዚህ መንገድ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለውጡ የሚመራበት ማዕቀፍ ነው፡፡

ወደ ፓርቲውም ስናመጣው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫን እንደሚተካ በማስመሰል የሚራመዱ ሀሳቦች ትክክል አይደሉም፡፡ ፕሮግራሙም በራሱ ስርዓት ነው መሻሻል የሚችለው፡፡ ለፕሮግራምም ሆነ ለደንቦች መሻሻል፣ ለተፈጸመው ውህደትና በአጠቃላይ ለሀገራዊውና ለፓርቲው ሪፎርም ከመደመር እሳቤ የወሰድናቸውና በቀጣይም የምንወስዳቸው ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮች አሉ፡፡ ይህንን ደግሞ ፓርቲያችን በየደረጃው እየመከረና እየወሰነ የሚሄድና በፓርቲ ሂደት ውስጥ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ከፓርቲ ፕሮግራም ለውጥ ጋር ተያይዞ ተክቷል የሚለው ሀሳብ ግን ትክክል አይደለም፡፡ የመደመር እሳቤን ለሪፎርማችንና ለለውጣችን አንጠቀምም ማለት ግን አይደለም፡፡ እየወሰንን የምንጠቀመው ይሆናል፡፡ ሀሳቡ ቀርቧል የሚጨመር ካለ እየጨመረ የሚቀነስ ካለም እየተቀነሰ በጥቅሉ እየዳበረ ይሄዳል፡፡ ሀገራዊ ለውጡ በብቃት መመራት አለበት፡፡ ሀገራዊ ለውጡ ሲመራ ደግሞ ብልፅግና መሪ ፓርቲ በመሆኑ የገዢ ፓርቲው አመራሮች ተነሳሽነቱን መውሰድ አለባቸው፡፡ የድርጅታችንን ሊቀመንበርና ጠቅላይ ሚንስትራችን ዶክተር አብይ አህመድ የመደመር ፅሳቤን በተነሳሽነትና በቁርጠኝነት ማቅረብ መቻላቸው ሊበረታታና ቀጣይነት ሊኖረው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ነውም መታየት ያለበት፡፡

*አውደ ለውጥ፡- በክልል ደረጃ ካለው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በብልፅግና ውስጥ እንዴት ነው ሊተገበር የሚችለው?*

*ጓድ መለሰ፡-* ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳይ የፓርቲ ጉዳይ ሳይሆን የመንግስት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሲባል የመንግስት አስተዳደር ጉዳይ ነው የሚሆነው ማለት ነው፡፡ የፌዴራል ስርዓቱን በሚመለከት በህገ መንግስቱ በግልፅ የተቀመጠ ስለሆነ እራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳይ በህገ መንግስቱና በህገ መንግስታዊ አስተዳደር ስርዓቱ የተመለሰ ነው፡፡ የፓርቲው ማሻሻያ ሁሉም በሁሉም አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች እኩል ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ዕድል ለመፍጠር የሚያግዝ ነው፡፡ እራስን በእራስ የማስተዳደር ጉዳይ ከብሔር ማንነት ጋር ብቻ ሊታይ አይገባም፡፡

የኢህአዴግ አባል የነበረውን ደኢህዴንን ለአብነት ወስደን ብንመለከት 56 ብሔር ብሔረሰቦችን የተለያዩ ፓርቲዎች ተዋህደው አንድ ፓርቲ ሆነው መምራት ችለዋል፡፡ ይህ ለአገሪቱ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በብልፅግና ፓርቲም ውስጥ እንደዚህ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የድርጅቱ ውህደት በዋናነት በሁሉም የአስተዳደር አካባቢዎች ላይ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት

*"ተግዳሮቶችን አስረ መሰረታቸው ለመፍታትም የተዋሃደ ህብረ ብሄራዊው ብልፅግና ሰውን መሆን ትልቅ ፋይዳ ያለው እና ጥሩ እድል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡"*

ተጠብቆ፤ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ተጠናክሮ፤ ጠንካራና የተናበበ አመራር በመፍጠር የተቀናጀ አመራር ለመስጠት ብሎም አገራችንና ህዝቦቿን ከድህነት እንዲወጡ የማድረግና እዚህም እዚያም የሚታዩ ችግሮችንም መልክ ለማስያዝ ዕድል የሚሰጥ ነው።

ከእዚህ በዘለለ የፓርቲ አመራሩ በሚመራቸው ተቋማትና በመንግስት አገልግሎቶች ውስጥ ያሉትን ለስርዓቱ እንቅፋት የሆኑና ህዝብን የሚያስመርሩ ሌብነትና መሰል ችግሮችንም ወጥ በሆነ መንገድ ያለ ድንበር ለማስተካከል፣ ብሎም የአቅም ችግሮችንም በጋራ ለመፍታትና ለመደጋገፍ የበለጠ አቅም ይሆናል ተብሎም ይታሰባል። በመሆኑም የፓርቲው የውህደት አላማና የመንግስት አስተዳደር ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው። እርስ በእርስ እንዲናበቡ ለማድረግ ግን የውህደቱ ውጤት የሆነው ብልፅግና ፓርቲም በጣም ይጠቀማል ተብሎ ነው የሚወሰደው።

*አውደ ለውጥ፦ እራስን በእራስ የማስተዳደር ጉዳይ መንግስታዊና ህገ-መንግስታዊ ከሆነ በተዋሃደው ህብረ ብሄራዊ ፓርቲና በመንግስት መካከል የሚኖረው ግንኙነት ምን አይነት ነው የሚሆነው?*

*ጓድ መለሰ፦* የፓርቲው ውህደት ባለው ህገ መንግስታዊ ስርዓት፣ ባለው የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ለዓላማው የሚታገልበት እንጂ አንድ ፓርቲ የራሱን ውህደት ስለፈፀመ የመንግስት ስርዓት፣ ህገ መንግስታዊ ስርዓት ይጨፈለቃል ማለት አይደለም፤ ስርዓቱም አይፈቅድም፤ ሊሆንም አይችልም።

ይልቁንም እስከ አሁን ድረስ የመጣንበት ጅምር ፌዴራላዊ ስርዓት ከእንከን የፀዳ እንዳልሆነ ብዙ ችግሮች እንደሉበት ባለፉት አመታት ታይቷል። ጥንካሬ እንዳለው ጉድለትም አለው ማለት ነው። ስለዚህ ብልፅግና ጉድለቶችን ሊፈታ የሚችል የፓርቲ አቋም የአለው ሆኖ በውህደቱ ተፈጥሯል። በመሆኑም እውነተኛ የፌዴራል ስርዓት እንዲመጣ ያግዛል። ከተሳትፎ አንፃር የነበረውን ጉድለት ይፈታል። አገር ስለሆነ የምንገነባው በአራቱም ጫፍ ያሉት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በአገር ግንባታ ላይ እኩል የሚሳተፉበትን እድል ይሰጣል።

ከመንግስትና ከፓርቲ ጋር ያለው ግንኙነት አሁን ባለው አደረጃጀት እና ቀጥሎ ውህደት ይፈፀማል ከተፈፀመው ውህደት ጋር ወስደን ካየነው ምንም አዲስ ነገር የለውም። ተዋሃደ ማለት ብልፅግና ህብረ ብሄራዊ ሀገራዊ ፓርቲ ሆነ ማለት ነው። ብልፅግና በየደረጃው ያሉ የመንግስት እርከኖች በህገ-መንግስቱና በመንግስት አስተዳደር መሰረት ለእዚያ የሚሆነውን ስልጣን በመውሰድ አመራር ይሰጣል። መሪ ፓርቲ ገዥ ፓርቲ ይሆናል ማለት ነው። ለምሳሌ ኢህአዴግ አራት አባል ድርጅቶች ነበሩት፣ አጋሮች ነበራቸው። ፓርላማው ላይ እነዚህ የጋራ ስምምነት አላቸው። በጋራ ስምምነታቸው መሰረት ገዥው ፓርቲ ከአጋር ፓርቲው ጋር መንግስት መስርተዋል። የመከልከል ነገር የለም ማለት ነው። ቢዋሀዱም ባይዋሀዱም የሚከለክል ነገር የለም።

የውህደቱ ጉዳይ የመጣው ፓርቲውን ለማጠናከር ነው። የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አንዱ ማሳያም ይኸው ነው። ፓርቲዎቹ በየአካባቢያቸው በሚመሩበት ወይም ደግሞ አመራር በሚሰጡበት ክልልና ዞን የሚነሱ ጉዳዮች ፓርቲው ሲዋሀድ በጋራ አመራር ያገኛሉ፤ በጋራ ይወስናሉ፤ በጋራም ይፈፅማሉ። ስለዚህ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት እና ያልተማከለ አሰራር ሚዛናቸውን ጠብቀው የበለጠ ይጠነክራል ማለት ነው።

ኢህአዴግ በመሪነት ዘመኑ አገራዊ ፓርቲነቱን ይዞ ነው ፓርላማ ላይ መንግስት የመሰረተው። ብልፅግናም ይህን በይበልጥ ከማጠናከር ውጪ የሚያላላው አንዳችም ነገር የለም። በድርጅቱ ውስጥ ታቅፈው ያሉ ፓርቲዎች ስለተዋሀዱ ነው የበለጠ ጠንካራ የሚሆኑት።

*አውደ ለውጥ፦ ውህደቱ መካሄዱ ተገቢ አይደለም ለሚሉ ወገኖች ምላሽዎ ምንድን ነው?*

*ጓድ መለሰ፦* ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ለውጡንና ውህደቱን አሰናስሎ ማየት ያሻል።

በመጀመሪያ ደረጃ ለውጡ ውህደቱን የሚያፋጥን ዕድል እንጂ የሚጎትት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ውህደቱ ለለውጡ ሞተር ስለሆነ በእጅጉ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ብልፅግና ፓርቲ 'የህብረተሰብን ዕድገት የሚመጥን የርዕዮተ ዓለም ግንባታ፣ አደረጃጀትና አሰራር ይኑረን' የሚለው አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡ በውህደቱ ዙሪያ ከመነሻው ውይይት እየተደረገበት የመጣውም ለእዚህ ነው፡፡ ለውጥ አስፈላጊና አይቀሬ መሆኑን ኢህአዴግ ቢገነዘበውም ፈጥኖ ምላሽ ባለመስጠቱ ምክንያት ለውጡ በህዝብ ተገፍቶ መጥቷል፡፡ በኢህአዴግም እየተመራ ነው፡፡

ባለፉት ዓመታት በድርጅቱ መሪነት የተከናወኑ ተግባራት ያመጡት አዳዲ ፍላጎትና በመልካም አስተዳደርና በብልሹ አሰራር ሳቢያ የተከሰቱ የህዝብ ቅሬታዎች ተደማምረው የለውጥ ሂደቱ እንዲፈጥን አድርገዋል፡፡ ስለዚህ ለለውጡ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ኢህአዴግ ውህደቱን አጠናክሮ ምላሽ መስጠቱ ተገቢ በመሆኑ ነው የተፈፀመው ነው፡፡ ይህ መሆኑ ለውጡና ሂደቱ በጣም እንዲገጣጠሙ አድርጓቸዋል፡፡ ውህደቱ የአረፈደ ግን ፈጥኖ መካሄድ የነበረበት መሆኑ መፍጠን ያለበት ጥሩ እድል ነው፡፡ ብልፅግና ይህንን እድል ተጠቅሞ የለውጡን ፍላጎት በአግባቡ ሲመራ አላማውን ለማሳካት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት ነው፡፡ ለውጡ ዴሞክራሲው እንዲሰፋ እድል ፈጥሯል፡፡ ዴሞክራሲው መስፋቱ የሚጠቅመው ብልፅግናን ነው፡፡ ዴሞክራሲ የሚገለጸው ከህዝቡ አንፃር ስለሆነ ከጠበበ ብልፅግና በምንም መንገድ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

ሁለተኛው ለውጡ ውጤታማ እንዲሆን ኢህአዴግ በውስጡ የፖለቲካ ሪፎርም ማካሄድ ነበረበት፡፡ ከፖለቲካ ሪፎርሙ ውስጥ አንዱ ይህን የውህደት ጥያቄን ማፋጠን ነበር፡፡ ለዚህ ነው ጉባኤው "ዘግይቷል መፍጠን አለበት" ብሎ የወሰነው፡፡ ጉባኤው ደግሞ የለውጡን ሂደት እውቅና የሰጠና ተቋማዊ ያደረገ ነው፡፡ ስለዚህ ውህደቱና ለውጡ በዚህ ደረጃም ይተሳሰራሉ ማለት ነው፡፡

ለውጡን ለመምራትና ስኬታማ ለማድረግ እንዲሁም ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የለውጥ ፍላጎት መንስኤ የሆነውን የዴሞክራሲ ችግር መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ተግዳሮቶችን ከስረ መሰረታቸው ለመፍታትም የተዋሃደ ህብረ ብሄራዊው ብልፅግና ዕውን መሆን ትልቅ ፋይዳ ያለው እና ጥሩ እድል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ለውጡ ቀጣይነት እንዲኖረው ደግሞ ብልፅግና የመሪነት ሚናውን በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል፡፡

ስለዚህ ኢህአዴግ በራሱ የሚያደርገው ለውጥ ለሀገሪቱ የለውጥ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ትልቅ አቅም ነበር ተብሎ ይወሰዳል፡፡ ደግሞም ነው፡፡ ስለሆነም ለውጡ ስኬታማ እንዲሆን የሁሉንም የለውጥ ሃይሎች ድጋፍ ይፈልጋል፡፡ እስካሁን የመጣንበትን መንገድ ወስደን ስናይ ውህደቱ አጀንዳ ሆኗል፣ በጉባዔውም ውሳኔ አግኝቷል፣ ተግባራዊ መደረግ አለበት ተብሎም ጉባዔው ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ተፈጽሟል። ይህንንም አቅጣጫ መሰረት በማድረግ አቅደን ስራዎችን በመስራታችን ውጤት አግኝተናል። ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ውህደቱን አስፈላጊና እንዳይዘገይ የአደረጉ ሁኔታዎች ነበሩ። ፓርቲው ህዝቡና ሀገሪቷ የደረሱበት የእድገት ደረጃ እንዲሁም ህዝቡ ውስጥ ያሉ የእርካታ ችግሮች ሰፊ ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች አሉ፡፡ ግጭቶችና የግጭት መነሻዎች አሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች በሙሉ መፈታት አለባቸው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ የተለያዩ ጽንፈኝነቶች ይንጸባረቃሉ፡፡ እነዚህ በሙሉ ተደምረው በሚታዩበት ጊዜ ያኔ 'ፓርቲው መዋሀድ አለበት፤ የተጠናከረ አመራር መስጠት አለበት' የተባለው ምናባዊ ጉዳይ አሁን ላይ ምላሽ መሰጠት እንዳለበት የሚያስገድድ ነባራዊ ሁኔታ መፈጠሩ ዋነኛው ነው፡፡

**"የመደመር እሳቤ ቢያንስ ይቺ ሀገር ከጥፋት ጎዳና እንድትመለስ የራሱ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው ማለት ነው፡፡"**

በዚህም ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ጉዳዩን ተረድቶና ተገንዝቦ የለውጡን ፍላጎት በማወቅ መዳረሻውን አስቀምጦ ለውጡን በትክክል የመምራት ሀላፊነት የፓርቲው ነው፡፡ ምክንያቱም የመንግስትን ስልጣን ይዞ እየመራ በመሆኑ፡፡ ከዚህ አንጻር ፓርቲው ተራማጅ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ራሱን እየለወጠ ለውጡን መምራትና በለውጡ ደግሞ ለህዝቡ የተገባውን ቃል ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ የህዝቦች ችግር ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡ የዚህ ሀገር ችግር ቶሎ ተፈትቶ ከቀውስ መወጣት ይኖርበታል፡፡ ይሄ ካልሆነ ደግሞ እንደ ሀገር የህልውና ጥያቄ ይመጣል ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የፓርቲ ውዴታም ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነበረበት ማለት ነው፡፡

በእነዚህና ሌሎች መሰረታዊ ምክንያቶች ውህደቱን ማፋጠን ለነገ የሚባል ጉዳይ አልሆነም፡፡ መፋጠን እንዳለበት ታቅዶና አቅጣጫ ተቀምጦ ተሰርቷል፡፡ ብሄራዊ ድርጅቶቹም ውህደቱን በሚመለከት ጥናቱን መነሻ በማድረግ ተወያይተው ለጥናቱም ግብዓት የሚሆን ሀሳብ በመስጠታቸው በስራ አስፈፃሚም ሆነ በምክር ቤት ደረጃ ውይይት ተደርጎ ውህደቱ ይሁንታ ያገኘው፡፡ የብልፅግና ፓርቲ ፕሮግራም እና ህገ ደንብም በዚህ ውይይት የጋራ ሆኖ ፀድቋል፡፡ አብዛኞቹ ብሄራዊ ድርጅቶች እራሳቸውን አፍርሰው ወደ ውህደቱ መግባት ጀምረዋል፡፡ የአጋር ፓርቲዎችም በየራሳቸው መድረክ መክረው የብልፅግና ፓርቲ ውህድ አካል ሆነዋል፡፡ በየደረጃው የሚገኘው አባላትም እየተወያዩበት ነው፡፡ የፓርቲው ጉዳይ የፓርቲ ጉዳይ ብቻ ሆኖ የሚቀር ስላልሆነ በአንድም በሌላም ምክንያት ህዝቡንም ይመለከታል፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችም የሚሳተፉበት እቅድ ወርዶ ተግባራዊ እየሆነ ነው፡፡

በአጠቃላይ ውህደቱ ፈጥኖ ማለቁ ለሀገራዊው ለውጡ ምላሽ የሚሰጥ እንጂ ምንም የማያመጣው ችግር የለም፡፡ ለድርጅታችንም ወሳኝ ለሆኑ የህልውና ጉዳዮችም ምላሽ ሰጥቷል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጭ በፓርቲም ሆነ በመንግስት ለውጡ ለውጥ ነው፡፡ ስለሆነም በለውጥ ሂደት በርካታ ተግዳሮቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ተግዳሮቶችንም ማለፍ ደግሞ ይጠይቃል፡፡ ያለ ተግዳሮት ደግሞ ለውጥ ሊመጣ አይችልም፡፡ ስለዚህ ሀገራችንም ሆነች ድርጅታችን ባሉበት ሁኔታ ይህንን ውህደት እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ መሄድ በአንድም በሌላም መንገድ አስፈላጊና የግድ የሚል ነባራዊ ሁኔታና ጊዜ ላይ መሆናችን ልብ ሊባል ይገባል፡፡

*አውደ ለውጥ፡- አሁን የተፈጸመው ውህደት የሚጠበቅበትን ውጤት እንዲያስገኝ ከብልፅግና ፓርቲ አባላትና አመራር ምንድን ነው የሚጠበቀው?*

*ጓድ መለሰ፡-* በብልፅግና ውስጥ ለውጡ ሀገራዊና አንድነትን የሚያረጋግጥ መሆኑ ስለታመነበት የለውጡ ቀጣይነት እንዲረጋገጥ ተሰርቷል፡፡ ለውጡ ሀገራዊ ስለሆነ የሀገር ክብር የሚያጎናፅፍ መሆን መቻል አለበት፡፡ በመሆኑም አገራዊ አንድነትና ክብርን የሚያጎናፅፍ ለውጥ ለማድረግ ሁሉም ዜጋና የፖለቲካ ሀይሎች መረባረብ አለባቸው፡፡ ድርጅታችንም የሚመራው ለውጥ ስለሆነ ከሀገራዊ የለውጥ ፍላጎት ተነጥሎ ሊቆም ስለማይችል ሀገራዊ ለውጡን ከዳር ለማድረስ ራሱን ማዘጋጀት አለበት፡፡ ከውህደቱ ጋር ተያይዞ አመራሩም ሆነ አባሉ የራሱ ጉባኤ ውሳኔ ስለሆነ የጉባኤውን ውሳኔና አቅጣጫ ተከትሎ የመጣው ብልፅግና ፓርቲ ጠንካራ አመራር እንዲሰጥና ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም በየደረጃው ርብርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህ ማለት የሁሉ ሃላፊነት ስለሆነ ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው የፓርቲው ውህደት ጥቅሙ ከምንም በላይ የብልፅግና ፓርቲ አባልና አመራር እንደሚገነዘበው ሁሉ የእስካሁኑን የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ተግዳሮቶችን እና ከዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ችግሮች የህዳሴ ጉዟችንን እንዳያደናቅፉ ለማድረግ ካለው ፋይዳ አንፃር ሊታይ ይገባል፡፡

የድርጅታችን አመራርና አባላት የሀገራችንን ህዳሴ እውን ለማድረግ ለምንፈጥረው አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ግንባታ ሂደታችን ያለንን አቅም አስተባብረን መረባረብና መታገል ከምንጊዜውም በላይ አስፈላጊ የሆነበት ወቅታዊ ፖለቲካዊ ጉዳይ ውስጥ ስለምንገኝ ውህደቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን አገራችን ለምትገኝበት ፈታኝ ሁኔታ በጣም ጠቃሚ በመሆኑ ለውጤታማነቱ የበኩላቸውን ርብርብ ማድረግ አለባቸው። ሚናቸውንም መጫወት አለባቸው፡፡ ብልፅግና በዚህ ሀገር ዴሞክራሲ፣ ልማትን፣ ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን፣ እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚታገል ተራማጅ ድርጅት እንደ መሆኑ መጠን አባሉና አመራሩም የዚህ ተራማጅ ድርጅት አመራርና አባል በመሆናቸው የድርጅቱን ዓላማ፣ መርሆዎችና እሴቶችን ማዕከል አድርገው ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡ በባለፈው ጉባኤያችን የመደመር እሳቤና የለውጡ እሳቤዎች መርሆዎች በግልፅ የተቀመጡ በመሆናቸው መላው የድርጅታችን አባላት እነዚህን መርሆዎች ከዋናው መርህ ጋር አስተሳስረው በመታገል የሀገራችንን መፃኢ እድል ብሩህ የማድረግ የተለመደ ሀላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

*አውደ ለውጥ፡- የተከበሩ ጓድ መለሰ ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ለዝግጅት ክፍላችን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ስለሰጡን በአንባቢያን ስም እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፡፡*

*ጓድ መለሰ፡-* እናንተም እድሉን ስለሰጣችሁኝና ለቃለመጠይቁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

# ለጥያቄዎች የተሟላ መልስ የሰጡን አንባቢያን ስም ዝርዝር እነሆ

1. የምስራች ወልደ ገብርዔል
2. ልጅ ያሬድ
3. ዳንኤል ፀሃይ
4. ጌታሰጠኝ ዳዲ
5. ለገሰ ኦላና
6. ኢርኮ አለሙ
7. ክብሮም አለሙ
8. ሜቲ በቀለ
9. ዮዲት ሃይለገብርዔል

## ሲሆኑ የጥያቄዎቹ መልስም የሚከተለው ነው፡፡

- የማስላት ጥበብ መልሱ 20,10,30,40 ነው የተሸጠው
- የአንገት ልብስ ደግሞ ሻርፕ C ነው
- በየራሳቸው የተጠላለፉት ገመዶች ገመድ 3 እና 4 ሲሆኑ በየራሳቸው ያልተጠላለፉት ደግሞ ገመድ 1 እና 2 ናቸው፡፡


1
ብልቃጥ፣ቁርቁር ጠርሙስ ያለው...
2
ና እስኪ... ዲንጓይን ስንት ትገዛለህ?
3
እ..እ...እኔ መርዛማ ነገር መያዣ አልገዛም አያቀጣም...
4
ምን አለከኝ?!
5
የሚወገድና የሚነገድ አያውቁም፣ እሜቴ?
ንቀት
ፀረ አንድነት
ፀረ ማንነት
ጥላቻ

# ስተጠና ችግር መፍትሄ የፀና አገልጋይ!

## መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የለውጥ አመራር ዓይነተኛ መለያው ያደረገው በከረሙ፣ በአደሩም ሆነ በተፈጠሩ ችግሮች ላይ ታይቶ በማይታወቅ ቁርጠኝነት ወስኖ ለመፍትሄ መትጋትን ነው፤ ከቁጥቁጥ አጀንዳዎች ይልቅ ደንዳና ፕሮጀክቶች ላይ ማተኮርንም ነው።

በአስተዳደሩ መላ መዋቅር ውስጥ የሚገኘው የለውጥ አመራር እንደ ከነዳው እንዳይለካ፣ እንደመተረው እንዳይቆርጥ፣ እንደ አረማመዱ እንዳይፈጥን ከሚገዳደሩት ችግሮች አንዱ መልካም አስተዳደር የማስፈን ጉዳይ ነው። በቀጥታ ሲገለፅ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታይ ችግር ነው። ስለዚህ ከተለመደው እብስ ድብስ የማስታገስ አቅጣጫ ይልቅ በመሰረታዊነት ትርጉም ባለው መንገድ ለመፍታት ችግሩ በምሁራን ተጠንቶ እስከነ መፍትሄው እንዲቀርብ አድርጓል። የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ትልቅ ምሁራዊ ሃይል አሰማርቶ የተጠና ችግርና የተጠና መፍትሄ አቅርቧል። የዝግጅት ክፍላችንም የጥናቱን ግኝትና መፍትሄዎቹን ለውይይት በሚያመች መልኩ እንደሚከተለው አቅርቧል።

ከተሜነት እየተስፋፋ በመምጣቱ ምክንያት በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ትልልቅ ከተሞችና ከተማ ቀመስ አካባቢዎች በብዛት በመፈጠር ላይ ይገኛሉ። አብዛኞቹ ትልልቅ ከተሞች ደግሞ በጊዜ ሂደት በዙሪያቸው ከሚገኙ አሰፋፈሮች ጋር ጥብቅ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ቁርኝትና ትስስር በመፍጠር የጋራ ፍላጎት ያለው አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመፍጠር ሜትሮፖሊታን ማንነት ተላብሰዋል። በዚህ ሂደት የሚፈጠረው ኢኮኖሚያዊ ትስስርም ጥብቅ በመሆኑ አንደኛው ያለ ሌላኛው ስኬታማ ሊሆን አይችልም። ብዙውን ጊዜ የከተማ ዕድገት የአንድን አካባቢ ባህርይ ስለሚቀይር ሜትሮፖሊታን ከተሞች ብዙ አካባቢያዊ ራስ ገዝ ስልጣን (local government jurisdictions) ይኖራቸዋል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካም በተመሳሳይ ሁኔታ የከተሞች እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየፈጠነ መጥቷል። ፈጣን የከተማ እድገት በሚታይበትና የተቋማት መዋቅር ደካማ በሆነባቸው በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገራት ደግሞ በትክክል የሚሰሩ ሜትሮፖሊታን ከተሞች መኖር እጅግ በጣም ጠቃሚ መሆኑ አያጠያይቅም።

በአንድ ከተማ ውስጥ በተለያዩ የመንግስት አካላት እና በዜጎች መካከል ባለው ግንኙነት የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን፤ ማቀላጠፍ እና ተደራሽ ማድረግ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ባለፉት አሥርት ዓመታት ዜጎች ደንበኞች መሆናቸውን መገንዘብ ለመንግስት አሰራሮች እና ድርጊቶች መሻሻል በከፍተኛ ሁኔታ ጠቃሚ እየሆነ መጥቷል። ደንበኞች ፍላጎታቸውን በሚያሟሉ አቅራቢያዎች አገልግሎቶችን ከሚመለከታቸው አገልግሎት ሰጭዎች የመጠየቅና ፈጣን፣ ተደራሽ፣ ጥራት እና ዝቅተኛ ወጪን ያማከለ አገልግሎት በተገቢው መንገድ የማግኘት መብት አላቸው። መንግስትም ይህንን የህዝብ አገልግሎት አንዳንድ ጊዜ ራሱን ችሎ አልያም ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር የመስጠት መሠረታዊ ሃላፊነት አለበት። ይህም በተለይ መንግስት ቁልፍ ሕዝባዊ አገልግሎቶችን የሚሰጥ እንደመሆኑ መጠን

ከደንበኞቹ ጋር ያለውን ግንኙነት በእጥፍ ከፍ ያደርገዋል፡፡

ጥራት ያለው እና ተመጣጣኝ አገልግሎት አሰጣጥ ደግሞ ለወደፊቱ ተገልጋዮች በመንግስት ላይ ያላቸው እይታ ጥሩ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በዚህም አገልግሎት አሰጣጡ ያልተቆራረጠና በመንግስት እና በዜጎች መካከል የግንኙነት አካል ተደርጎ መወሰድና የዘርፉን አሰራር ለማዘመንና ጊዜው ከሚጠብቀው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማስኬድም መንግስት ተጨማሪ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልገው ግልፅ ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከመቼውም ጊዜ በላይ የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራራቸውን ከጊዜው ጋር ማዘመን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በከተማ መስተዳድሩ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሚከሰቱ ክፍተቶችና አለመጣጣም ምክንያት ተገልጋዩ ቅሬታና አቤቱታ እንዲያቀርብ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ማህበረሰቡ የተለያዩ የመድልዎ ዓይነቶች እና ድክመቶች ስለሚገጥሙት በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ፍትሃዊነት እና እኩልነት መኖሩን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት የሚያስችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት አገልግሎቶች በተቀላጠፈ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መሰጠታቸውን ማረጋገጥ የበለጠ አስፈላጊ ነው፡፡

በእነዚህ እና ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች የተነሳ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 21/2/ሸ መሰረት ከንቲባው የህዝቡን ቅሬታና አቤቱታ ተቀብሎ የመፍታት ግዴታ የተጣለበት በመሆኑ ይህንኑ ኃላፊነት ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ከተማ አስተዳደሩ (ደንብ ቁጥር 78/2008) አውጥቶ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ የደንቡ ዓላማ አንቀጽ አምስት ላይ በሚከተለው መልኩ ሰፍሯል፡፡

፩. በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና ለሚያጋጥሙ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት፣ ስህተቶችን ለማረምና አገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ ማድረግ፣

፪. በየደረጃው ያሉ የመስሪያ ቤት ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ለህብረተሰቡ በሚሰጡት አገልግሎት አስተዳደራዊ ጥፋቶችና በደሎች እንዳይፈፀሙ መከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት፣

፫. በሥነ-ምግባር የታነፀ የመስሪያ ቤት ኃላፊ እና ሠራተኛ በማፍራት ውጤታማ ሥራ እንዲኖር የማስቻል ዓላማዎች ይኖሩታል በማለት ይደነግጋል፡፡

ደንቡ በመግቢያው ላይ በግልጽ እንዳመለከተው ከንቲባው በመልካም አስተዳደር ችግር ምክንያት እየመጡ ያሉትን ቅሬታዎችን ያስተናግድ ቢባል ለከተማው ስትራቴጂክ አመራር ከመስጠት ይልቅ የዕለት ተዕለት ቅሬታዎችን በማስተናገድ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር ስለሚያስገድድ፣ ከንቲባውን በማገዝ የህዝቡን ቅሬታዎችን በመፍታትና የቅሬታ መንስኤዎችን እያጠና መፍትሔ በመስጠት በከተማው ለመልካም አስተዳደር መስፈን ጠንካራ ሚና ሊያበረክት የሚችል ጽ/ቤት ተቋቁሟል፡፡ ጽ/ቤቱ ስራ ከጀመረ ቀላል የማይባሉ ጊዜያትን ያሳለፈ ሲሆን የተሰጠውን ኃላፊነት በመከወን ረገድ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ በኩል ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ ነዋሪዎች በመሰረታዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸውን ሚና ማስገንዘብና ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትብብር ሊሰሩ የሚችሉበትን ግልፅ የአሰራር ዘዴ መፍጠር አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ሲቪል ማኅበረሰቦች እና ዜጎች የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ ደግሞ በከተማው አገልግሎት አሰጣጥና የተጠያቂነት አሰራሮች ውስጥ ለምን እና እንዴት መሳተፍ እንዳለባቸው ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት የት እንደደረሰ

እና የዜጐች ፍላጎቶችን ለማሟላት በዜጎች ላይ ያተኮሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ለውጦች ላይ ክትትል በማድረግ በዜጎች ላይ የተሻለ ስኬት እንዲፈጥሩ እና በአጠቃላይ የዜጎችን ደህንነት ለማሻሻል የሚረዱ ውጤቶችን በአስተሳሰብ መለወጥ ነው፡፡

ደንበኞች/ዜጎች የሚፈልጉትን አገልግሎት ለማግኘት ወረፋ በመጠበቅ የሚያባክኑት ጊዜ በሰዓት አጠቃቀም ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ ምን እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡ በአገልግሎት አሰጣጡ ድክመት የተነሳ በሚመጣ የዜጎች እርካታ ማጣትና ወዳልተፈለገ ቅሬታና አቤቱታ መሄድ ይህንንም ቅሬታና አቤቱታ ተቀብሎ መፍትሔ ለመስጠት በሚደረገው ሂደት የሚባክን ሀብት እና ጊዜ የአገሪቱንም ሆነ የከተማዋን ኢኮኖሚ በእጅጉ እንደሚጎዳ ግልፅ ነው፡፡ ውጤታማ የቅሬታና አቤቱታ መቆጣጠሪያና አሰራር በመዘርጋት መልካም አስተዳደር የማስፈኑ ጉዳይ ጊዜ ሊሰጠው ወይም ችላ ሊባል አይገባም፡፡ ቅሬታዎች ከማህበረሰቡ ግብረመልስ ለማግኘት እና የአገልግሎትና የፖሊሲ መሻሻል ፍላጎትን ለመለየት እጅግ በጣም ጠቃሚ አጋጣሚዎች በመሆናቸው በሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚነሱ አቤቱታዎች ተመሳሳይ የሆነ አዎንታዊ አመለካከት ሊኖር ይገባል፡፡

ለተግባራዊነቱም ሰፊ፤ ጥልቅ እና በተግባር ያሉ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ተገቢውን የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ጥናት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በዚህም መሰረት  የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለቅሬታና አቤቱታ ምንጭ የሆኑ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያሉ ተግዳሮቶችንና ፈተናዎቹን ማጥናትና በጥናቱ መሰረትም የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ ነው፡፡

በሁሉም መንግስታት ውስጥ ከሚታዩ በርካታ ችግሮች መካከል አንዱና ዋነኛው በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ እና በህዝብ ፍላጎት መካከል ያለው አለመጣጣም ነው፡፡ እንደ ግል ዘርፍ ሁሉ የደንበኞች እርካታን ማሟላት የመንግስት አገልግሎት የአፈፃፀም ብቃት መለኪያ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል:: ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት በመንግስት ተቋማት እና ዜጎች መካከል ባለው ግንኙነት ቁልፍ ተግባር በመሆኑ መንግስታት ባለፉት ዓመታት ዜጎች የመንግስት አገልግሎት ደንበኞች መሆናቸውን በመገንዘብ አሰራሮችንና አገልግሎቶችን ለዜጎች በሚጠቅም መልኩ እያደራጁ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሀገራት ላይ መንግስት ዜጎች በሚፈልጉት ልክ አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ ህዝቡ በተለያየ ዘዴ ቅሬታውን ሲገልፅ ይስተዋላል፡፡

ለመንግስት ተቋማት መፈጠር ዋናው ምክንያት አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ ዜጎች ደግሞ በርካታ አገልግሎቶችን ከመንግስት የሚጠብቁ ሲሆን በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን (ማለትም ድህነት፣ ስራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነት፣ ወንጀሎች፣ ኢ-ፍትሃዊነት፣ የሀብት ብክነት ወዘተ) መቅረፍ የሚቻለው በቀልጣፋና ብቁ የአገልግሎት አሠጣጥ ዘዴ ነው፡፡ ዜጎች በሚጠብቁት ልክና ወቅት አገልግሎት ካላገኙ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ስለሆነም ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ለመዘርጋት በመጀመሪያ ተገልጋይ ህብረተሰቡ ባለው የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴ ላይ ያለውን ቅሬታና የቅሬታ መንስዔ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ከፐብሊክ አገልግሎት አሠጣጥና ቅሬታ ጋር ተያይዞ በቂ ጥናቶች በሀገራችንም ሆነ ውጪ ባሉት ሀገራት አልተደረጉም፡፡

ከላይ የተገለፁትን ነባራዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁኔታ ሲታይ በከተማ አስተዳደሩ ህዝባዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ላይ በበቂ ሁኔታ የተደራጀ ጥናት አልተደረገም፡፡ ሆኖም ህብረተሰቡ ያሉበትን የአገልግሎት አሠጣጥ ክፍተቶች በተለያየ ዘዴ ለመንግስት ሲያሳውቅ ይታያል፡፡ በ2011 ዓ.ም የቦሌ ክፍለ ከተማ

ባደረገው ጥናት ላይ እንደታየው የአገልግሎት አሰጣጡ ላይ በርካታ ክፍተቶች ያሉት ሲሆን በአገልግሎት ወቅት ቀጠሮ ማብዛት፤ ደንበኞችን ማመላለስ፤ የስራ ሰዓት አለማክበር፤ ፍጥነት ማነስ፤ ብልሹ አሰራሮችና የባለሙያ የክህሎት ክፍተት የህብረተሰቡ የቅሬታ ምንጭ ሆነው ተገልፀዋል፡፡ ሆኖም ጥናቱ በአንድ ክፍለ ከተማ ስር ባለ አንድ የአገልግሎት ዘርፍ (የመሬት ማኔጅመንት ጽ/ቤት) ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ የሌሎች ዘርፎችን ክፍተት ለማወቅ የሚያስችል አይደለም፡፡

ይህንኑ ራዕይ ለማሳካት የአዲስ አበባ ከተማን አጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጥና የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን በአግባቡ የሚያሳይና የሚገልፅ ጥናት አስፈላጊ ነው፡፡

## *የጥናቱ ግኝት (በማጠቃለያነት የተቀመጠ)*

በአብዛኞቹ ተገልጋዮች እይታ የተቋማት የአገልግሎት አሠጣጥ ሁኔታ በመካከለኛ ደረጃ የተቀመጠ ሲሆን በሠራተኞች እይታ ደግሞ የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ በጥሩ ደረጃ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የሰራተኞችን እና የተገልጋዮችን እይታ በክፍለ ከተሞችና በአገልግሎት ተቋማት ተለይቶ የታየ ሲሆን በተገልጋዮች እይታ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ያለው የአገልግሎት አሠጣጥ ሁኔታ በተመሳሳይ በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳ የሁሉም ክፍለ ከተሞች አገልግሎት አሰጣጥ በመካከለኛ ደረጃ የሚገለፅ ቢሆንም በመሀከላቸው ግን ልዩነት አለ፡፡ የአገልግሎት አሰጣጡን ሂደት በተቋማት ስንመለከት በተገልጋዮች በኩል ሁሉም የአገልግሎት ተቋማት መካከለኛ ደረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ በአማካይ ውጤት ሲታይ በመካከለኛ ደረጃ ያለ ሲሆን ከተገልጋዮች በተሰበሰበው ውጤት (Kruskal-Wallis Test ውጤት) መረዳት የተቻለው ምንም እንኳን ሁሉም ተቋማት በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙ ቢሆንም በመሀከላቸው ግን ልዩነት መኖሩን ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማየት ጥናቱ ታዋቂውን ሰርቭ-ኩዋል (SERVQUAL) ሞዴልን የተጠቀመ ሲሆን ከአምስቱ ዋና ዋና የአገልግሎት ጥራት መለኪዎች አንፃር ሲታይ የአዲስ አበባ ከተማ አገልግሎት ጥራት አነስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት መለኪያዎች መካከል በPearson Correlation መሰረት ትርጉም ያለው ዝምድና መኖሩን እንታዘባለን፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአገልግሎት ጥራት መለኪዎች ተዛማጅና አንደኛው ለሌላኛው አዎንታዊ አስተዋፆ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

በአዲስ አባበ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ተቋማዊ ሁኔታን በተመለከተ አጠቃላይ የከተማ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ አማካይ ነጥቡ (በሁሉም አገልግሎቶች እና ክፍለ ከተሞች) 3 ነጥብ 09 ከ 5 ወይም 15 ነጥብ 47 ከ 25 ነው፡፡ ይህም ማለት ከአጠቃላዩ ነጥብ ከ 50% በላይ ወይም ከአማካይ ነጥቡ ከፍ ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ጥቅል መረጃ የሚያሳየውም ክፍለ ከተሞች በሚሰጧቸው መሰረታዊ የከተማ የህዝብ አገልግሎቶች ላይ መካከለኛ የሆነ በራሳቸው የመወሰን ስልጣን እንዳላቸው ያሳያል፡፡ የዝምድና ማትሪክሱ (correlation matrix) ሲታይ በህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተቋማዊ አፈፃፀም መመዘኛዎች መካከል ያለው ዝምድና ወይም ግንኙነት (Correlations) ከፍተኛ ወይም ትርጉም ያለው ነው፡፡ የቅሬታ ምንጮችን ተዘማጅነትን በተመለከተ በሁሉም መንስዔዎች መካከል በPearson Correlation መሰረት ትርጉም ያለው ዝምድና መኖሩ ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የቅሬታ ምንጮች ተዛማጅና አንደኛው ለሌለኛው አዎንታዊ አስተዋፆ እንዳለው ያሳያል፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ከአጠቃላይ ተገልጋዮች ውስጥ 32 ነጥብ 2 ፐርሰንት ያህሉ

ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን፣ ግማሾቹ ቅሬታቸውን በቃል ሌሎች ደግሞ በፅሁፍ እና በተዘጋጀ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ሞልተው አሳውቀዋል። 56 ነጥብ 2 ፐርሰንት የሚሆኑ ተገልጋዮች ቅሬታቸውን ለሚመለከተው ሀላፊ አቅርበዋል። የተገልጋዮቹ ቅሬታ መንስዔዎች ሆነው የተገኙት በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡- የሀላፊ ቶሎ ውሳኔ አለመስጠት፤ ሙስና፤ የመመሪያና ህግ ክፍተት፤ ባለሙያዎች መመሪያዎችን ተከትለው አለመስራት፤ የስራ መጓተት፤ የባለሙያዎች የባህሪ ችግር እንዲሁም የሙያና ሙያተኛ አለመገናኘት። ተገልጋዮች ያቀረቡትን ቅሬታ ለመፍታት ረጅም ጊዜ ወስዷል። 22 ነጥብ 8 ፐርሰንት የሚሆኑ ተገልጋዮች በቅሬታ አፈታት ሂደት ደስተኛ  አልነበሩም። ተገልጋዮች ስለ ቅሬታ አፈታት ሂደቱ ያቀረቡት ምላሽ በክፍለ ከተሞችና በአገልግሎት ዘርፍ ተቀራራቢነት አለው።

በዚህ ጥናት የቀረበው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተቋማዊ የመፈፀም ብቃት ትንታኔ የሚያመለክተው በከተማዋ ባሉ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል አንፃራዊ የአገልግሎት አሰጣጥ አደረጃጀት ልዩነት ያለ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ በትንሹም ቢሆን በአገልግሎት ዓይነቱ ባህርይ የሚወሰን ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይ በውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ላይ ያለው ከሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተለየና የተማከለ ተቋማዊ የአደረጃጀት ሁኔታ መመልከት ተችሏል።

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንታኔ ግኝት እንደሚያሳየው በየክፍለ ከተሞች በሚገኙት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተመዘገበው አማካይ ነጥብ፣ ከሞላ ጎደል መካከለኛ የሆነ ስልጣንና ውሳኔ የመስጠት ነፃነት ያላቸው መሆኑን ያመላክታል። እነዚህ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት የተሰጣቸው ቢሆንም ትርጉም ያለው የአስተዳደር እና አመራር እንዲሁም በገንዘብ ላይ የመወሰን ስልጣን ያላቸው ባለመሆናቸው በከተማዋ የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው እሙን ነው።

በአይነታዊ የመረጃ ትንተና ዘዴ የጥናት ቡድኑ የተተኳሪ የቡድን ውይይትን እና ቃለ-መጠይቅን የተጠቀመ ሲሆን ለቅሬታ መነሻ በሆኑ ምክንያቶች ላይ ዝርዝር ያለ ምላሽ ሰጥቷል። በአይነታዊ የመረጃ ትንተና ዘዴ ከቀረቡት የቅሬታ ምንጮች መካከል ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተሉት ቀርበዋል። እነዚህም ከመመሪያዎች/ህጎች እና ደንቦኞች፤ ከመሰረተ ልማት እና ግብአት አቅርቦት፤ ከአመራሮች ጋር የተያያዙ ምክንያቶች፣ ከሰራተኞች ወይንም ፈፃሚዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ ሙስና እና መዋቅራዊ ችግሮች በሚል አስቀምጧቸዋል።

በህጎች፤ ደንቦችና መመሪያዎች ዙሪያ ክፍተቶች በመኖራቸው ሃላፊዎችና ሰራተኞች ክፍተቶቹን በመጠቀም ሙስና፤ አድሎአዊ አሰራር፤ ከበላይ አካላት ደግሞ ሰርኩላሮችን በመፃፍና ህግን በመጣስ አላግባብ ግለሰቦችን እና ራሳቸውን እንዲጠቅሙ ማደረጉንና በዚሁ ምክንያት ተገልጋዩ ህብረተሰብ ተመሳሳይ አገልግሎት እንዳያገኝ በማድረግ የቅሬታና አቤቱታ ምንጭ ሆነዋል።

በአገልግሎት ተቋማት መሰረተ ልማቶች በበቂ ሁኔታ ባለመሟላታቸው ለህብረተሰቡ ቶሎ ምላሽ ላለመስጠት፤ ለሥራ መጓተት፤ ለቀጠሮ መብዛት፤ እንዲሁም ለፋይሎች መጥፋት ምክንያት በመሆናቸው፣ ህብረተሰቡ አገልግሎቱን በአግባቡ እንዳያገኝ በማድረጋቸው የቅሬታና አቤቱታ ምንጭ ለመሆን ችለዋል፤

የአመራርና ሰራተኞች ምደባ ብቃትን መመዘኛ አለማድረጉ ኃላፊዎቹና ሰራተኞቹ በራሳቸው ተማምነው ለሥራዎች ኃላፊነትን እንዳይወስዱ፤ ቶሎ ውሳኔ እንዳይሰጡ፤ እርምጃዎችን እንዳይወስዱ አድርጓቸዋል። በሠራተኞች መካካል ልዩነት እንዲፈጠር በማድረግ ለህብረተሰቡ ቅሬታና አቤቱታ መብዛት መንስኤ ሆነዋል።

አመራሮች የመወሰን ችግር እንደሚታይባቸው ሰራተኞች እና ተገልጋዮች ገልፀዋል፤ ሃላፊነትን ወደሌሎች መግፋት የተለመደ አሰራር እንደሆነ ከቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት የተገኘው መረጃ ያሳያል። ይህም ዋና የቅሬታ ምክንያት ለመሆን ችሏል።

በጥናቱ ላይ እንደተሳተፉ ሰዎች ምላሽ ከሆነ አመራሩ ውሳኔ የመስጠት አቅም ማነስ ብቻ ሳይሆን በሚፈጠሩ ጥፋቶች ላይ እርምጃ የመወሰድ አቅም እንደጎደለውም ተገልጿል። አመራሩ ጥፋት ሲፈፅም  በዝምታ መታለፉ፣ የተጠያቂነት ሥርዓት መላላት፣ እንዲሁም በሥርዓት ላይ የተጠያቂ አካላት የእርስ በርስ ትስስር ለተከሰቱ እና ለሚከሰቱ ችግሮች ዋና ምክንያት ናቸው። አመራሮች እርምጃ የማይወስዱበት ምክንያት በሚፈጠረው ትስስር ወይም ኔትወርክ ምክንያት እንደሆነ ተገልጧል፤ አመራሮች ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ በተለያየ ጥቅማ-ጥቅም ስለተሳሰሩ ሊነካኩ እንደማይችሉ ተጠቅሷል። አመራሩ ባጠፋው ጥፋት መጠየቅ ሲገባው፤ ያጠፋ አመራር በህግ ከመጠየቅ ይልቅ ወደ ተሻለ ቦታ የሚሾምበት የሚዘዋወርበት ሁኔታ እንዳለ ተጠቅሷል፤ ይህም በተገልጋዩ ላይ ቅሬታን ፈጥሯል።

መሬትን በተመለከተ በርካታ ችግሮች ተነስተዋል። ከካሣ ጋር ተያይዞ፣ ከልማት ተነሺዎች ጋር ተያይዞ፤ በፕላን ተቃርኖ ያለባቸው ባለይዞታዎች ተያይዞ ለሚነሱ ጥያቄዎች በሚጣረሱ ህጎች ምክንያት አመራሩ መፍታት እንዳልቻለ እና በአፈጻጸም ደረጃ ይሄ እንደማይፈፀም፤ በተቀመጠው ደረጃ እንደማይሰራ የጥናቱ ተሳታፊዎች ይገልፃሉ። እንዲሁም የቤት ችግር ለቅሬታ ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል በዋናነት የሚጠቀስ ነው። በተለይ መሀል ላይ በሚገኙ ክፍለ-ከተሞች ላይ የልማት ተነሽዎች (የምትክ ቤት ይሰጠኝ ጥያቄ)፣ የማካካሻ ቤት ጥያቄ እና ካርታ ይሰራልኝ የሚሉ ቅሬታዎች በብዛት የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው።ይህንን መሰረታዊ ችግር ለመፍታትም በቦታው ላይ ያለው አስፈፃሚ አካል የሚፈፅማቸው ብልሹ  አሰራሮች ጉዳዩ እንዲወሳሰብ አድርገውታል።

የአመራሩ ብቃት ማነስ ችግር በተደጋጋሚ ከተነሱት ችግሮች መካከል አንዱ ነው። አመራሩ በአግባቡ የመሪነት ሚናውን እንደማይወጣ፣ ውሳኔ እንደማይሰጡ በርካታ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። የፖለቲካ ስርዓቱ የፖለቲካ ታማኝነትን እና የብሄር ተዋፅዖን መሰረት አድርጎ የስልጣን ምደባ ስለሚያካሂድ ብቃትን መሰረት ማድረግን የሚስትበትም ሁኔታ መኖሩም ተገልጿል። በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ላይ የሚገኙ ሀላፊዎች መሰረታዊ የአቅም ችግር እንዳለባቸውም የጥናቱ ተሳታፊዎች አስረድተዋል። አንዳንድ ቦታ ላይ የተመደቡ ሀላፊዎች እንኳን ትልቅ ቦታ ሊሰጣቸው ይቅርና ለምንም ነገር ሊወከሉ እንደማይችሉ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ለነዚህ  ሁሉ ችግሮች መከሰት ወይም ይህም ችግር በመንግስት ሲቪል-ሰርቪስ መዋቅር ላይ አሉታዊ ጫና እንደሚያስከትል ይታመናል። ቅጥር እየተፈፀመ ያለው በዝምድና በጓደኝነትና በብሔር እንደሆነ እና ይህም ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር እየዳረገን እንደሆነም የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል።

የህዝብ አገልግሎት በሚበዛባቸው ቢሮዎች ላይ አገልግሎት ሰጭ ባለሙያዎች የመሰላቸት ባህሪ ይታይባቸዋል:: ደካማውንና ጠንካራውን የሚለይ የአሰራር ዘዴ በሌለበት ሁኔታ ታታሪው እና ጠንካራው አገልጋይ  በሚሰራው ስራ ላይ መሰላቸትን ይፈጥራል። በተመሳሳይ የሰራተኞች የቅንነት ማጣት  የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለፁት የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ ተናግረዋል። አገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች ተገልጋዮችን በቅንነት እንደማያስተናግዱ ለመረዳት ተችሏል።

በሰራተኞች ላይ የሚታየው የታታሪነት ጉድለት ማነስ ወይም ቸልተኝነት እንደ ዋና ችግር ከተነሱት ምክንያቶች አንዱ ነው።ከጥናቱ ተሳታፊዎች ለመረዳት እንደተቻለው የአገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች የአገልጋይነት መንፈስ ስላልተላበሱ የስራ ትጋት በመካከላቸው እንደሌላቸው ለመረዳት ተችሏል።

አገልጋዮች የስራ ስዓታቸውን እንደማያከብሩ እና ይህ ደግሞ የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች ቢሯቸው እስኪገቡ ድረስ ተቀምጠው ብዙ ሰዓት መጠበቃቸው የቅሬታ ምክንያት ሁኗል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች ለስራ ወይንም ለሻይ ብለው ከቢሮ ከወጡ ቶሎ አይመለሱም፤ አንዳንዴ እንደወጡ በዛው ይቀራሉ፡፡ የሰራተኞች ብቃት ማነስም እንደ ችግር ከተነሱት ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡

አገልጋዮች የአድሎዓዊነት ባህሪ ወይም ስሜት እንደሚታይባቸው እና ይህም የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ የፖለቲካ ስርዓቱ በአብዛኛው ብሄርን መሰረት አድርጎ ነገሮችን ማከናወኑ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የብሄርተኝነትን ስሜት ፈጥሯል፡፡ ከአስተሳሰብ ልዩነቶች ውጭ የአገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች በባለ-ጉዳዮች መካከል የአድሎዓዊነት ስሜት እየታየባቸው እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ክስተት በየመንግስት መስሪያ ቤቶች መንፀባረቁ የሚታይ ክስተት ነው፡፡

አገልጋዮች የተጠያቂነት ባህሪ አለመላበሳቸው የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ ይህም ክስተት ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ይፈጥራል፡፡

በሰራተኞች ላይ የግብረ-ገብነት ችግር እንደሚታይ ጥናቱ የሚያመላክት ሲሆን ለዚህ ችግር ምክንያት በርካታ ሲሆኑ የትምህርት ስርዓቱ ውድቀት፣ የማህበራዊ ሚዲያዎች ልቅ መሆን፣ ቤተ-እምነቶች የባህሪ ለውጥ ላይ ትኩረት ሰጥተው አለመስራት፣ የማህበራዊ ቀውሶች መብዛት እና የመሳሰሉት ጉዳዮች እንደ-ምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ከአገልጋዮች ላይ የስራ ፍቅር እንደማይታይ እና ይህም የስራ ፍቅር መቀነስ የቅሬታ ምንጭ እነደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ የስራ ባህል መጥፋት የመልካም አስተዳደር እጦትን እና የብልሹ አስተዳደራዊ መዋቅርን ችግር የሚያንፀባርቁ ክስተቶች ናቸው፡፡ በሙስና በተበከለ ማህበረሰብ ውስጥ ስራን ሰርቶ መለወጥን እና ስራ-አክባሪነትን መጠበቅ አስቸጋሪ ነው፡፡

ከሰራተኞች የቅሬታ ምንጮች መካካል ለተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ እና ልምድ የተለያዩ ክፍያዎች መኖራቸው ሲሆን ይህ ቅሬታ በሚያገለግሉት ህዝብ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ የደመወዝ አከፋፈል መለያየት የቅሬታ ምክንያት እንደሆነ ተገልፆዓል፡፡ ይህም ክስተት የሠራተኛው የሥራ ተነሣሽነትን ይቀንሳል፤ የሚሰጡትንም አገልግሎት ጥራት በመቀነሱ ቅሬታንም ይፈጥራል፡፡

የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች፤ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰራተኞች፤ የስራ ሂደት መሪዎች እና አመራሮች እንደገለፁት ሙስና እና ብልሹ አሰራር በሰፊው የሚታይ ችግር እንደሆነ ነው፡፡ ሰራተኞችም ሆነ የአመራር አካላቱ ነገሮችን በትውውቅ፤ በጉቦ፤ በወዳጅ እና በዘመድ መሰራታቸው ህበረተሰቡን በእኩልነት ባለማገልገላቸው የተለያዩ ቅሬታዎች እንደሚነሱ ገልፀዋል፡፡ በእኩልነት አለማስተናገድ፣ አድልኦ መፈፀም፡፡ ተገልጋዮች በግልፅ ብር እንዲከፍሉ መጠየቃቸው የሚታዩ ችግሮች እንደሆኑ ይነሳሉ፡፡ በቀጠሮ ማመላለስ እና መረጃ ማጥፋት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡ ባለሙያው ተገልጋዩን ያልሆነ ነገር ወይንም መረጃ በመስጠት በማደናገር ገንዘብ እንዲከፍል ማድረጋቸው ከተጠቀሱት የቅሬታ መነሻ ምክንቶች ውስጥ ይካተታሉ፡፡

ሌላው ከህጎች፣ መመሪዎች እና ደንቦች ጋር ተያይዞ የሰርኩላሮች መብዛት፤ የወጡ ህጎች ተፈፃሚነት ችግር፤ የአሳታፊነት ችግር፤ የግልፀኝነት ችግር፤ የመመሪያዎች እርስ በርስ መጣረስ፤ የተለያዩ ፅ/ቤቶች ተናብበው የሚሰሩበት መመሪያ አለመኖር፤ መመሪያዎች አሻሚ እና ለድርድር የሚያመቹ መሆናቸው፤ ችግር ፈቺ ያልሆኑ ህጎች እና መመሪያዎች መኖር፤ እና

መመሪያዎች ከጊዜው ጋር ጊዜውን ጠብቀው አለመሻሻል ከተነሱት ህግ ነክ የቅሬታ መንስኤዎች ውስጥ ዋነኛዎች ናቸው፡፡

የመስሪያ አካባቢ ምቹ አለመሆን ማለትም የቢሮ መጣበብ፣ ለሰራተኛ ካፌ እና ሽንት ቤት የመሳሰሉት አገልግሎቶች አለመኖር፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታ አለመኖር፤ የቢሮዎች የፅዳት ሁኔታ ዝቅተኛ መሆን ህንፃዎች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለአገልግሎት አመቺ አለመሆናቸው (በተለይ የአካል ጉዳተኞችን እና አረጋዊያንን) የመብራት እና ኢንተርኔት መቆራረጥ፣ የግብዓት አቅርቦት እጥረት እንደ ወረቀት፤ ወንበር፤ ጠረጴዛ፤ መቀመጫ፤ ፕሪንተር፣ ኮፒ እና የሌሎች ቁሳቁስ እጥረት መኖር፣ የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት፣ የሰው ሃይል እጥረት፤ ያልተደራጀ የሰነድ አያያዝ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጅን አለመጠቀም ከመሰረተ ልማት እና ግብአት እጥረት ጋር በተያያዘ የተነሱ የቅሬታ መነሻ ምክንያቶች ናቸው፡፡

አመራሩ ስትራቴጂክ መሪ ከመሆን ይልቅ በተራ ስራዎች መጠመድ፣ የመስክ ስራ ላይ ማተኮር፣ ተደጋጋሚ ስብሰባ ማብዛት፣ የአመራሩ የእውቀት ማነስ እና የመፈፀም አቅም ዝቅተኛ መሆን የቅሬታ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ሰራተኞችን በተመለከተ ደግሞ የስራ ሰኣት አለማክበር፣ ማርፈድ፣ መቅረት፣ ከስራ ሰአት አቋርጦ መውጣት፣ ሰራተኞች ለደንበኞች ያላቸው አቀባበል ዝቅተኛ መሆን፣ የአገልጋይነት ስሜት እና ተነሳሽነት እየቀነሰ መምጣት፣ ተገልጋዮችን በቅንነት ትኩረት ሰጥቶ ለማገዝ አለመሞከር፣ እና ህጎችን፤ ደንቦችን እና መመሪዎችን አውቆ አለመስራት ዋና ዋና ለቅሬታ መነሻ ምክንቶች ናቸው፡፡

በተጨማሪም ከሰራተኞች፤ አመራሮች እና የስራ ሂደት መሪዎች ጋር በተደረገው ውይይት እና ቃለ መጠይቅ ከደንበኞች ጋር በተያያዘ ችግር እንዳለም ተመላክቷል፡፡ ለምሳሌ የግንዛቤ ማነስ፣ አላስፈላጊ ተጠቃሚነት፤ የስነ-ምግባር ችግሮች እና ለወረዳ ፅ/ቤት የተዛባ እይታ መኖሩ እንደ ምክንያት ተጠቅሰዋል፡፡

የደንበኞች የግንዛቤ ማነስ፣ ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋሙ ሲመጡ ባለማወቅ የሚያስፈለገውን ቅድመ ሁኔታ ሳያሟሉ መምጣት እና ላልተፈለገ ምልልስ መዳረግ፣ ህግን ባለማወቅ የተለያዩ ደንቦችን በመጣስ ለተለያዩ የሃብት ብክነቶች መዳረግ፣ በተለይ ከግንባታ ፈቃድ ጋር በተያያዘ፣ አላስፈላጊ ተጠቃሚነት ፍላጎት፡፡ ግለሰቦች ህጉን ወይንም መመሪያውን እያወቁት ነገር ግን በመከራከር፣ ተደጋጋሚ ክፍለ ከተማ እና ከተማ አስተዳደሩ ድረስ በመሄድ መፍትሄ ለማግኘት መሞከር፣ ትክክለኛ መልስ ተሰጥቷቸው ነገር ግን በሁሉም እርከን ቅሬታ ለማቅረብ መሄድ የተጠቃሚዎች ችግር እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ አንደኛው ፈፃሚ መልስ ሲሰጣቸው መመሪያውን በደንብ ባለማወቅ ወይንም በርህራሄ ይሰራልኛል ብሎ በማሰብ ትንሽ ቀን ቆይተው ሌላ ፈፃሚ ወይንም ሃላፊዎች ላይ መሄድ የተለመደ የተገልጋይ ችግር እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የተገልጋዮች የስነ-ምግባር ችግር ተገልጋዮች ሰራተኞችን መሳደብ፣ ፀያፍ ቃል መናገር፣ የበታች አድርጎ ማየት፣ እና ሌሎች አግባብ ያልሆኑ ባህሪዎችን የማሳየት ችግር በጥናቱ ላይ ታይቷል፡፡ አንዳንድ ባለሙዎች በመታገስ አገልግሎቱን ይሰጣሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ አፀፋ መልስ በመመለስ አምባጓሮ ሲፈጠር ደንበኛው ተሰደብኩ፣ አገልግሎቱን ከለከለኝ በማለት ለሃላፊዎች ቅሬታ የማቅረብ ሂደት ይታያል፡፡

## *የመፍትሄ ሃሳብ*

አጠቃላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በሰራተኞች እና በተገልጋዮች እይታ አገልግሎት አሰጣጡ ያለበት ሁኔታ መካከለኛ እና ከዛ በታች እንደሆነ

ተገልጿል። በተመሳሳይ ጥናቱ የሰርቭ-ኩዋል (SERVQUAL) ሞዴልን የተጠቀመ ሲሆን ከአምስቱ ዋና ዋና የአገልግሎት ጥራት መለኪዎች አንፃር ሲታይ የአዲስአበባ ከተማ አገልግሎት ጥራት አነስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ችግሩን በመሰረቱ ሊቀርፉ የሚችሉ መፍትሄዎችን መውሰድ እንደሚያስፈልግ ያሳያል።

ከህጎች፣ መመሪዎች እና ደንቦች ጋር በተያያዘ የሰርኩላሮች መብዛት፤ የወጡ ህጎች የተፈፃሚነት ችግር ማጣት፤ የአሳታፊነት ችግር፤ የግልፀኝነት ችግር፤ የመመሪዎች እርስ በእርስ መጣረስ፤ የተለያዩ ፅ/ቤቶች ተናብበው የሚሰሩበት መመሪያ አለመኖር፤ መመሪያዎች አሻሚ እና ለድርድር የሚያመቹ መሆናቸው፤ ችግር ፈቺ ያልሆኑ ህጎች እና መመሪዎች መኖር፤ እና መመሪዎች ጊዜውን ጠብቀው አለመሻሻል ከተነሱት ህግ ነክ የቅሬታ መንስኤዎች ውስጥ ዋነኛዎች ናቸው። በመሆኑም በዋናነት ሁሉም ህግ ነክ ችግሮች ሲጠቀለሉ አንደኛ ህጎች ሲወጡ አሳታፊ መሆን እንደሚገባቸው ያሳያል። ህጉ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ጊዜ ወስዶ አካታች የሆኑ ህጎችን ለማውጣት መሞከር። ሌላኛው ደግሞ ህጎች ሲረቀቁ በጥናት ላይ የተመሰረቱ እና ነባራዊ ሁኔታን በደንብ የሚያዩ እና ሊፈጠሩ የሚችሉ ነገሮችን አስቀድመው የሚተነትኑ ቢሆኑ የሚከሰቱ የህግ ክፍተቶች እና ቅሬታዎችን ለመቀነስ ያግዛል። በህጎች፤ ደንቦችና መመሪያዎች ዙሪያ የሚታዩ ክፍቶችን በከተማ አስተደዳር ደረጃ በአግባቡ በጥናት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ለይቶ ህጎቹን ደንቦቹንና መመሪያዎቹን ህብረተሰቡን ባሰተፈ መልኩ መከለስና ወቅታዊ ሁኔታውን በአገናዘበ መልኩ በማዘጋጀት ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

በመሰረተ ልማት አለመሟላት ምክንያት ህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እያገኘ ባለመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ፤ ክፍለ ከተሞችና ሴክተር መስሪያ ቤቶች በዚህ በኩል ያሉትን እጥረቶች ከጥቃቅን የቢሮ መገልገያዎች ጀምሮ እስከ አይሲቲ መሰረተ ልማቶች በየአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በማሟላት የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን ማዘመን ተገቢ ይሆናል።

በኃላፊዎችና በሠራተኞች አመዳዳብ ዙሪያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመፍታት የከተማ አስተዳደሩና ክፍለ ከተሞች በአግባቡ በተጠና ሁኔታ በመለየትና የአመዳደብ ስርዓት በመከለስ መፍትሄ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ይህም ማለት በክፍለ ከተሞችም ሆነ በወረዳዎች ያሉ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲጠናከሩና አንፃራዊ የመወሰን ነፃነት እንዲኖራቸው መስራት ህብረተሰቡ የሚያገኘውን አገልግሎት ለማሻሻል እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

የፖለቲካ ተሳትፎን መሰረት ያደረገ የአመራር ምደባን በሚመለከት ሰራተኞች እና የስራ ሂደት መሪዎች እንደገለፁት የአመራሩ ምደባ ሂደት ለአመራሩ የብቃት ማነስ እንደ ዋና መነሻ ምክንያት እየሆነ ስለሆን ለአመራሩ የግል አቅም እና ችሎታ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የሰራተኞች ምደባ ብቃትን መሰረት ያደረገ ምደባ እንዲካሄድ ማድረግ። በአመራር ምደባም ብቃትን መሠረት ማድረግ ከፖለቲካ ታማኝነትና ከብሄር ተዋፅዖ ባልተናነሰ መልኩ ትኩረት በመስጠት አቅምን ያገናዘበ ምደባ ማካሄድ።

አመራሮች ስህተት ሲፈፅሙ አንኳን መሸፋፈን እንጂ ተጠያቂነት እንደማይታይ ተገልጿል፤ ስለዚህ አመራሮች በተጠያቂነት መንገድ መስራት እንደሚገባቸው ግንዛቤ ማስጨበጥ።

የአመራሩ የእውቀት ማነስ እና የመፈፀም አቅም ዝቅተኛ መሆን፣ የአመራሩ የመፈፀም አቅም ማነስ ሃላፊነትን ወደሌሎች መግፋት የሚታዩ ችግሮች እንደሆኑ ተገልጿል። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ አመራሩ በእውቀት እና ችሎታ የመመደብ መስፈርት የማይጣስ በማድረግ መመደብ ይገባል።

መሬትን እና ቤትን በተመለከተ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በቦታው ላይ ያለው አስፈፃሚ

አካል የሚፈፅማቸው ብልሹ አሰራሮች ጉዳዩን እንዳያባብሱት መንግስት አስፈላጊ መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

አመራሩም ይሁን ሰራተኞች ባጠፉት ጥፋት መጠን ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት መዘርጋት፡፡ አገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች የቸልተኝነት እና የመሰላቸት ባህሪ እንደሚታይባቸው፣ የስራ ትጋታቸው አነስተኛ እንደሆን እና የስራ ሰዓታቸውን እንደማያከብሩ፣ የአድሎዓዊነት ባህሪ ወይም ስሜት እንደሚታይባቸው በጥናቱ ላይ ተገልጧል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ አገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች ተከታታይ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡

አገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች ዘንድ የሚንፀባረቅ የግብረ-ገብነት ችግር የተጠያቂነት ባህሪ አለመላበስ፣ የስራ ፍቅር መጓደል የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በመፍትሔነት ከተቀመጠው ተከታታይ ስልጠና ባሻገር የትምህርት ስርዓቱን ከግብረ-ገብነት አንፃር መቃኘት ነው፡፡

መዋቅራዊ አሰራሮች፤ የተጠያቂነት አሰራር ማነስ፤ የክትትል እና ቁጥጥር ስራዎች መጓደል፣ የአመራር በየጊዜው መቀያየር፤ በመስሪያ ቤቶች መካከል ተናብቦ አለመስራት፤ የሰራተኛ ደመወዝ መጠን የአከፋፈል ሁኔታ ፍትሃዊ አለመሆኑ ሰራተኞች ተከታታይ የሆነ ስልጠና እና የማብቂያ ስልጠና አለማግኘታቸው፤ ተደጋጋሚ የስብሰባዎች መብዛት፤ ወጥ የሆነ የአመራሮች እና ሰራተኞች ማበረታቻ እና ቀጣይነት ያለው ስልጠና አለመኖር፤ ችግሮችን በህግ እና በመመሪያ ከመመራት ይልቅ በተደጋጋሚ ስብሰባዎች እና በአስተዳደራዊ ውሳኔ የመፍታት አካሄድ ሌሎች መዋቅራዊ ችግሮች እንደሆኑ ተነስተዋል፡፡

በመሆኑም ተደጋጋሚ ስብሰባ በተመለከተ የሚጠፋውን ሰአት ለመቀነስ አንደኛ ህጎችን እና መመሪያዎችን በማጠናከር በህግ እና ደንቦችን ብቻ መሰረት በማድረግ ለመስራት መሞከር፤ አለፍ ሲል አንዳንዴ ወጣ ያሉ ችግሮች ሲፈጠሩ ስብሰባዎችን ከስራ ሰአት ውጭ ማድረግ፡፡

የውሳኔ ሰጭነት ማነስ እና ሃላፊነትን ወደ ሌሎች መግፋት በሚመለከት ሃላፊዎች ወይንም ፈፃሚዎች የመወሰን ብቃት እንዲያዳብሩ አንደኛ ምድባ ላይ ችሎታን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ ሁለተኛ የእውቀት ክፍተትን በተደጋጋሚ ስልጠና ማጎልበት፡፡

ለሰራተኞች ተከታታይ የሆነ የስልጠና እና የማብቃት ስራ ለመስራት መዋቅራዊ በሆነ መልኩ ባለሙያውን በየጊዜው አቅሙን ለማዳበር ወይንም የማጎልበት ስራ መሰራት አለበት፡፡ ዲግሪ፤ ዲፕሎማ ወይንም ቴክኒክ እና ሙያ ሰልጣኞችን ከመቅጠር በተጨማሪ የተቋሙን ባህሪ ሊረዳ የሚችል እንዲሆን ሰራተኛውን በየጊዜው የማብቃት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት ቢሰራ፡፡ ከአዲስ ገቢ ሰራተኛ ጀምሮ ስለ ቢሮው ጽ/ቤቱ ምንነት እና ሌሎችን በተመለከተ በቂ ቅድመ ስልጠና መስጠት፡፡ ስራ ላይ እያለም ቢሆን ቋሚ በጀት ተይዞለት በየጊዜው አቅምን የማጎልበት ስራ መስራት፡፡

የሰራተኛ ደመወዝ ማነስ እና ፍትሃዊ ያልሆነ የአከፋፈል ስርአት፣ ሰራተኛ በቢሮአቸው ተገኝተው መደበኛ ስራቸውን በጥራት እና በትጋት የመስራት ተነሳሽነታቸውን ስለሚሰልብ ሊመረመር ይገባል፤ በተጨማሪም በተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ በተመሳሳይ ወረዳ በተለያዩ ቢሮዎች የተለያየ ደመዎዝ አከፋፈል ስርዓት መኖሩ፤ እና ስራ ጫና ያለበት ሴክተር ላይ የሚከፈለው ደመወዝ አነስተኛ መሆን የሰራተኛውን ተነሳሽነት እንደሚቀንስ ብሎም በአፈፃፀሙ ላይ ተፅእኖ እንዳለው ሰራተኞች ያነሳሉ፡፡ በመሆኑም ወጥ የሆነ የቢሮዎችን የስራ ሁኔታን እና የትምህርት ደረጃን መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ስርአት በመዘርጋት ችግሩን ለመቅረፍ አስተዋፅኦ እንዲኖር ማድረግ፡፡

ግንኙነት ባላቸው መስሪያ ቤቶች መካከል በቅንጅት ተናብቦ በጋራ ያለመስራት ችግር መኖር

በህብረተሰቡ ዘንድ ለቅሬታ ምንጭ የሆነ ሌላው መንስኤ እንደሆነ ሰራተኞች እና ተገልጋዮች ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ ወደ ጎንም ይሁን ወደ ላይ እና ወደ ታች ተቋማት አብረው የሚሰሩበት አሰራር እና መመሪያ ተዘጋጅቶ አብሮ/በትብብር እንዲሰሩ ቢደረግ፡፡

ሰራተኞች እንደገለፁት የአመራሮች በየጊዜው መቀያየር ሌላው ችግር እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ አመራር የተመደበበትን ፅ/ቤት በደንብ ሳይለምደው እና ገና መስራት ሳይጀምር ወደ ሌላ ቦታ መቀየር ተረጋግቶ እንዳይሰራ እና ተጨባጭ የሚመዘን ለውጥ  እንዳያመጣ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ስራውን አተኩሮ እንዲሰራ እና በሚሰራበትም ውጤታማ እንዲሆን፣ ህብረተሰቡን እና አካባቢውን ተረድቶ ከህብረተሰቡ ጋር ተቀራርቦ በእቅድ እንዲሰራ አመራሩን በጥናት መመደብ እና በተመደበበት ቦታ የአቀዳቸውን ስራዎች እንዲፈፅም ማድረግ ችግሮችን ለመፍታት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

የሚለኩ እና የሚጨበጡ መለኪያዎችን ወጥ በሆነ መልኩ በማዘጋጀት ሽልማቶች እና ሌሎች ማበረታቻዎችን ማዘጋጀት ቢቻል ሰራተኞችን እና አመራሮችን በቀላሉ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል፡፡ የአመራሮች እና ሰራተኞች ወጥ እና ቀጣይነት ያለው ማበረታቻ እና ስልጠና ቢሰጥ፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት ጥሩ ውጤታማ የሆኑ ሰራተኞች፣ አመራሮች እና የስራ ሂደት መሪዎች አልፎ አልፎ ባልተደራጀ መልኩ እውቅና ከመስጠት ባለፈ በተናጥል መልክ ህግ ወጥቶለት በየተቋሙ የማበረታቻ ስራ እየተሰራ ስላልሆነ መንግስት ሰራተኞችን ለማበረታታት ይህንን መስራት ቢችል፡፡

የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች፤ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰራተኞች፤ የስራ ሂደት መሪዎች እና አመራሮች እንደገለፁት ሰራተኞችም ሆኑ አመራሮች ነገሮችን በትውውቅ፤ በጉቦ፤ በወዳጅ እና በዘመድ መስራታቸው ህብረተሰቡን በእኩልነት ባለማገልገላቸው ለተለያዩ ቅሬታዎች እንደዳረጓቸው ገልፀዋል፡፡ በእኩልነት አለማስተናገድ፣ አድልኦ መፈፀም፡ ተገልጋዮች በግልፅ ብር እንዲከፍሉ መጠየቅ የሚታዩ ችግሮች እንደሆኑ ያነሳሉ፡፡ በቀጠሮ ማመላለስ እና መረጃ ማጥፋት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ መስተዳድሩ  በሙስና ላይ እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል፡፡ በመሆኑም መንግስት ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በመስራት ተጠያቂነትን ማጠናከር እና ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ መፍጠር አለበት፡፡ አመራሮች እና ሰራተኞች ሙስናን ፈፅመው ሲገኙ እርምጃ መውሰድ ለሙስና የሚዳርጉ ህጎችን እና አሰራሮችን መዝጋት፡፡ ስለዚህ መንግስት አጠቃላይ መዋቅሩን ከላይ እስከ ታች ድረስ መፈተሽ እና ተጠያቂነትን ማስፈን አለበት፡፡

የመስሪያ አካባቢ ምቹ አለመሆን ማለትም የቢሮው መጣበብ፣ ለሰራተኛ ካፌ እና ሽንት ቤት አለመኖር፣ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታ አለመኖር ለደንበኞችም ለሰራተኞችም የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ ተነስቷል፡፡ በመሆኑም፤ የሰው ሃይሉን ብዛት መሰረት ያደረገ የቢሮዎች ማስፋፊያ ማድረግ፡፡ ቢሮዎች ሲገነቡም ሽንት ቤት እና መዝናኛዎችን ለሰራኞችም ይሁን ለደንበኞች አገልግሎቶችን መስጠትን ያካተቱ ማድረግ፡፡ የቢሮዎች የፅዳት ሁኔታ በተመለከተ በቀላሉ ቋሚ የፅዳት ሰራተኞች መቅጠር፤ ህንፃዎች ሲገነቡ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ታሳቢ ያደረጉ ቢሆኑ በተለይ የአካል ጉዳተኞችን እና አረጋዊያንን ግምት ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም ቢሮዎች ሲመደቡ ተገልጋይ የሚበዛባቸው ቢሮዎች ከታች ምድር ላይ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

የኤሌክትሪክ ሃይል እና ኢንተርኔት መቆራረጥ፣ የግብዓት አቅርቦት እንደ ወረቀት፤ ወንበር፤ ጠረጴዛ፤ መቀመጫ፤ ፕሪንተር፣ ኮፒ እና ሌሎች እጥረት መኖር፣ የሰራተኞች መንቀሳቀሻ የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት በተመለከተ ወረዳዎች በጀት ሲይዙ እነዚህን ችግሮች

ለመፍታት በታቀደ መንገድ ማድረግ። ቢያንስ አንድ ወረዳ ላይ አንድ ጀነሬተር እንዲኖር ማድረግ፣ ደንበኞች አንድ ኮፒ ለማድረግ ብዙ ርቀት መሄድ ሳያስፈልጋቸው እዛው ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

ባልተደራጀ የሰነድ አያያዝ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጅን ባለመጠቀም የሚመጣውን የሃብት ብክነት፣ የሰነድ መጥፋት፤ መፋለስ፣ መቀደድ አንዳንዴም በአይጦች መበላትን ለመቀነስ መንግስት የኢንተርኔት መረጃ ሲስተምን እንደዋና ትኩረት አድርጎ ሊሰራ ይገባል። በኮምፒውተር የተደገፈ እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ ድረስ የተያያዘ የሰነድ አያያዝ መንገድን መጠቀም።

በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የሰው ሃይል እጥረት ስለ አለ የሰው ሃይል የሚያስፈልግባቸውን ቦታዎች ማሟላት ይገባል።

የደንበኞች የግንዛቤ ማነስ አላስፈላጊ ተጠቃሚነት፣ የስነ-ምግባር ችግሮች እና ለወረዳ ቢሮዎች ጽ/ቤቶች ያላቸው እይታ ዝቅተኛ መሆን እንደ ምክንያት ተጠቅሰዋል። በመሆኑም የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም እያንዳንዱ ቢሮ ወይንም ጽ/ቤት የሚሰጠውን አገልግሎትን፣ መብት እና ግዴታ፣ እንዲሁም ባለጉዳዮች ማድረግ ስለሚገባቸው ነገሮች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት። በተለይ ስለ ቅሬታ እና አቤቱታ ሰሚ ጽ/ቤት የግንዛቤ ፈጠራ ስራው በደንብ መሰራት ይኖርበታል።

ሌላው የደንበኞችን አላስፈላጊ የተጠቃሚነት ፍላጎት ችግርን ለመቅረፍ ተጠያቂነትን ማስፈን። ግለሰቦች አላስፈላጊ እና ከህጉ ውጭ ተደጋጋሚ ጥፋት ሲፈፅሙ ተጠያቂ ማድረግ።

የስራ ሰዓት አለማክበር፤ ማርፈድ፤ መቅረት፤ በስራ ሰአት አቋርጦ መውጣት፤ ሰራተኞች ለደንበኞች ያላቸው አቀባበል ዝቅተኛ መሆን፤ የአገልጋይነት ስሜት እና ተነሳሽነት አየቀነሰ መምጣት፤ ተገልጋዮችን በቅንነት ትኩረት ሰጥቶ ለማገዝ አለመሞከር፤ እና ህጎችን፤ ደንቦችን እና መመሪያዎችን አውቆ አለመስራት ለቅሬታ መነሻ ምክንያቶች እንደሆኑ ተገልጿል። በመሆኑም የሰራተኞች ቁጥጥርን መጨመር፤ የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ስለ ህዝብ አገልጋይነት ተደጋጋሚ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና አመለካከትን የመቀየር ስራ መስራት። ምቹ የስራ አካባቢን ለሰራተኞች በመፍጠር ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ። ጥሩ አገልግሎት ለሚሰጡ ሰራተኞች በቋሚነት ማበረታቻ በማዘጋጀት ጤናማ ውድድር እንዲኖር ማድረግ። የሚለኩ እና ተጨባጭ የሆኑ የውጤት መመዘኛ መንገዶችን በማዘጋጀት ሰራተኞች ከራሳቸው ጋር የሚወዳደሩበትን መንገድ ማመቻቸት ብሎም የደረጃ እድገቶችን በትክክለኛ መንገድ በተቀመጡት መመዘኛዎች ማድረግ።

የሰራተኛውን መሰረታዊ ችግሮች አቅም በፈቀደ መንገድ መፍታት እና ትኩረቱን ስራው ላይ አድርጎ እንዲሰራ ማድረግ። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በየሴክተር መስሪያ ቤቶች ያሉ ህጎችን መመሪዎችን እና ሰርኩላሮችን በቅርብ የማግኘት እና የማንበብ ልማዱ ወይንም ተነሳሽነቱ አናሳ ነው። በመሆኑም በይበልጥ ተደራሽ በማድረግ ሰራተኛው አንብቦ፤ ተረድቶ እና አውቆ እንዲሰራ ለማድረግ አዋጆች፤ መመሪያዎች፤ ሰርኩላሮች እና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ህጎችን በየ ፅ/ቤቱ እንደ ቤተ-መፅሐፍት ወይንም መደርደሪያ በማዘጋጀት በየቀኑ ሁሉም ሰራተኞች ሊያገኟቸው እና ሊያነብቧቸው በሚችሉበት ቦታ በማስቀመጥ እንዲያነብቡ ማድረግ። ይህም ከህጎች እና ከደንቦች ጋር ያለውን ክፍተት ለመሙላት ያስችላል። በተጨማሪም ስለ ህጎች እና መመሪዎች በተመለከተ ሰራተኞችም ሆኑ አመራሮች ያለባቸውን ክፍተቶች ለመቅረፍ ቀጣይነት ባለው መንገድ በትኩረት ስልጠናዎችን መስጠት እና የማብቃት ስራ መስራት።

ወደ ገፅ 40 ዞሯል


1
መጀመሪያ እኔ ከገደሉ ልውጣና ከዛ እኛተ..
2
ለምን ለሁለት ኣትካፈሉትም?
1
2


3
ብንስማማ ኖሮ
እንዲህ ጉድባልሆንን
ነበር!
4
ኢሃሃሃሃሃ....
3

# ከገፅ 37 የዞረ


## *ማጠቃለያ*

የለውጡ ምክንያትም የለውጡ መለኪያም የሆነውን የህዝብን ቅሬታ ትርጉም በአለው መልኩ መፍታት እንደ አንድ አቢይ ተግባር የያዘው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅሬታ ምንጮችን እነሆ ከደመነፍስ እና ከስሜታዊ ጭፍን ግምት ይልቅ በሳይንሳዊ ጥናት እንዲደገፍ አድርጓል፡፡

የመፍትሄ ሃሳቦቹም በዚሁ መንገድ ተለይተው ቀርበዋል፡፡ ለተጠና ችግር የተጠና የመፍትሔ ሃሳብ ከቀረበ ዘንዳ ቀሪው ተግባር የከተማ አስተዳደሩ ፖለቲካዊ አመራር፣ የየተቋሙ አመራርና ባለሙያ ቀና ርብርብን የሚሻ ነው፡፡

በቁጥርም በጥራትም ከፍተኛ ምሁራዊ አቅም ተበጅቶለት የተሰራ ጥናት ስኬታማ የሚሆነው የመፍትሄ ሃሳቦቹን ወደ ተግባር በቀናነትና በቁርጠኝነት የሚመነዝር የሰው ሃይል ሲኖር ነው፡፡ አለበለዚያ ማለፊያ የመደርደሪያ ማሳመሪያ ሆኖ አቡዋራ ይለብሳል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ለውጡ አይፈቅድም፤ ሌላው ቀርቶ በአፈፃፀም ላይ እንኳን የትጋት መጓደል ጎታች ነው የሚሆነው፡፡

በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኘው ከመቶሺህ በላይ ሲቪል ሰርቫንት፣ ባለሙያና አመራር የቅሬታ ምንጮችን ለማድረቅ በቁርጠኝነት ሊነሳ ይገባል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ የለውጡ መሪሃይል የሆነው ድርጅታችን የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ ይጠበቃል፡፡ የመሪነት ሚና የሚተገበረው ደግሞ በመንፈስ ሳይሆን በየተቋሙ የሚገኝ አመራርና አባል የግንባር ቀደምነትና አርዓያነት ሚናውን ሰርቶ በማሳየት ሌሎችን ማስተካከል አለበት፡፡ ከዚህ አንፃርም እኔ እንደ አንድ የመሪ ድርጅት አመራር ወይም አባል ምንድነው የሚጠበቅብኝ የሚለውን ራስን መጠየቅና ራስን ለለውጥ ሃይልነት ማብቃት ያሻል፡፡




**በቅደም ተከተል**
**መግጠም**
**ከስር የሚገኙትን አምስት ቁራጭ ጥለቶችን በመገጣጠም ከላይ የሚታየውን አንድ ረጅም ጥለት ይፍጠሩ፡፡ እባክዎን የአገጣጠም ቅደም ተከተሉን ይዘርዝሩልን፡፡**

**የዚህ ዕትም ጥያቄዎችን መልስም በawdelewt@gmail.com ኢሚይል አድርጉልን።**

# ስለውጡ ውስጥ ግጭቶች መፍትሔዎች እንሁን

ግጭት የሰው ልጅ ከሚከሰቱበት የህይወት ገጠመኞቹ አንዱ ነው፡፡ በዚህም ከሠው ልጆች መፈጠር ጀምሮ አሁን እስካለበት የስልጣኔ ደረጃ ድረስ ብዙ የግጭት ውጣ ውረድ አልፎ እንደመጣ እርግጥ ነው፡፡ የብዙ ግጭቶች መነሻ ምክንያት በትክክል ይሄ ነው ብሎ መናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ለምን ከተባለ ግጭቶቹ በአንድ ጊዜ በሚፈጠር ሁነት ብቻ የሚመጡ ሳይሆኑ የበርካታ ችግሮች ድምር ውጤት ናቸው፡፡ በአንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ውስጥ ያለ የሀሳብና የፍላጐት ተቃርኖ ድንገት ምክንያት ሲያገኝ ፈንድቶ በመውጣት ሁለቱን አካላት ወደ ለየለት ግጭት እንዲያመሩ ምክንያት ይሆናል፡፡ ከግጭት ጋር የተያያዙ አንዳንድ መረጃዎች ይህንን ከግምት በማስገባት ግጭት በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ማለትም በኢኮኖሚ፣ በእሴት እና በስልጣን እንደሚከሰቱ ይገልፃሉ፡፡

## ኢኮኖሚያዊ ግጭት (Economic Conflict)

የግጭት መነሻ ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ነው ሲባል ቡድኖች ወይም ግለሰቦች የተፈጥሮ ሀብት ውሱንነት ሲያጋጥማቸው አንዳቸው ከአንዳቸው የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያደርጉት ጥረት ወደ ግጭት እንዲገቡ ምክንያት ይሆናቸዋል ማለት ነው፡፡ ሁለቱ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ያላቸው ፍላጎት እየናረ ሲመጣ ይህን ፍላጐት ለማሳካት ፉክክር ውስጥ ስለሚገቡ መጨረሻቸው ግጭት ይሆናል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግና አስተዳደር ኮሌጅ የሰብዓዊ መብትና ፌዴራሊዝም ረዳት ፕሮፌሰሩ ዶክተር ሲሳይ መንግስቴ ግጭት በእራሱ ማህበራዊ ክስተት እንደመሆኑ መጠን ከህብረተሰቡ እድገት ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑንና ኢኮኖሚያዊ ይዘት ሊኖረው እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ጤናማ በማይሆንበትና ጎጂ በሚሆንበት ጊዜ አደገኛነቱ እየጎላ እንደሚሄድም ነግረውናል፡፡

## የእሴት ግጭት (Value Conflict)

እነዚህ የግጭት መነሻ ምክንያቶች በሰው ልጆች የአኗኗር ዘይቤ፣ የርዕዮተ ዓለም ምርጫና ፍላጐት መቃረን ማለትም የኑሮ መርህና እምነት መለያየት የሚፈጥሯቸው ናቸው፡፡ ይህም ማለት የእነርሱ ስለህይወት ያለ አመለካከትና እምነት ከሌላው ጋር አልጣጣም ሲል አልያም የሌሎችን የአኗኗር ዘይቤ በግድ እንዲከተሉ ጫና ሲደርስባቸው ይህ አይነቱ ግጭት ይፈጠራል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግና አስተዳደር ኮሌጅ የሰብዓዊ መብትና ፌዴራሊዝም መምህር አቶ

*"በተግባቦት ሂደት በሚፈጠር አለመጣጣም ሳቢያም ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ ሁሉም ሰው አንድን ነገር በራሱ አመለካከት ብቻ አጥሮ ሲተረጉም ተግባቦት ይቀጭጫል፤ ከነአካቴውም ይከስማል፡፡ ይህ ደግሞ ለግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡"*

አባይ ይመር እሴትን መሰረት ያደረገ ግጭት ከማንነት ጋር ተያያዥነት ስለሚኖረው የግጭቱ ስፋትና መጠን የከፋ ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል አውግተውናል፡፡

## *የስልጣን ግጭት (Power Conflict)*

ይህ የግጭት መነሻ የሚፈጠረው አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ በሌላኛው ቡድን ወይም ግለሰብ ላይ የበላይ ለመሆን ተፅዕኖ ሲያሳርፍ አንዱ ወገን በሌላኛው ላይ የበላይ ለመሆን የሚያደርገው ጥረት ሁሌም የግጭት መንስኤ መሆኑንም ዶክተር ሲሳይ እንደገለፁት ተፅእኖ የደረሰባቸው ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች የተነጠቁትን የኃይል ሚዛን ወደ እራሳቸው ለመመለስ ጥረት ማድረጋቸው ስለማይቀርም የስልጣን ሽኩቻው አይቀሬ ይሆናል፡፡ እንደ ምሁሩ ገለጻ ይህ ግጭት እልባት የሚያገኘው አንዱ ወገን ተሸናፊነቱን አውቆ የሌላኛውን ወገን የበላይነት ሲቀበል ነው፡፡ ይህ የግጭት መንስኤ በግለሰቦች፣ በቡድኖች ወይም በሀገር ደረጃ ሊፈጠር ይችላል፡፡

ዶክተር ሲሳይ መንግስቴ እነዚህ የግጭት ምክንያቶች በተናጠል ለግጭት መንስኤ የሚሆኑበት አጋጣሚ መኖሩንና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሶስቱ አልያም ሁለቱ ተዳብለው ለአንድ ግጭት እሳትና ነዳጅ የሚሆኑበት አጋጣሚ እንደሚፈጠር አውግተውናል፡፡ በዋናነት የግጭት ምክንያቶች ተብለው እነዚህ ተጠቀሱ እንጂ በተግባቦት ሂደት በሚፈጠር አለመጣጣም ሳቢያም ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ ሁሉም ሰው አንድን ነገር በራሱ አመለካከት ብቻ አጥሮ ሲተረጉም ተግባቦት ይቀጭጫል፤ ከነአካቴውም ይከስማል፡፡ ይህ ደግሞ ለግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡

ግጭት ዓይነቱ የተለያየ ቢሆንም በሚሳተፉ አካላት ልክ መከፋፈል ይቻላል፡፡ ክፍፍሉ ከግለሰብ ጀምሮ እያደገ በመሄድ ድንበር ተሻጋሪ ወደሆኑ አለም ዓቀፍ ጉዳዮች ይደርሳል፡፡ ለአብነት ግለሰባዊ ግጭት (Interpersonal conflict) የግጭት ዓይነት የሚፈጠረው ሁለት ሰዎች በፍላጎት፣ በዓላማ፣ በአቀራረብ በተግባቦት መጣጣም ሲያቅታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ልዩነታቸውን ለማጥበብና የዓላማ ልዩነታቸውን አቻችለው ማስኬድ ከቻሉ በመካከላቸው ያለው ተቃርኖ ይቀንሳል፡፡ ዶክተር ሲሳይ ‹‹እንዲያውም የተግባቦት አቅምን በትምህርት በማበልፀግ እንዲህ አይነቱን ግጭት ለማስቀረት መፍትሄ ነው›› ይላሉ፡፡

ሌላኛው ቡድናዊ ግጭት (Intergroup conflict) ሲሆን ይህ የግጭት ዓይነት የአመለካከት፣ የባህልና የዝርያ አንድነት ባላቸው ሰዎች የተፈጠረ ቡድን በተመሳሳይ ከተፈጠረ ሌላ ቡድን ጋር የሚያደርጉት ግጭትን ያጠቃልላል፡፡ ይህ አንድ ቡድን በሌላኛው ላይ የበላይ ለመሆን ሲሻ፣ ሲያገልና ሲንቅም የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው፡፡ መገለልና ንቀት የደረሰበት ቡድን ይህን የበታችነት ስሜት አምኖ ሳይቀበል ሲቀር ተቃርኖው የከፋ ይሆናል፡፡ በአቅም ውሱንነት አልያም በተለያዩ አመለካከቶች ሳቢያ ዝቅተኛነቱን አምኖ ሲቀበል ግን ግጭቱ ዘላቂ መፍትሄ ባይኖረውም ይረግባል-እንደ ዶክተር ሲሳይ መንግስቴ አገላለጽ፡፡

ዶክተር ሲሳይ መንግስቴ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከላይ ከጠቀስናቸው ዋና ዋና ምክንያቶችም በላይ አሳሳቢና አስጊ ሆኖ እስከ መታየት የደረሰም ነበር፡፡ የሚታይና የአጋጠመ መታወክም አለ፡፡ በማንኛውም ጊዜ ላይ ዴሞክራሲን የገነቡም ሆነ በመገንባት ላይ ያሉ አገራት እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ይገጥማቸዋል፡፡ አገራቱ ከአንደኛው የፖለቲካ ምዕራፍ ወደ ሌላኛው ሽግግር በሚያደርጉበት ጊዜም ግጭቶችና አሁን በአገር ውስጥ

***"የቤት ስራዎቻችንን ተጋግዘንና ተደጋግፈን ማሟላት እንጂ በውሃ ቀጠነ መነሾ መጋጨት የለብንም፡፡"***

ከሚስተዋሉት ሁነቶች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ችግር ይታያል። በአግባቡ መምራት ከተቻለ፣ ሽግግሩ ውጤታማ የሆነ የዴሞክራሲ ግንባታ ደረጃ ላይ ይደርሳል።

በአንጻሩ አሁን በሽግግሩ ጊዜ የሚታየውን ሁኔታ በአግባቡ መምራት ካልተቻለ፣ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዳይሸጋገር ማድረግ ካልተቻለ ሽግግሩ ላይሳካ ይችላል። ይህ ዓይነት ሁኔታ ተመሳሳይ የፖለቲካ ሽግግር ውስጥ የገቡ አገራት ተሞክሮም ያሳያል። ለምሳሌ፤ ሊቢያን ብንመለከት ኮሎኔል መሀመድ ጋዳፊ ከስልጣናቸው በአመጽ በወደቁ ማግስት የተፈጠረው የሰላም መታወክ ለአገሬው ዜጎች ጥሩ አልነበረም። እንዲያውም ጋዳፊ በፕሬዝዳንትነት በነበሩበት ጊዜ የነበረው ሁኔታ ይሻላል ማለትም ይቻላል። ሶርያን ብንወስድም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው።

በኢትዮጵያም አሁን የሚታየው ሁኔታ ስጋት የተጋረጠበት ነው። ከለውጡ ዋዜማ አንስቶ በአንዳንድ አካባቢዎች ልዩ ልዩ ግጭቶች በመከሰታቸው ምክንያት፣ የሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ሥጋት ላይ ከርሟል። ቁጥራቸው ወደ ሶስት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች በግጭት ምክንያት መፈናቀላቸው በአንዳንድ የአገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን በተደጋጋሚ ጊዜ ይገለጻል። በመሆኑም፤ የህግ የበላይነት ሰፍኗል ብሎ ለመናገር አይቻልም። የዜጎች የመንቀሳቀስ መብት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል። ማንነት የግጭት መንስኤ ሆኗል ይላሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰብዓዊ መብትና ፌደራሊዝም መምህሩ አቶ አባይ ይመርም፤ አገሪቱ በለውጥ ሂደትና በሽግግር ላይ የምትገኝ እንደመሆኗ የተለያዩ በለውጡ ሂደት ደስተኛ ያልሆኑ አካላት እዚህም እዚያም በሚፈጥሩት ነገር ግጭቶች እንደሚከሰቱና በተለያየ ሁኔታ ላይ የሰላም መደፍረስ እንደሚታይ ያመለክታሉ። ከአንዳንድ አገሮች ነባራዊና ታሪካዊ ሁኔታ አንጻር በሚታይበት ጊዜም የሰላም ሁኔታው አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ የታየበት ሁኔታም ነበር ሲሉም ይጠቁማሉ።

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት የግጭት አፈታት የሰላም እሴቶች ግንባታ ጥናትና ንቃተ ህገ መንግሥት ዳይሬክተር አቶ አስቻለው ተክሌ፤ ኢትዮጵያ በለውጥ ላይ እንደምትገኝ ያነሱና፤ መንግሥት የሕዝቡን ጥያቄ በዘለቄታዊነት ለመመለስ ስር ነቀል እርምጃዎችን ሲወስድ መቆየቱን ይጠቅሳሉ። በርካታ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮችን፣ ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ አክቲቪስቶችን ከእስር መፍታቱ፣ በአገር ውስጥ ካሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሲቪክ ማኅበራት ጋርም በለውጡ ዙሪያ ሠፊ ውይይት ማድረጉን፣ በውጭ አገራት ተሰድደው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ተቃዋሚዎችንና የፖለቲካ አክቲቪስቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባቱን፣ የትጥቅ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ ኃይሎች ወደአገር ውስጥ መግባታቸውን ማሳያ አንስተው ይገልጻሉ።

የምርጫ፣ የሲቪክ ማኅበራት እና የተለያዩ ሕጎችን የማሻሻል ስራም መጀመሩንና የፍትህና የፀጥታ ተቋማትን ጨምሮ ሰፋ ያለ ተቋማዊ የመዋቅር ማሻሻያዎችም መደረጋቸውንም ያመለክታሉ። ከኤርትራ ጋር የሰላም ስምምነት በማድረግ መልካም ግንኙነት እንደተጀመረና እርምጃዎቹ የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋት እንዳስቻሉም ይጠቁማሉ። አቶ አስቻለው፤ ለግጭት መንስኤ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው። አሁን የሚታየው ግጭት አብዛኛው የሚያጠነጥነው የማንነት ጉዳዮች እና ያልተመለሱ ጥያቄዎች ላይ ነው። ለውጡ ተቋማዊ አለመሆኑ፤ በሂደት ላይ መገኘቱ፤ የፖሊሲ ማዕቀፍ ያልተሰራለት መሆኑ የግጭት ዋና ዋና አባባሽ ምክንያቶች ልንላቸው እንችላለን።

*"ምሁራን ሲሎች የእውቀትም ሆነ መደረኮን የማግኘት ችግር እንደለበባቸው ለካላት በተለያዩ ግፊቶች በስሜት መነዳት ሳይሆን እውነትና እውቀትን ለዳብሰው ጤናማ አሰባትን የሚያበረክቱ መሆን ለለባቸው።"*

ለውጡ ከመጣ በኋላ ግጭት የሌለባቸው አካባቢዎችም የግጭት ቀጠና ሆነዋል፡፡ በፊት የነበረው በወልቃይት ጠገዴ፣ በራያ በኩል ጎንደር የተወሰነው ማዕከላዊና ምዕራብ ጎንደር ቀጥሎ ደግሞ ምስራቅ አማራ በተለይም ወሎና ሸዋ አካባቢ ግጭቶችም ስጋቶች ተስተውለዋል፡፡ በደቡብ ክልልም ብንመለከት በፊት ግጭት የነበረባቸው ጌዴኦና ጉጂ ብቻ ነበሩ፡፡ ቀጥሎም አማሮ ወረዳ፣ ኮሬዎችና በዚያ አካባቢ ኗሪዎች ተጋጭተው ነበር፡፡ መፈናቀሎችም ታይተዋል፡፡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም መተከል አካባቢ የነበረውን ግጭትም ማየት ይቻላል፡፡

ሌላው ችግር የሚመነጨውም ይላሉ አቶ አስቻለው፣ የልሂቃን ተቃውሞ መኖር ነው፡፡ ከ19 60ዎቹ ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አብዛኛው የሚቃኘው በልሂቃን ነው፡፡ የልሂቃኑ ህልም ደግሞ በርካታው ማለት በሚቻልበት መልኩ እርስ በእርሱ የማይታረቅ ነው፡፡ ሁልጊዜም ህዝቡን እንደ መሳሪያ ተጠቅመው የራስን ፍላጎት ብቻ ለማሟላት ይጠቀሙበታል፡፡ የብዙሃን መገናኛ ጽንፍ መያዝም አንድ ችግር ነው፡፡ ሌላው ልንም የሌለውና ህጋዊ አካሄድን የማይከተለው የማህበራዊ መገናኛ ትስስር ግጭቶች እንዲባባሱ አንዱ ሌላውን በሌላ መልኩ እንዲያስበው የሚያደርግበት ሁኔታ አለ፡፡ እነዚህን እንደ አባባሽ ምክንያቶች ልንጠቅሳቸው እንችላለን፡፡

ለውጡ ያመጣው በጎ ነገር ቢኖርም የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች ጉድለት መኖርም እንደ አንድ ምክንያት ይወሰዳል፡፡ ዶክተር ሲሳይ ለአገራዊ ግጭቱ ዋናው ምክንያት ተብሎ የሚታሰበው የአገሪቱ ፖለቲካ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፉ ተዋንያን በመካከላቸው ያለው ግንኙነት አገር ውስጥ ላለው የሰላም ሁኔታ ወሳኝ ተደርጎ ይታያል፡፡ ይህ ማለት ፖለቲከኞች የሚያራምዱት አቋም ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የሚኖራቸው ልዩነትና ይህን ለመፍታት የሚከተሉት መንገድ የሰለጠነ ካልሆነ ወደ ግጭት ያመራል፡፡ ልዩነታቸውን ተነጋግረው በማጥበብ፣ በሚያግባቧቸው ጉዳዮችም በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በማያግባቧቸው ጉዳዮችም ሃሳባቸውን አቅርበው በህዝብ መዳኘት አለባቸው፡፡ ይህን ዓይነት አካሄድ ካልተከተሉ ሁል ጊዜም ግጭት መከሰቱ አይቀርም ይላሉ፡፡

አገሪቱ የምትከተለው ፌዴራሊዝም በአደረጃጀት የተከተለው ብሄር ተኮር መዋቅር ለግጭት አንዱ ምክንያት ተደርጎ ይታሰባል የሚሉት ዶክተሩ፣ አንዳንዶች በአገር ውስጥ ላሉ ግጭቶች መነሻም ሆነ መድረሻ ህገ መንግሥቱን አድርገው የሚወስዱ መኖራቸውንና ምክንያቱ ደግሞ ህገ መንግሥቱ የብሄር ፌዴራሊዝምን ያዋቀረና አሁን በዋናነት በሚፈጠረው ማንነት ላይ መሰረት ባደረገው ግጭት ምክንያት መሆኑን እንደሚጠቅሱም ያወሳሉ፡፡ አሁን ከሚታየው ተጨባጭ ችግር አንጻር አብዛኛው እየተከሰተ ያለው ግጭት በብሄሮች መካከል እንደመሆኑ ያለውን የፌዴራሊዝም አደረጃጀት የግል ጥቅማቸውን ለማራመድ የተሰለፉ አካላት የተጠቀሙበት እንደሆነ ይታያል፡፡

በተጨማሪም፣እንደ ምክንያት መውሰድ የሚቻለው የተለያዩ የማህበረሰብ አንቂዎች /አክቲቪስቶች/ እና ልሂቃን ነን የሚሉ አካላት አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሚፈልጉትን ማህበረሰብ ለማንቀሳቀስ የሚጠቀሟቸው አገላለጾች፣ መግለጫዎች፣ ቅስቀሳዎችና ሌሎች ጥሪዎች ለግጭት ይዳርጋሉ፡፡ ይህ ከማህበራዊ ድረ ገጽ ጋር ተዳምሮ ሌላ የግጭት መንስኤ እየሆነ ተስተውሏል፡፡ ባይ ናቸው፡፡ ለእዚህ እንደ ድልድይ እያገለገለ ያለው በከፍተኛ ሁኔታ አብዛኛው ወጣት ሥራ አጥ መሆኑ ነው፡፡ ከሥራ አጥነት ጋር ተያይዞ ተስፋ መቁረጥ አለ፡፡ ይህ ወጣት ደግሞ በምክንያት ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ እንዲገነባ ማድረግ ካልተቻለ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ወጣት የግልና የቡድን ፍላጎታቸውን ማስፈጸም የሚፈልጉ አካላት የመሳሪያነት ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ፡፡

በመንግሥታዊ የስልጣን እርከን ላይ የሚገኙ አንዳንድ ሆድ አደር የፖለቲካ አመራሮችና ሌሎች አካላት በውጭ መዋቅር ውስጥ ያላቸውን ስልጣንና ተሰሚነት በመጠቀም አንዳንዶች

ከኃላፊነት የተነሱም በህገ ወጥ ሥራ ላይ መሰማራታቸው ለግጭት እንደ አንድ መንስኤ እየሆነ ነው፡፡ መንግሥት በጉያው ውስጥ ያሉትን አካላት ለይቶ አለማወቁ ወደፊትም የሚያሳስብ ከመሆኑም ባሻገር ግጭት ሊነሳ የሚችልበትን ጊዜም ለማወቅ አዳጋች ነው፡፡

አቶ አስቻለው እንደሚገልጹት፤ አዲስ የለውጥና የሽግግር መንፈስ በአገሪቱ ቢሰፍንም፣ ለውጡን የሚያደናቅፉና በሕዝቦች መካከል መቃቃርን፣ ጥላቻን፣ አለመተማመንንና መነጣጠልን ያስከተሉ በርካታ ሥርዓት አልበኝነት፣ ግጭቶችና ብጥብጦች ተከስተዋል፡፡ አንዱና ትልቁ ክስተት ብሔርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችና ብጥብጦች ናቸው፡፡ በእርግጥ ግጭቶቹና ብጥብጦቹ ባሳለፍናቸው ጥቂት ዓመታት ውስጥ የተከሰቱ ቢሆንም፣ ለውጡ ከተጀመረ ወዲህ ስፋታቸውና ውጤታቸው አስከፊ እየሆኑ መጥተዋል፡፡

አቶ አስቻለው በምሳሌነት ሲጠቅሱም፤ ጅግጅጋ፣ ሀዋሳ፣ በአዲስ አበባ ቡራዩ፣ ጉጂ፣ አሶሳ፣ ሚዛን ቴፒ እና ካማሺ (በቤኒሻንጉል ጉሙዝ የሚገኝ ዞን) ሐረር የተከሰተው ብሔርን መሠረት ያደረገ ጥቃትና ግጭት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አፈናቅሏል፣ በርካታ የሰው ሕይወትም አጥፍቷል፡፡ በርካቶችን አካል ጉዳተኛ አድርጓል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2018 የመጀመሪያው አጋማሽ ከአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ተፈናቃዮችን በመያዝ በዓለም ካሉ አገራት ቀዳሚ እንድትሆን አድርጓታል፡፡

ለውጡን እያደናቀፈ የሚገኘው ችግር ስርዓት አልበኝነት ነው የሚሉት አቶ አስቻለው፤ ሕብረተሰቡ አገራዊ ለውጡ የፈጠረውን መልካም ዕድል ተጠቅሞ ማንኛውንም አይነት ጥያቄ ወደ መንግሥት የሚያቀርብበት ዕድል ሳለ፤ በአንዳንድ አካባቢዎች የመንግሥትን ሕልውና በሚፈታተን መልኩ በርካታ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ይታያል ይላሉ፡፡ ሕገ-ወጦቹ ድርጊቶች ክልሎችን የሚያገናኙ የፌዴራል መንገዶችን መዝጋት፣ የእምነት ተቋማትን ማቃጠል፣ ነጻ የቁሳቁስና አገልግሎት ዝውውሮችን ማገድ፣ የመንግሥት ተቋማትን መዝጋት እና ኃላፊዎችን ማውረድ፣ ያለ በቂ መረጃ በመንጋ ፍርድ የሰውን ሕይወት ማጥፋት፣ ‹ጥያቄያችን ምላሽ አላገኘም› በማለት በተለያዩ አካባቢዎች የሚደረገው ሕገ-ወጥ ድርጊት የሰዎችን ደህንነትና ሰላም ሲያናጋ ቆይቷል ሲሉም ያብራራሉ፡፡ ዘላቂ ሰላም ሊገኝ የሚችለው የግጭቶችን መነሻ ምክንያታቸውን በሚገባ በመመርመርና መፍትሄ ሲፈለግለት ብቻ ነው፡፡ ከላይ ከላይ ለሚታየው ችግር ብቻ መፍትሄ ብንሰጥ ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ ሰላም አናገኝም ባይ ናቸው አቶ አስቻለው፡፡

ከዚህ በኋላ ግጭቶች እንዳይከሰቱ የሚስተዋሉትም እንዲከስሙ ከተፈለገ ሁሉም አካላት የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል፡፡ በተለይም የመንግሥት የአደጋ ጊዜ መከላከል ሂደት የተሻለና ሊፈጠሩ የሚችሉ ቀውሶችን የሚቀንስ ብሎም የሚከላከል መሆን ይገባዋል፡፡ የደህንነት ስጋት አለ ተብሎ በሚታሰብበት ጊዜ በተለይም፤ ከአካባቢው ማህበረሰብና በአካባቢው ካሉ አገር በቀል ተቋማት፣ ሽማግሌዎችና የሃይማኖት ተቋማት ጋር አብሮ በመስራት መከላከል የሚቻልበት መንገድ መዘርጋት ዘላቂ መፍትሄው ሊሆን ይችላል ባይ ናቸው አቶ አስቻለው፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የመንግሥት አካላት መረጃዎች እንዳላቸው ሲገልጹ ይሰማል፡፡ ለምሳሌ፤ የአማራን ክልል ማንሳት ይቻላል፡፡ ማዕከላዊ ጎንደር ላይ ለነበረው ግጭት መረጃ እንደነበራቸው የክልሉ መንግሥት ከግጭቱ በኋላ ሲገልፁ ነበር፡፡ አጣዬ፣ ከሚሴ አካባቢ የተፈጠረው ግጭትም በተመሳሳይ መልኩ ይታያል፡፡ ይህ የሚያሳየው መከላከል አለመቻሉን ነው፡፡ የመንግሥት አካላት የደህንነት ስጋት መኖሩ መረጃ ካላቸው ቅድመ መከላከል ላይ አልሰሩም ወይም ክፍተት አለ፡፡

ችግር ከተፈጠረ በኋላ የሚደረገው እንቅስቃሴ በቂ አይደለም፡፡ የአካባቢውን ማህበረሰብ በመያዝ፣ የችግር መፍቻ ተቋማትን በመጠቀም ለማስታረቅ ነው የሚሞከረው፡፡ መንግሥት

ግጭትን አስቀድሞ በመከላከል ረገድ ተቋማቱን ቢጠቀምባቸው ኖሮ ግጭት እንዳይነሳ ማድረግ ይቻላል። ከተነሳም ደግሞ አደጋ ሳያደርስ ችግሮች ሳይከሰቱ ባለበት እንዲቆይ ማድረግ ይቻላል። ስለዚህ ግጭት በመከላከል ላይ ጠንከር ያለ፣ ተቋማዊ ይዘት ያለውና ሁሉን አቀፍ የግጭት አፈታትን የተላበሰ አሰራር ሊተገበር ይገባል ይላሉ።

የህግ የበላይነት አሁን ባለበት ሁኔታ ተጨማሪ ስራዎች ያስፈልጉታል። ሰዎች ያለስጋት መንቀሳቀስ አለባቸው፣ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርም ከጊዜ ጊዜ እየተባባሰ ይገኛል። በእነዚህ ላይም መስራት ያስፈልጋል። የህግ የበላይነትም መከበር አለበት። ብዙሃን መገናኛዎችም ግጭት መከላከል ላይ መስራት አለባቸው። ግጭት ከተከሰተ በኋላ ደግሞ ማርገብ የሚችል ሥራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን በተለይ ማህበራዊ ሚዲያ ግጭት የሚያስነሳና አባባሽ ሁኔታ ጎልቶበት ይታያል። ይህንንም ሰዎች በተሳሳተ ሁኔታ ስለሚረዱት ራስን የማደራጀት ሁኔታ ይኖራል። በግጭት ጊዜም እንዲህ ዓይነት የግንኙነት ሁኔታ አደጋ ላይ ይጥላል። በመሆኑም መገናኛ ብዙኃን ግጭትን ሊያረግብና ሊከላከል የሚችል፣ የህብረተሰብን ሰላማዊ መስተጋብር ሊያጠነክር የሚችል የዘገባ ሥራ ሊሰሩ ይገባል። ይህ ፈር የለቀቀው የመገናኛ ብዙሃኑ ዘገባ  ከነባራዊ ሁኔታ አንጻር ወደ ከፋ ቀውስና ብጥብጥ ሊከት ይችላል።

መምህር አባይ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ዘላቂ መፍትሄ የሚሆነው አገራዊ መግባባት መፍጠር ነው። ፍጹም መግባባት ባይኖርም በመሰረታዊ ጉዳዮች ተነጋግሮ መግባባት ይቻላል። አዲስ የፖለቲካ የጨዋታ ህግ ማዘጋጀትም ያስፈልጋል። ለውጡ ይዞት የመጣው የጨዋታ ህግ በአግባቡ ባለመታወቁ አንዳንዶች ሂደቱን ባልተገባ መንገድ ለግል ጥቅማቸው እያዋሉት ይገኛሉ።

ሰላም ለማስፈን ተብሎ የተደራጁ የተለያዩ አካላት አሉ። ለምሳሌ፤ የሰላምና ዕርቅ ኮሚሽንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ሚናቸውን በተገቢው መንገድ መወጣት አለባቸው። ግጭቶችን የማባባስ ሚና ያላቸው አካላት ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል። የፍትህ ሥርዓቱ ለሚዲያ ፍጆታ ብቻ ተብሎ ሳይሆን በአግባቡ መለወጥ፤ በትክክል ነጻ መሆን ይጠበቅበታል። በዋና ዋና የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል መግባባት መፈጠር አለበት። ሁሉም ሰርቶ እኩል መጠቀም የሚችልበት ሁኔታም መዘርጋት ይገባዋል። ወጣቱ ከተስፋ መቁረጥ ተመልሶ ወደ ገንቢ ሚና የሚገባበት ሁኔታ መኖር አለበት። ፖለቲከኞች ከግል ፍላጎት በዘለለ ህዝብን በሚጠቅም ዓላማ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። መንግሥት በጉያው ውስጥ ያሉትን በተለያየ የጥፋት ተግባር የተሰማሩ አካላትን መለየትና መነጠል ይጠበቅበታል።

ሰላምን ከማስፈንና ግጭቶችን ከማርገብ አኳያ መንግሥት እየሰራ ያለውን ሁኔታ በቂ ነው ለማለት ይከብዳል። በተለያዩ አካባቢዎች መፈናቀል ግጭቶች ከጊዜ ጊዜ እየተባባሱ ናቸው። ችግር ከተፈጠረ በኋላ ሰላምን ለማምጣት የአካባቢውን ችግር መፍቻ፣ ሽማግሌዎችን በመጠቀም ለመፍታት የሚደረግ ሁኔታ አለ። ይህ መልካም ነው። ግን ችግሮች ከመሰረቱ ሳይፈቱ የሚደረግ ዕርቅ ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም። ግጭት ያስነሱ አካላት በህግ ሊጠየቁ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን የይስሙላ ዕርቅ ችግሩን በዘላቂነት አይፈታውም። በመሆኑም መንግሥት ይህንን ክፍተት ማየት ይገባዋል።

አቶ አስቻለውም በበኩላቸው፤ አሁን እየተስተዋለ ያለውን ችግር በመቅረፍ ረገድ መንግሥት ከፍተኛውን ሚና መጫወት እንዳለበት ያምናሉ። ሕግና ሥርዓት እንዲከበር በማድረግ ሰላምን ማስፈንና የሕዝቡን ደህንነት ማረጋገጥ፣ ፀጥታን በማስከበርና ስርዓት አልበኝነትን በማጥፋት ሰላምን የማረጋገጥ ተልዕኮው የላቀ ነው ይላሉ። የዴሞክራሲ ተቋማት ሚና ህብረተሰቡ የውይይት ባህል እንዲያዳብሩና ችግሮችን በሰለጠነና በሰከነ መንገድ በንግግር መፍታት እንዲችሉ የበኩላቸውን ሚና መጫወት አለባቸው።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች፣ ቋንቋዎችና ማንነቶች ያሏቸው የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች የሚገኙባት አገር ናት የሚሉት አቶ አስቻለው፤ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት ይላሉ። የባህላዊ ተቋማት ሕብረተሰቡ በጊዜ ሂደት የገነባቸው ባህላዊ አሰራሮችና እሴቶች ናቸው። የጋሞ ብሄረሰብ የሚያጋጥሙትን ግጭቶች እና አለመግባባቶች የሚፈታበት ለሌላው ማህበረሰብ ተምሳሌት ሊሆን የሚችል "ቱጌ" የሚባል ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት አለው። በሲዳማ ብሔረሰብ ግጭቶች ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንዴት እንደሚፈቱና እነዚህንም ግጭቶች የሚፈቱ አካላትን እንደ አይዱ ሶንጎ" የቤተሰብ ጉባኤ፣ "ጭናንች ሶንጎ" የቤተዘመድ ጉባኤ፣ "ኦላ ሶንጎ" የመንደር ጉባኤ እና "ሞቴ ሰንጎ" የጎሣ ሽንጎዎች አሉ። በሀላባ ብሔር ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ችግር የሚፈታው ተቋም 'ኦገቴ' ሲሆን በየደረጃቸው ግን 'ቦኪ አገቴ' የቤተሠብ ሸንጎ፣ 'ዶቦ አገቴ' /የጎሳ ሸንጎ/ና 'ሀላቢ ኦገቴ' (የሀላባ ሸንጎ) በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ ለአብነት የጠቃቀስናቸው ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች እንጂ አገራችን በርካታ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ እንዳላት ልብ ይሏል።

የሃይማኖት ተቋማትም ቢሆኑ ከመንግሥት ባልተናነሰ መልኩ በሕዝቦች መካከል እርቅ እንዲፈጠር እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ አካላት እንደመሆናቸው መጠቀም ያስፈልጋል ይላሉ አቶ አስቻለው። እነዚህ ተቋማት በስራቸው ያለውን ተከታይ ስለ ሰላም ስለአብሮነትና ስለመቻቻል በማስተማር ረገድ በህዝቦች መካከል ግጭት እንዳይፈጠር የማድረግ አቅማቸው የጎላ ነው።

ሚዲያም ለበጎ ዓላማ ከዋለ የመቻቻልና አብሮ የመኖር እሴትን በማጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፤ ዋነኛ የእርቅ መሳሪያም ይሆናል። በእውነታ ላይ የተመሠረቱ የሕዝቦችን አዎንታዊ ግንኙነት የሚያጎሉ፣ እርቅን የሚሰብኩ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ከሚዲያ ይጠበቃል። ከእዚህ ውጪ በሆነ መንገድ በህዝቦች መካከል መቃቃርን የሚሰብኩና ልዩነት ላይ አተኩረው የሚሰሩ ከሆነ ግን በሩዋንዳ እንደታየው ሁሉ አገር ሊያፈርሱ የዘር ግጭትን ሊቀሰቅሱ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩ ልብ ሊባል ይገባል ይላሉ።

መንግሥት ሰላምን ለማስፈን በአንድ በኩል የአገሪቱ ወቅታዊ ችግር መሆኑን በመገንዘብ ከእዚህ ቀደም ያልነበረውን የሰላም ሚኒስቴርን ከማቋቋም ጀምሮ ሌሎች እርምጃዎች እየወሰደ ይገኛል የሚሉት ዶክተር ሲሳይ መንግስቴ፤ ሂደቱ አበረታች መሆኑን ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ ከችግሩ ይዘትና ስፋት አንጻር ሲታይ አሁንም ገና ብዙ የሚቀር የቤት ስራ አለ፡፡ በተለይም የጸጥታ አካላት አቅማቸው እየተፈተነ ይገኛል ሲሉ ያመለክታሉ። የጸጥታና የደህንነት መዋቅሩ ግጭቶች ታቅደውና ተቀነባብረው እስከሚፈጸሙ ከመረጃ ውጪ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። በአንድ አገር ውስጥ የጸጥታና የደህንነት መዋቅሩ ዋና ዓላማ ችግር ከተከሰተ በኋላ መድረስ አይደለም። አደጋ ከመከሰቱ በፊት የሰው ህይወት ሳይጠፋ፣ ንብረት ሳይወድምና መፈናቀሎች ሳይከሰቱ ደርሶ የሚያከሽፍበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። አንዳንድ ችግሮች እየተፈጠሩ ያሉት መንግሥት የለም በሚያስብል ሁኔታ ነው። በመሆኑም መንግሥት በሚፈለገው ደረጃ እየሰራ ነው ብሎ ለማለት ያስቸግራል።

መንግሥት የህግ የበላይነትን ለማስከበር በሰራው ሥራ አፈናቃይ ተጠርጣሪዎች ጉዳያቸው ተጣርቶ ግማሾቹ በቁጥጥር ስር ማዋሉ መልካም ነው። ግን ተጠያቂነት፣ የህግ የበላይነት አለ፣ ፍትህ ሰፍኗል የሚባለው ተጠርጣሪ ወንጀለኞች በህግ አግባብ ተመርምረው ፍትህ ሲሰጥ ነው። አሁን የህግ ሂደቱ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ እንደመሆኑ ምንም ማለት አይቻልም። ግን ሂደቱ ለፖለቲካ ፍጆታ መዋል የለበትም። ቀድሞ የነበሩ አሰራሮች መደገም የለባቸውም። እንደቀድሞው በተለያዩ ምክንያቶች ውሳኔ ሳያገኙ የሚቆይበት፣ የሚፈቱበትና ሌሎች ምክንያቶች

የሚገጥሙበት ሁኔታ መደገም የለበትም። አሁን ስላለው ገና በውል ባይታወቅም ፍርድ ቤቶች ነጻ መሆናቸውና ፍትህን ማስፈን መቻሉን የማረጋገጥ ጉዳይ ትኩረት ያሻዋል ይላሉ ዶክተር ሲሳይ።

የመንግሥት አካላት በህግ የበላይነት ካልተጉ አሳሳቢነቱን ከፍ ያደርገዋል። የሰላም ሚኒስቴር በርካቶች መጠየቃቸውን ገልጿል፤ ግን ብዙዎች በጥርጣሬ ይመለከቱታል። በመሆኑም፤ በነጻ አካላት መረጋገጥ አለበት። በትክክል ለፍትህ እየቀረቡ ስለመሆናቸው ተጨባጭ ማሳያ ካልቀረበ አስቸጋሪ ነው፤ በሚባለው ደረጃ 50 በመቶ ተጠያቂ ማድረጋቸው አጠያያቂ ነው። ካደረጉ ጥሩ ነው። ካልሆነ ግን በትኩረት መስራት ይገባዋል። ይህ አንድ መንግሥት እየተፈተነ ያለበት ነው፤ እንደ ዶክተሩ አገላለጽ።

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግጭት ቀድሞ የመተንበይና መከላከል የመንግሥት ድክመት አለበት፤ ይላሉ መምህር አባይ፤ አሁን እየተፈጠሩ ያሉ ግጭቶች የመንግሥት አካላት መረጃ እንዳላቸው በመግለጫዎችና በዘገባዎች ላይ ይገለጻል። ይህ የግጭት መከላከል ስርዓቱ ክፍተት እንዳለበት ያሳያል።

የአደጋ መከላከል ሥራው ስኬታማ እንዲሆን አካታች የግጭት መከላከል ስልት ቢተገበር ይሻላል። የችግሮችን ደረጃ በየጊዜው መረጃ በመሰብሰብ፣ በመፈተሽና በመተንተን መፈጠርና አለመፈጠራቸውን በማረጋገጥ፣ የመፈጠር ዕድል ካላቸው ቀድሞ የመከላከል ዘዴ መደራጀት ይገባዋል። ችግሮች የመፈጠር ዕድል አላቸው ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ በአካባቢው ያሉ አገር በቀል የችግር መፍቻ መንገዶችን በመተግበር መፍታት ያስፈልጋል።

በአገር በቀል የችግር መፍቻ መንገዶች ማስቆም ካልተቻለ ደግሞ መንግሥት ባሉት መዋቅሮቹ ግጭቶቹ እንዳይከሰቱ ማድረግ ያስፈልገዋል። የግጭት መከላከል ላይ ያለው ችግር የደህንነት ስጋት መኖሩ ከተደረሰበት በኋላ ውሳኔ የመስጠት ውስንነት አለ። ሌላው አደጋው ባልታሰበበት ጊዜ ሊከሰት ይችላል። ያለውን ጊዜ ተጠቅሞ ግጭት መከላከል ላይ ያለውን ክፍተት ማስተካከል ይገባል። ግጭት ከተፈጠረ በኋላ እየጨመረና እየባሰ ይሄዳል። ከግጭት በኋላ ደግሞ ሁኔታውን መፍታት ከባድ ይሆናል። በመሆኑም እዚህ ደረጃ ላይ ሳይደረስ ግጭትን ቀድሞ መከላከል ላይ መስራት ያስፈልጋልም ይላሉ።

የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ የመንግሥት መሰረታዊ ግዴታ ነው። ዜጎች ከመንግሥት የሚጠብቁት መሰረታዊ አገልግሎት ቢኖር ሰላምና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ነው። ከዚህ አኳያ በየደረጃው የሚገኘው የመንግሥት አካል የተናበበ፣ ቁርጠኛ የሆነ፣ ከግል ፍላጎት የዘለለ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባዋል።

የህግ የበላይነትን በትክክል ማስከበር ካልተቻለ የሁከት ሃይሎች በተግባራቸው መቀጠላቸው አይቀርም። ለግጭት አስጊ የሆኑ አካባቢዎችን ለይቶ መስራትም ያስፈልጋል። በተለይ ኩታ ገጠም የሆኑ አካባቢዎች ላይ የሰላም ግንባታና የአብሮነት ሥራ መሰራት አለበት ይላሉ መምህሩ።

ልዩነቶች የሰላም ምንጮች እንጂ የጠብና ግጭት መንስኤ ሊሆኑ አይገባም፤ ይህንን እሴት በአግባቡ መንከባከብ ይገባል። «መቻቻል ብዝሃነትን ማክበር፣ መቀበልና ማድነቅ ማለት ነው።» ይህም በእውቀት፣ በግልጽነት፣ በመነጋገር እንዲሁም በማሰብ፣ በህሊናና በእምነት ነፃነት የሚጎለብት ነው። መቻቻል በልዩነት ውስጥ ያለ ስምምነት ነው።

መቻቻል ከራስ የተለየን ሃሳብ እንዲደመጥ መፍቀድ ወይም ከራስ የተለየን ሃሳብ በምክንያት መደገፍ ወይም መቃወምን ያመለክታል። የመቻቻል ባህል ለሰላም ቁልፍ አስተዋጽኦ ያበረክታል፤ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ግልፅና እውነተኛ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ያግዛል። የመከባበር እና የመተሳሰብ ባህል ስር-እንዲሰድና እንዲዳብር፤ አለመግባባቶችና ግጭቶች

እንዳይከሰቱ አስቀድሞ ለመከላከል ይረዳል ባይ ናቸው ዶክተር ሲሳይ፡፡

## *በግጭት አፈታት ዙሪያ የመሪው ድርጅት የመንግስት ሚና*

ለውጡ ያመጣውን ትሩፋት በመጠቀም ወይም የለውጡ ማዕከል የሆነውን የዴሞክራሲ ምህዳር የማስፋት ዕድል ተጠቅሞ አንዳንድ አዳዲስ የሚዲያ ተቋማትን የከፈቱ፣ በብዙ መልኩ ሚያስቧቸውን ነገሮች ማስተላለፍ የሚፈልጉ አክቲቪስቶች፣ ጦማሪያንና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ለውጡን በበለጠ መንገድ የሚያጠናክር ሳይሆን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ጥላቻና ግጭትን ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ነገሮች፤ ሰላምን ሊያደፈርሱ የሚችሉ የሀሰት መረጃዎችን የሚሰብኩና የሚያሰራጩ ሰዎች ከፍተኛ ውዥንብርና አሉባልታ በተለይ ደግሞ በማህበራዊ ሚዲያ ተጠቅመው እዚህች አገር ብጥብጥ እንዲሰፍን እየሰሩ መሆኑን የአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ጓድ ተስፋዬ በልጅጌ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ አውስተዋል፡፡

እነዚህ አካላት ለማንም ሳይሆን ለአገራችን፣ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ሲባል ጥሩ አገር እንዲኖረን በእጃቸው የሚገኘውን ሃብት መጠቀም ያለባቸው ለገንቢ ተግባር መሆን እንደአለበትም ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡ ‹‹መንግስትን መተቸት፣ አመራሩን ሂስ ማድረግ ማለት አሉባልታ፣ ውዥንብርና በሬ ወለደ የሆኑ የሃሰት መረጃዎችን ማሰራጨት ብሎም ዜጎችን ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬ ማፈናቀል ማለት አይደለም›› ያሉት ጓዱ፤ ይሄም የራሱ የሆነ ህግና ገደብ እንደአለው ያስገነዝባሉ፡፡

‹‹ለውጡ ያመጣቸውን ትሩፋቶች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይጠቀማሉ›› ያሉት ጓድ ተስፋዬ አንዳንዶቹ ግን በተዛባና ባልተገባ መንገድ በመስራት ለውጡ እንዲቀለበስ እንቅፋት እየሆኑ ስለሆነ መታረም ይገባቸዋል ሲሉ በአጽንኦት አስገንዝበዋል፡፡

እንደ አንድ አገር የሚመራ ፓርቲ የአገርን ሰላምና ልማት እንዲሁም ዴሞክራሲን ከማጎልበት በላይ ሌላ አጀንዳ የለንም፡፡ ከእዚህ ውጪ የሚንቀሳቀሱና ጽንፈኛ ብሄርተኝነትን፣ ዘረኝነትን፣ ውዥንብርን፣ አሉባልታን መነሻ አድርገው ወደ ግጭት የሚሄዱ ለዚህም መሳካት የሚሰሩና የሚሰብኩ አንዳንዴ ደግሞ ጥቃት የሚፈጽሙ ኃይሎች ከእዚህ ድርጊታቸው ይቆጠባሉ በሚል በማዕከላዊ መንግስት ጭምር ጥሪ ተላልፏል፡፡ ለውጡ ያመጣው ትሩፋት ተጠቅመው ተመልሰው የሚያደናቅፍ ስራ ከመስራት ሊቆጠቡ እንደሚገባም አውስተዋል፡፡ ከእዚህ ውጪ የሚፈጠሩ ችግሮችን ድርጅቱ በቸልታ እንደማይመለከታቸውም አስገንዝበዋል፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ ጓድ መለሰ ዓለሙ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በድርጅቱ የውህደት ጉዞ ዙሪያ ቆይታ ባደረጉበት ወቅት የፓርቲውን ውህደት ፖለቲካዊ አንድምታውንና ፋይዳውን ሲያስረዱ የመጀመሪያው አሁን በአገራችን ውስጥ እየታየ ያለውን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ መነሻ በማድረግ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ፖለቲካ ነክ የሆኑ ችግሮች ሲከሰቱ መቆየታቸውንና እነዚህን ችግሮች ከመቅረፍም አንጻር ኢህአዴግ በእራሱ የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ ለመፍታት ጥረት ሲያደርግ መቆቱን ያስረዳሉ፡፡ አሁን ባለንበት የለውጥ ሂደት ውስጥም ያለው የፖለቲካ ችግር አንዱና ዋነኛው የጽንፈኛ ብሔርተኝነት መሆኑንና ይህንንና ከእዚህ ጋር የሚያያዙ ችግሮችን ለመቅረፍ ዋነኛው ድርሻ የመላው የአገራችን ህዝቦች መሆኑን የጠቆሙት ጓድ መለሰ የፓርቲው መዋሃድም መፍትሄ እንደሚሆን ያላቸውን እምነት አስቀምጠዋል፡፡

ብልፅግና እንደ ድርጅት በአገሪቱ የሚታዩ ችግሮችን መፍታት የሚያስችለው የእራሱ የፖለቲካ ሪፎርም እያደረገ ነው፡፡ ከእዚህ አንጻር እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ሪፎርሙ ለአገራችን የፖለቲካ ችግሮች መፍትሄ የመስጠት አቅም አለው፡፡ ምክንያቱም ብልፅግና አንዱ

በአገራችን የአስተዳደር ስርዓት ልምድ ያለው ፓርቲ በመሆኑና ይህም ትልቅ ሚና የሚኖረው በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው ድርጅቱ መሪ ፓርቲ ነው፡፡ ስለዚህ የመንግስትንም ኃላፊነት ይዞ የሚሰራ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን ተጽእኖ የማሳረፍ አቅሙን ተጠቅሞ የአገሪቱን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

እነዚህ ተደምረው ነው ለሚስተዋሉ ቀውሶች ሁሉ ፍቱን መድኃኒት መሆን የሚችሉት፡፡ ከእዚህ አኳያ የብልፅግና ሪፎርም ጉዳይ እንደ አንድ ፓርቲ ሳይሆን እንደ መሪ ፓርቲ በውስጡ የሚያደርገው ሪፎርም በድርጅቱ ውስጥ የሚቀር ብቻ ሳይሆን በህዝቡ ውስጥ የሚታየውን የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ በማገዝና ለስርዓቱ ግንባታ የተመቸ ሁኔታ ለመፍጠር የእራሱ ሁኔታ ስለሚኖረው በየአካባቢው የሚስተዋሉ ግጭቶችንም ሆነ ሌሎች ፖለቲካዊ ችግሮች ከመፍታ ከፍተኛ ሚናም እንዳለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

በህዝብ ይሁንታ የተሰጠውና አገሪቱን በማስተዳደር ላይ የሚገኘው መንግስትም ከግጭት አፈታት ጋር ቁርኘት ያላቸውን መዋቅራዊ አደረጃጀቶች በመፈተሽና በማስተካከል ከምሁራን ጋር እንዲቀራረቡ የማድረግ ኃላፊነቱን አጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡ በምሁራን የሚፈልቁ አማራጮችና የመፍትሔ ሃሳቦችን በመመርመርና በመረዳት በአገር ውስጥ ለሚታዩ ግጭቶች ማቆሚያ እንደ መሳሪያነት መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ምሁራን የሚደመጡበት፣ በነጻነት የሚወያዩበት፣ ሃሳባቸውን በነጻነት የሚያራምዱበት አውድ የማስፋት ጥራቱን ማጎልበት ይገባዋል፡፡

## *በግጭት አፈታት ዙሪያ የምሁራን ሚና*

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግና አስተዳደር ኮሌጅ የሰብዓዊ መብትና ፌደራሊዝም ረዳት ፕሮፌሰሩ ዶክተር ሲሳይ መንግስቴ በአንድ አገር የፖለቲካ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የምሁራን ሚና ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ምሁራን ለልማት የሚጠቅሙ ሐሳቦችን በማመንጨት ረገድ የላቀ ሚና የሚኖራቸው ሲሆን፣ በተለይ ከሌላው ኅብረተሰብ በላቀ ደረጃ እውነት በመናገር ሐሰትን ሊያጋልጡ፣ ዕውቀትን አክብረው ሊያስከብሩና ለምሁርነታቸው ታማኝ ሊሆኑ፣ ራሳቸውን ለውይይትና ጥያቄ ክፍት ሊያደርጉ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ ‹‹እንዳለመታደል ሆኖ አገራችን ባለፈው ሩብ ክፍለ ዘመን የሚሻገር ጊዜ የአደባባይ ምሁራንን አላፈራችም፡፡›› የሚሉት ዶክተር ሲሳይ፣ ከእዚያ ትውልድ የተሻገሩትም ቢሆን በጣት የሚቆጠሩ መሆናቸውን ያወሳሉ፡፡

ጋናዊው ፕሮፌሰር ጆርጅ አይቲ ምሁራንን በሁለት እንደሚከፍሏቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ‹ቅምጥ ምሁራን› እና የአደባባይ ምሁራን በሚል በፕሮፌሰሩ አተያይ የእኛ ሀገር አንዳንድ ቅምጥ ምሁራን ወደ ስርዓተ መንግስቱ በመጠጋት “አለባብሰው ቢያርሱ…” አይነት ምሁራዊ ትንታኔ ሲሰጡ የኖሩ ናቸውና እነርሱ የለውጡ እንቅፋት ከመሆን ተሻግረው ረብ ያለው ሚና የሚጫወቱ ናቸው ማለት የሚቻል አይመስለኝም፡፡

ምሁራን የሚሳተፉባቸው መድረኮች መስፋት እንደአለባቸው ይጠቁማሉ፡፡ በአገሪቷ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ሙያው ያላቸው ምሁራን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ እንደ ምሁር በጥናት ላይ ተመስርተው ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሃሳብ አመንጭተው በእዚህ መልኩ ‹ብንሄድ› ብለው መደገፍ አለባቸው፡፡ ያደጉት አገራት ለእዚህ የደረሱት በሃሳብ አመንጪ ምሁራን ነው፡፡ የሚያስቡ፣ የሚፅፉ፣ ስትራቴጂ የሚነድፉ ብዙ ሰዎች ያሏቸው አገሮች አድገዋል፡፡ ስለዚህ የአገሪቷን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን በሚመለከት የመጣነው እንዴት ነው? ወደፊት እንዴት እንራመድ? ብለው አጥንተው ተከራክረው በሳይንሱ በሙያው በሃሳብ ተከራክረው በጎ ነገርን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ለዛ የሚመች መድረክንም ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

እንደ ዶክተር ሲሳይ ገለጻ፣ ምሁራን ምክንያታዊ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ አንድ ምሁር ይህ

ትክክል አይደለም ብሎ ሲተች ትክክል መሆን ያለበት ጉዳይ የትኛው እንደሆነ መግለፅ እንጂ እርሱ የወጣበትን አካባቢ ከሌላው አካባቢ፤ ማህበረሰቡንና ክልሉን የሚያተራምስ መላ ምት ማቅረብ የለበትም:: ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ ይጠበቅበታል:: ሌሎች ስሜታዊ ሲሆኑ፤ ምላሽ በመስጠት መመለስ ያለባቸው ምሁራን ናቸው:: ይህ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ ተመራማሪዎችን እና ሌሎች ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ምሁራንን ሁሉ ይመለከታል፡፡

አሁን አሁን እየታየ ያለው ግን አንዳንድ ምሁራን በጥናትና ምርምር ሰበብ ታሪክ ሲያዛቡ፤ ወደእራሳቸው አካባቢና ጎጥ እየተሸጎጡ ህዝብን ሲያጋጩ፤በየአካባቢው ለሚከሰቱ ግጭቶች እልባት የሚሆኑ ፍቱን መፍትሄዎችን ከማመንጨት ይልቅ ነዳጅ ሲያርከፈክፉ ይስተዋላል፡፡ ይህ ደግሞ አገርና ህዝብን ከማፍረስ የዘለለ ምንም አይነት ፋይዳ ለእራሱ ለምሁሩም ሆነ ለሚጠቅሰው አካባቢ የለውም፡፡ በመሆኑም ምሁራን በሰከነ መንፈስ በመንቀሳቀስ አገራዊ አንድነትን በሚያጎለብቱ ጉዳዮች ላይ መሰማራት አለባቸው የዶክተር ሲሳይ መንግስቴ መልዕክትና ማሳሰቢያ ነው፡፡

መምህር አባይ ይመር በበኩላቸው በስራ ላይ ያለው ህገ መንግስት በህግ ደረጃ በርካታ ጥሩ ጎኖች እንደአሉት ጠቅሰው ስለሰብዓዊ መብትም ሆነ ስለ ህዝብ ሉዓላዊነት ብዙ ቁምነገሮችን ያካተተ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ችግሩ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ እነዚህንና መሰሎቹን ወደተግባር መመንዘር አለመቻል ላይ ነው፡፡

አንዳንድ የማያስፈልጉ አንቀፆች ደግሞ ሊኖሩ ይችላሉና እነዚህም ላይ በስፋት ህብረተሰቡ፣ የኃይማኖት ተቋማትም ሆኑ የግሉ ዘርፍ፣ እድሮችና ሌሎችም ሁሉ በተወካዮቻቸው አማካይነት አንጥረው አውጥተው ይህን ጉዳይ በድጋሚ ‹እንወያይበት› በማለት ብሄራዊ መግባባት ላይ መድረስ ይኖርባቸዋል፡፡ ልማት ለማካሄድ፣ ህብረተሰቡ የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖር ለማድረግ፣ የጋራ እሴቶቻችንን አጠንክረን ወደፊት ለመሄድ፣ ልዩነቶቻችንን ለመፍታት፣ የአገራችንን ዋና ዋና ችግሮች ለመፍታት በመጀመሪያ በአገራችን ውስጥ ሰላም ሊኖር ይገባል፡፡ በመሆኑም ለሰላም ቅድሚያ መስጠት ተቀዳሚው ጉዳይ ነው፡፡

ምሁራን የዕምነትም ሆነ የማንነት ጽንፈኝነት አራማጅ ወይንም አራጋቢ ሳይሆኑ መፍትሔ አፍላቂና ሰጪ መሆን አለባቸው፡፡ ሌሎች የእውቀትም ሆነ መድረኩን የማግኘት ችግር እንደአለባቸው አካላት በተለያዩ ግፊቶች በስሜት መነዳት ሳይሆን እውነትና እውቀትን አዳብለው ጤናማ እልባትን የሚያበረክቱ መሆን አለባቸው፡፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ ምሁራን ድምጻቸውን የሚያሰሙበት ምቹና አንጻራዊ ነጻነት በአገራችን በመኖሩ የለውጡ እንቅፋቶችን የሚያመክኑና የሚያደክሙ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## በግጭት አፈታት ዙሪያ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ሚና

በአገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እራሳቸውን ሁልጊዜም በተፎካካሪነት ከማሰብ አባዜ አውጥተው አገራዊ ለሆነው የዴሞክራሲ ግንባታ ስርዓት መሳለጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጊዜውን የምሁራን የዕውቀት የብስለት የመፍትሄ እንዲያደርጉ በቁርጠኝነት መስራት አለባቸው፡፡

ምሁራንን ከሚነቅፉ የፍረጃ አስተሳሰቦች በመላቀቅ ወደ እነሱ በማቅረብ እወቀታቸውንና ምርምራቸውን ለፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው አጋዥ አድርገው መጠቀም ይገባቸዋል፡፡ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግጭትን ከሚቀሰቅሱ እንቅስቃሴዎች መታቀብና መቆጠብ የመጀመሪያ ግዴታቸው ሲሆን ለግጭት ከሚሰሩ ማናቸውም አካላት ጋር በጋራ ከመንቀሳቀስ መቆጠብም አለባቸው፡፡

## *ማጠቃለያ*

ኢትዮጵያ ከተያያዘችው የመደመርና ይቅርታ ለውጥ ጎን ለጎን አሳሳቢ የሆኑ አካባቢያዊ ግጭቶችም ተከስተውባታል፡፡ እነዚህ ግጭቶች የብዙ ዜጎች ሕይወት አካልና ሥነ ልቦና ላይ ጉዳቶችን ከማድረሳቸው በተጨማሪ፣ በላባቸው ጥረው ግረው ያፈሩትን ንብረት ለዘረፋና ውድመት በማጋለጥና ረጅም ጊዜ ከሚኖሩበት አካባቢ በማፈናቀል ከፍተኛ የሆነ ማኀበራዊ ቀውስ ማስከተላቸውም ይታወቃል፡፡ የለውጥ አመራሩ ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ አንስቶ በወሰዳቸው የእርምት እርምጃዎች መልካም የሚባሉ ጅምር ተግባራትን የከወነ ቢሆንም እዚህም እዚያም የሚስተዋሉ ግጭቶችን መፍታት ላይ ተጨማሪ ርብርብ ያሻዋል፡፡

የተያዘው የመደመርና የይቅርታ ለውጥ በአብዛኛው ኀብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ የተቸረውና በአገሪቱ መፃኢ ዕድል ላይ አዎንታዊ ተስፋ ያሳደረ ከመሆን አልፎ በጎረቤትና በልማት አጋር አገሮች እንዲሁም፣ በዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ድርጅቶች ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፈ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የለውጡ እንቅስቃሴ በአገራችን የፖለቲካ መረጋጋት እንዲሠፍን፣ እንዲሁም የማኀበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ዕውን እንዲሆን ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ ከመገንዘብ የመነጨ ነው፡፡

ከእዚህ በተቃራኒ ለውጡን በሕዝበኝነት የሚነዳና ፋይዳ ቢስ እንደሆነ በመፈረጅ በጥርጣሬ የሚመለከቱና የሚቃወሙ ጥቂት አካላት መኖራቸው የሚካድ አይደለም፡፡ ሆኖም ምንም እንኳ የማይፈለግ ቢሆንም፣ በማንኛውም ለውጥ እንቅስቃሴ ጥርጣሬና ተቃውሞ የሚጠበቅና ሊያጋጥም የሚችል በመሆኑ፣ በለውጡ ትግበራ የሌሎችን ሥጋትና ጥርጣሬ ለመቅረፍና በአጋርነት እንዲሠለፉ ለማስቻል በለውጥ አመራሩ በኩል ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶች መንስዔዎችን በውል መገንዘብ፣ ውጤታማ ለሆነ የግጭት አፈታት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን የተከሰቱ የአካባቢ ግጭቶች መንስዔዎች ፈርጀ ብዙና ውስብስብ ናቸው፡፡

በአገራችን ሺ ዓመታትን ለዘለሉ ጊዜያት ማህበረሰቦች በተለያዩ ሁኔታዎች አንድ ላይ ተሰብስበው መንግስት ሲመሰርቱ ኖረዋል፡፡ ልዩነቶች እንዳሉ ሁሉ አንድ የሚያደርጉን ደግሞ ዕልፍ ዕሴቶችም አሉን፡፡ የአገረ መንግስት ግንባታን ከበርካታ ዓመታት በፊት የጀመሩ አገራት እስካሁንም ድረስ አላጠናቀቁትም፡፡ በአንድ ጀምበር ተጀምሮ የሚጠናቀቅ አይደለም፡፡ ስለሆነም ስራው እየጎለበተ የሚሄድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እኛ ግን ኢትዮጵያን የመገንባት ፕሮጀክት ይዘን ወደፊት መንቀሳቀስ ጀምረናል፡፡ የሚቀሩን ነገሮች ደግሞ አሉ፡፡ እነዚህን የቤት ስራዎቻችንን ተጋግዘንና ተደጋግፈን ማሟላት እንጂ በውሃ ቀጠነ መነሾ መጋጨት የለብንም፡፡

ግንባታው ከእኛ በኋላ የሚመጡ በርካታ ትውልዶችንም ትጋት ይጠይቃልና በየፌርማታው ከሚያሰናክሉ ጉዳዮች ተቆጥበን በትክክለኛው ሃዲድ ላይ እንዲጓዝ እድል እንስጠው፡፡ አንዳንድ ወገኖች ‹‹በብሄር መብት ላይ ብቻ በትኩረት መሰራቱ በራሱ አሉታዊ ነው፡፡ ችግር ያመጣል በየአካባቢው ለሚስተዋሉ ግጭቶችና ውድመቶች መንስኤው ይሄ ነው›› ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ‹‹አሁንም ቢሆን ለብሄረሰቦች መብት እውቅና ሰጥቶ ይህን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ነገሮች አሟልቶ መሄዱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው›› ይላሉ፡፡ እንደ ዓውደ ለውጥ ዝግጅት ክፍል እይታ ግን ሁለቱም አተያይ የሚጋጭ አይመስለንም፡፡ የኢትዮጵያዊነትም ሆነ የብሄረሰቦች መብት ግንባታ አዳኝና ታዳኝ፣ በይና ተበይ የሌለው ተመጋጋቢ፤ አንዱ ለአንዱ ብርታትና ጤንነት፣ በድምሩም የልጆቿን እኩልነት የጠበቀች፤ የዳበረ ዴሞክራሲና ኢኮኖሚ የገነባች እናት አገር፣ ብዝሃነቷ ጉልበትና ግዝፈት የለገሳት በአህጉሩም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ጠንካራ ተወዳዳሪ አገር ትኖረን ዘንድ ሳናሰልስ ላባችንን እናፍስ ጉልበታችንን እንለግስ፡፡ የሚል መልዕክትም አለን!!፡፡



# ነጭ እና ጥቁር መንትያማቾች

ከነጭ አባትና የጃማይካ ክልስ ከሆነች እናት ነው የተወለዱት በአራስነታቸው የመጀመሪያዎቹ ሶስት እና አራት ወራት በእርግጥም የነጥብ ልዩነት ያልነበራቸው ከወራት በሁዋላ የሁለት አህጉር ህፃናት ሆነው አረፉት። አስኪላ ከጀመሩባት ቀን አንስቶ እነሆ 22ኛ ዓመታቸውም ላይ ለአያቸው ድንቅ እንደሆኑ ናቸው። “አንድ አይነት ለብሰን ብንታይም እንኳንስ መንትያነታችንን ዝምድና እንዳለን እንኳን ለማመን የሚቸገሩ አሉ የምትለን ነጯ ሉሲ “የማደጎ እህት እንደሆንኩ የጠየቁኝም አሉ” የአለችው አይኖቿ በእንባ ደፍርሰው ነው”

ጥቁሯ ማርያ እንዲህ ዓይነት የመንትያ ልዩነት ከሚሊዮን ጊዜ አንዴ እንደሚያጋጥም ነግረውኛል። ስትል ቢቢሲ ደግሞ ከ500 መንትያ በአንዱ የሚከሰት ማለቱንም ታስውሳለች። ልዩነቱም የራሱ ጉዳይ መንትያዎቹ ወጣቶች ግን በሆነው ሁሉ ደስተኞች ናቸው። ሉሲም ይህንኑ እንዲህ ገልፃዋለች “ማርያ በኮሌጅ ቆይታዋ ነጭ መንትያ እህት እንዳለሁዋት መግለፅ ትወዳለች። በጥቁር መንትያዬ ከፍተኛ ኩራትና ክብር ይሰማኛል”

**“ሴቶች በኢኮኖሚ ሴቶች በሳይንስ ሴቶች በፖለቲካ ከወንዶች እኩል ካለከልካይ መድረስ የሚገባቸው ስፍራ እንዲደርሱ እያሳዩ እያጓጓ የማያደርሰውንም ጋራ ከልሎ ያቆመውንም በመናድ ሴቶች በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ ከወንዶች የሚስተካከሉበትን መንገድ ለመፍጠር ብልፅግና አበክሮ ይሰራል፡፡”**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ

# ከቅርብ ያልመሰሰ እረኛ ሊሮጥ ይውሳል!

አብይ ጾምንና ሮመዳንን በጋራ የሚፆሙ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች ያሉባት የመቻቻል ምድር፡፡ ከ97 በላይ ህዝቦቿ ሀይማኖተኛ የሆኑባት ተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ፈጣሪም ‹‹ያዳላባት›› ድንቅ አገር ናት ኢትዮጵያ፡፡ በመፅሀፍ ቅዱስ ከ40 ጊዜ በላይ ስሟ የተጠቀሰ፣ በቅዱስ ቁራንም ነብዩ ሙሀመድ ስለ ታላቅነቷ የመሰከረላት ቀደምት አገር፡፡

ሙስሊሞች በራሳቸው ተነሳሽነት ቤተክርስቲያን ይገነባሉ፡፡ ክርስቲያኖች እንደ ራሳቸው የእምነት ተቋም ሆ ብለው መስጊድ ይሰራሉ፡፡ ይህ ሁነት በኢትዮጵያችን ከጥንትም የነበረ ያለና የሚኖር ነው፡፡ የበኩር ልጁን ለመዳር ቀናት እንደ ዓመታት የሚረዝሙበት የሙስሊም ቤተሰብ 55ቱን የአብይ ፆም ቀናት ታግሶ ከክርስቲያን ወንድም እህቶቹ ጋር ደስታውን ለመካፈል ሲወስን በደስታ ነው፡፡ ለበዓላት ድግስ ሰንጋ የጣለ የክርስትና እምነት ተከታይ ቤተሰብ ለእስልምና እምነት ተከታይ ጎረቤቶቹ ቢያንስ በግ ወይም ፍየል ጆባ ለማለት አይሰስትም፡፡

እስልምናና ክርስትና የራሳቸው የሆነ የእምነቱ አስተምህሮ እሁድና ሰንበት እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ግን አጥር ሆኖ ዜጎችን የሚያራርቅ አይደለም፡፡ እንዴውም ሀይማኖተኛ ህዝብ መሆናቸው አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለው በትህትና ተከባብረው ለመኖር አስችሏቸዋል፡፡

በአንድ ቤት ውስጥ ሙስሊሙም ክርስቲያኑም እንደየእምነታቸው ፈጣሪያቸውን የሚያወድሱበት፣ የሚማፀኑበት፣ የሁለቱንም በዓላት በደስታ የሚያሳልፉበት ሁነት ለዓለም እያስደመመ ዘመናትን የተሻገረ የኢትዮጵያውያን የጋራ እሴት ነው፡፡

በአገር ላይ የተቃጣን ፈተና ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በአንድነት በመትመም የጋራ ገድል ፈፅመው የጋራ ታሪክ ፅፈዋል፡፡ ለዚህም አይደል ተዋድዶ መኖርን ብቻም ሳይሆን እንደተዋደዱ መሞትንም ኢትዮጵያውያን ከአበው የወረሱት ሀይማኖታዊ እሴት ነው የሚባለው፡፡ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁንም ‹‹ተዋዶ ያለበት እስላም ክርስቲያኑ ተዘነጋሽ እንዴ ኢትዮጵያ መሆኑ›› ሲል የተቀኘው የኢትዮጵያዊያንን ጥልቅ ሀይማኖታዊ የአብሮነት እሴት ለመግለፅ ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡

ራስን ለሌሎች አሳልፎ መስጠትን፣ መቻቻልን፣ መከባበርን፣ መረዳዳትን፣ መተዛዘንን፣ ይቅር መበባልን ሀይማኖቶች ይሰብካሉ፡፡ ለታላላቆች መታዘዝን፣ ህፃናትንና ሴቶችን ማክበርንም የእስልምናውም የክርስትናውም አስተምሮ አፅንኦት ይሰጣል፡፡ ሰውን ብቻም ሳይሆን እንስሳትን፣ እፅዋትንና ሌሎችንም ፍጥረታት መንከባከብንና መጠበቅን ሀይማኖቶች ዘወትር ያስተምራሉ፡፡

ኢትዮጵያውያኑ ይበልጥ ሀይማኖተኛ በሆኑ ቁጥር አይደለም ለሰው ልጅ ለመላው ፍጥረት የሚሰጡት ፍቅርና እንክብካቤ እጅግ ይጨምራል፡፡ ትክክለኛ አማኞች ከሰው ቢሰወሩ ከፈጣሪ መሰወር እንደማይቻል ይረዱታልና ምንግዜም ለመልካም ነገር ይተጋሉ፤ ለእውነት እና ለፍትህ መቆም እንዳለባቸው በማመንም በህይወት እስካሉ ድረስ በተግባር ይተረጉሙታል፡፡

ሰላምን እንጅ ጥልን የሚሰብክ ሀይማኖት የለም፡፡ ፍትህን እንጅ አድሎን የሚያስርፅ ሀይማኖታዊ አስተምህሮም ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እስልምናም እንበለው ክርስትና ተከታዮቻቸው የፈጣሪን ህግ እንዲያከብሩ በሚደነግገው አስተምህሯቸው የህግን የበላይነት ይሰብካሉ፡፡



ጥፋትን ወደ ሰላም እየቀየረ ያለው የጋሞዎች ነባር እሴት

ቅዱስ ቁራንም መፅሀፍ ቅዱስም ስለ ሞራል ህጎች እና ስለ መልካም ስነምግባር አብዝተው ያስተምራሉ፡፡

የሀይማኖት ተቋማት በግላቸው የሚያከናውኑት እንዳለ ሆኖ ለአገር ሰላም፣ ለህዝቦች አንድነት፣ ፍቅር እና መከባበር ተቀናጅተው ሊሰሩ ግድ ይላል፤ መቼስ ሀይማኖትን ማራመድ ከዜጎች ደህንነትና ከአገር ሰላም ተለይቶ አይታይ፡፡

የሀይማኖት ተቋማት በጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ በጋራ ለመረባረብ በኢትዮጵያ ደረጃ በ2003 ዓ.ም አገር አቀፍ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ መስርተዋል፡፡ በከተማችንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክርቤት፣ የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት ህብረት፣ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አዲስ አበባ አገረ ስብከት፣ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አዲስ አበባ ጽ/ቤት፣ የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ እየሱስ እና የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በጋራ የአዲስ አበባ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤን በመመስረት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በቅንጅት እየተረባረቡ ይገኛሉ፡፡

‹‹እንዲሆንልህ የምትፈልገውን ለሌሎችም አድርግ፣ እንዲደረግብህ የማትፈልገውን ለሌሎችም አታድርግ›› የሚለው የፈጣሪ ትዛዝ ነው፡፡ ቃሉ በመፅሀፍ ቅዱስም በቅዱስ ቁራንም መጠቀሱ የየትኛውም እምነት ተከታይ የሆነ ሀይማኖተኛ ሁሉ ለመልካም ተግባር እንዲተጋ ማሳያ መሆኑን የሚናገሩት የአዲስ አበባ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ ዋና ፀሀፊ መጋቢ ታምራት አበጋዝ በዚህም አንድ በሚያደርጓቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ እየተረባረቡ እንደሚገኙ ያመላክታሉ፡፡

የሀይማኖት ተቋማቱ የጋራ ጉባኤ በኢትዮጵያውያን መካከል ለዘመናት የዘለቁትን የአብሮነትና የመከባበር እሴቶችን በዜጎች ላይ በማስረፅ እንዳይሸረሸሩ መጠበቅን ዓላማው አድርጓል፡፡ ከዚህም ባለፈ ዘር ቀለም ሀይማኖት የማይለየውንና የበርካታ ዜጎቻችን ህይወት እየቀጠፈ የሚገኘውን ኤች አይ ቪ ኤድስን እንዲሁም በየጊዜው መርዶ የምንሰማበትን አስከፊውን ህገውጥ የሰዎች ዝውውር ለማስቀረት በጋራ ለመረባረብ የሀይማኖት ተቋማት በአንድነት ይመክራሉ፡፡

የአዲስ አበባ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ ዜጎች በከተማቸውና በአገራቸው ልማት ላይ ጉልህ አሻራቸውን እንዲያሳርፉም እያስተባበረ ይገኛል፡፡ ለአብነትም የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በዜጎች የተባበረ ክንድ እውን እንዲሆን የአዲስ አበባ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ የድርሻውን እየተወጣ እንደሚገኝ ይወሳል፡፡

አንድነት ሀይል ነው፡፡ መተባበርም ብርታት ነው፡፡ በመሆኑም ልዩነታቸውን ውበት አድርገው ለተሻለ ውጤታማነት ቢረባረቡ እንደሚያተርፉ ስለተገነዘቡ ተቋማቱ ተቀራርበው

ይሰራሉ፡፡ ‹‹በአስተዳደራዊ እና በአሰራር ጉዳዮች አንዱ የእምነት ተቋም ከሌላኛው ልምድ ይለዋወጣል፡፡ የተለያዩ ግጭቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱበትን አግባብ አንዱ ከአንዱ ልምድ ይቀስማል፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለወጣቶችና ለሴቶች ግንዛቤ ለማስጨበጥም ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያቤቶች ጋር ተቀናጅተው ይሰራሉ፡፡›› የሚሉት ዋና ፀሀፊው መጋቢ ታምራት ጉባኤውን ለማጠናከርም ሁሉም አብያተ እምነት የፋይናንስ ድጋፍ እንደሚያደርጉ አውግተውናል፡፡

ትንሽ ጉድፍ ትልቁን መልካም ነገር ስለምታደበዝዝ ከአሉታዊ አስተሳሰቦች ጋር ተደማምሮ ‹‹ኢትዮጵያ መስቀለኛ መንገድ ላይ ናት›› ማለት የተለመደ ሆኗል እንጅ ዜጎች በሀይማኖት፣ በብሔር፣ በቋንቋ እና በመሳሰሉት ልዩነቶች ቢኖሯቸውም ጌጦቻቸው አድርገው ተጋምደው ኖረዋል፤ እየኖሩም ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን የጠበቀ ማህበራዊ መስተጋብር ካላቸው ህዝቦች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ታዲያ በዚህ ማህበራዊ ህይወታቸው ብሔርህ ወይም ሀይማኖትህ ሳይባባሉ ደስታውንም ሀዘኑንም በጋራ ያሳልፋሉ፡፡

በከተማችን አዲስ አበባ ከ7ሺህ 500 በላይ እድሮች እንዳሉ የአዲስ አበባ እድሮች ሰብሳቢ አቶ ታምራት ገ/ማርያም ይናገራሉ፡፡ በዚህ የጠንካራ ማህበራዊ እሴታችን መገለጫ በሆነው ተቋም ነዋሪዎች ቋንቋ፣ ብሔር እና ባህል ሳይለያቸው ሰው መሆንን በማስቀደም ደስታቸውን ይጋራሉ፤ ሀዘናቸውንም ይካፈላሉ፡፡ እድር በሀዘንና በደስታ የከተማችን ነዋሪዎች በገንዘባቸው፣ በጉልበታቸውና በእውቀታቸው እንዲተባበሩ ከማድረጉም ባለፈ የኢትዮጵያውያንን የጠበቀ የአንድነት ማህበራዊ እሴት እንደሚያጠናክር ሰብሳቢው አውግተውናል፡፡

ዜጎች ኢኮኖሚያቸውን ለመደጎም ሲሉ በየሰፈሩ እና በየስራቦታቸው የሚያከናውኑት ባህላዊ የቁጠባ ስርዓት ወይም እቁብ ኢትዮጵያውያን ካለምንም ልዩነት በጋራ የሚሰባሰቡበት እሴታቸው ሆኖ ዘልቋል፡፡

በተለይም በአገራችን በሁሉም አካባቢዎች የሚኖረው የገጠሩ ማህበረሰብ በጋራ የማረስ በጋራ የመዝራት እና በጋራ የመሰብሰብ የጠበቀ ማህበራዊ እሴት አለው፡፡ በደቦ /በወንፈል መልክ ሰዎች ተሰባስበው ለአንድ ግለሰብ የሚያከናውኑት ቤት የመስራት፣ አረማ እና አጨዳን ጨምሮ የአፈር ጥበቃ ማከናወን፣ የተራቆቱ አካባቢዎችን በችግኝ መሸፈን በገጠሩ ማህበረሰብ ዘንድ አሁንም በስፋት የሚስተዋል የአንድነትና የመተባበር እሴት ነው፡፡

የኢትዮጵያውያን የአንድነት እሴት መገለጫዎች የልማት ስራዎች ብቻ አይደሉም፡፡ ሰርጉም ለቅሶውም ዜጎች ካለምንም ልዩነት በጋራ የሚከውኑት የአንድነት እሴት ነው፡፡ ለአገራቸው ሉአላዊነት ሲሉ ደረታቸውን ለጦር እግራቸውን ለጠጠር ሰጥተው በጋራ የሚተምሙበት የጠበቀ የአንድነት እሴት ባለቤቶችም ናቸው ኢትዮጵያውያን፡፡

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓላትን በጋራ የማክበሩ ጥንታዊ እሴት እየጎላ መምጣቱን እየታዘብን ነው፡፡ በተለይም በከተማችን በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት የሚከበሩትን የመስቀል፣ የጥምቀት፣ የልደት እና የፋሲካ በዓሎችን የእስልምና እምነት ተከታዮችም በዓሉ የሚከበርባቸውን አካባቢዎች በማፅዳት /በተለይም በአደባባይ በዓላት ወቅት/ ‹‹በዓላችሁ በዓላችን ነው›› ሲሉ ማየት በየዓመቱ እየጎለበተ የመጣ መልካም እሴት ነው፡፡ በረመዳን፣ በአረፋ እና በመውሊድ የክርስትና እምነት ተከታዮች በዓሉ የሚከበርባቸውን አካባቢዎች በማፅዳት በበዓሉ ዋዜማ ጀምሮ‹‹እንኳን አደረሳችሁ›› ማለትም በእየዓመቱ እየተጠናከሩ የመጡ የአብሮነት እሴቶቻችን ሆነዋል፡፡

የጋራ ጉባኤው መመስረት እሴቶቻችንን ከማሳደጉ በተጨማሪ የሀይማኖት አባቶችም ቁጭ ብለው በጋራ የሚመክሩበትን ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ በዚህም አንዳንድ ችግሮች ሲከሰቱ ማዶና

ማዶ ሆነው ቃላት ሲለዋወጡ የነበሩት የሀይማኖት መሪዎች በጋራ ለመፍትሄው እንዲተጉ ከማስቻሉ በተጨማሪ በተለያዩ በዓላት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት የመለዋወጥ ባህላቸውን እንዳሳደገው ዋና ፀሀፊው አጫውተውናል፡፡

የሀይማኖት ተቋማቱ የሰላም እሴቶች እንዳይሸረሸሩ በመትጋታቸው እንዲሁም የከተማ አስተዳደሩ እና ነዋሪዎች ለሰላም በሰጡት ትልቅ ዋጋ ከተማችን ሰላሟ ተጠብቆ ትገኛለች፡፡ ‹‹ትንሿ ኢትዮጵያ›› የምትባለዋ አዲስ አበባ አሁንም ህብረ ብሔራዊ ውበቷን አስጠብቃ አንድነቷን አጠናክራ ቀጥላለች፡፡ ይህ ሲባል ግን የሰላም የአብሮነትና የመከባበር እንዲሁም የመቻቻል እሴቶችን የሚሸረሽሩ ዝንባሌዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡

ከራሳቸው አልፎ አፍሪካውያንን እና መላውን ጥቁር ህዝብ ያኮራው የኢትዮጵያውያን የአንድነትና የመተባበር እሴት መሰረቱ ፅኑ ነውና አሁንም ጎልቶ ይስተዋላል፡፡ ሆኖም የአንድነት ስሮችን የሚገዘግዙ ተግባራት እዛም እዚም እየተከሰቱ ‹‹ወደየት እየሄድን ነው›› ማስባሉን ተያይዘውታል፡፡ ለልማት እና ለመተባበር ጎልቶ ይንፀባረቅ የነበረው ነባሩ የደቦ እሴታችን አሁንም ከእነ ግርማ ሞገሱ ቀጥሏል፡፡ ሆኖም በደቦ ማልማት በደቦ መረዳዳቱ እየተሸረሸረ በደቦ መፍረዱ በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች እያቆጠቆጠ መምጣቱ አሳሳቢ ሆኗል፡፡ በደቦ ሚሊዮኖችን ማፈናቀል፣ በደቦ መዝረፍ፣ በደቦ ፍርድ መስጠት፣ በደቦ መግደል ነባር እሴቶቻችንን አጠልሽቷል፡፡ እናቶችን አስለቅሷል፣ አባቶችን አሳዝኗል፣ ወጣቶችን አሳፍሯል፣ ህፃናትን ስጋት ላይ ጥሏል፡፡ ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ አንገት አስደፍቷል፡፡ በእርግጥ ከለውጡ በኋላ እንደ ወረርሽኝ ተከስተው የነበሩ የደቦ ፍርዶችን ድርጅት፣ መንግስት እና መላው ህዝብ ባደረጉት ርብርብ አደብ እየገዙ መምጣታቸውን መታዘብ ይቻላል፡፡ በተለያዩ ቦታዎች የሚደረጉ መፈናቀሎች እየቆሙ ከመሆኑም በተጨማሪ ሚሊዮኖች ወደተፈናቀሉበት ቀዬ እንዲመለሱ መንግስትና ህዝብ የሚያበረታታ እንቅስቃሴ አከናውነዋል፡፡

ከየትኛውም የአገራችን ክፍሎች በተለየ አዲስ አበባ ሰላምና መረጋጋት እንዲርቃት እነ ‹‹ዝም ሲል አንወድም›› የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ የነዋሪዎች የቆየ አብሮነት እንዲሸረሸር የተለያዩ አካላት ከፋፋይ አጀንዳዎችን ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመደገስ ብዙ ተወራጭተዋል፡፡ የጥርጣሬ መንፈስን በማስረፅ የራሳቸውን አጀንዳ ለማስፈፀም ፀረ ሰላም ሀይሎች እንደ አዲስ አበባ የተረባረቡበት የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ኢትዮጵያውያን ከታሪካቸው የሰላምን ውድ ዋጋ ስለሚገነዘቡት በአስተውሎት በመራመዳቸው፣ መንግስትም ህገ ወጦችንም ጭምር በሆደ ሰፊነት በመመልከት በስራዎቻቸው ከዜጎች ልብ እንዲወጡ በትእግስትና በብስለት መራመዱ እንጅ ከለውጡ ወዲህም ጭምር የአገራችንን አንድነት የሚፈታተኑ በርካታ ድርጊቶች ተፈፅመዋል፡፡

ለውጡን ተከትለው የተከሰቱ የአገራችንን መልካም እሴቶች የሚሸረሽሩ የሞራል ዝቅጠቶች እንዲሁ በአጋጣሚ የተፈጠሩ ሳይሆኑ ለዘመናት የተሰሩ አፍራሽ ተግባራት ውጤቶች መሆናቸውን የሀይማኖት አባቶችና ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

ሀይማኖቶች ስነ ልቦና ይጎዳሉ፣ አደንዛዥ እፅ ናቸው የሚለውን የኮሙኒስታዊ ስርዓት ያራምድ የነበረው ወታደራዊው የደርግ ስርዓት የስነ ምግባርና የሞራል ትምህርቶችንም ኮንኗል፡፡ ‹‹የዛሬ 70 ዓመት የነበሩ አባቶች በብሔርና በቋንቋ ሳይለያዩ ሁሉንም ሰው አክባሪ እና አገር ወዳድነታቸው ከዛ ቀጥሎ ከመጣው ትውልድ በእጅጉ የተለዩ ናቸው፡፡ የሰዎች ስብዕና የሚገነባው በአስተምህሮ ነው፡፡ በቅድሚያ ትውልዱን በስነምግባር ሳናንፅ ህንፃ ብንገነባ ከመፍረስ አይድንም፡፡›› የሚሉት የአዲስ አበባ ሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ ዋና ፀሀፊ መጋቢ ታምራት የሞራል እና የስነምግባር ትምህርቶችን ችላ መባላቸውን ያወሳሉ፡፡ በዚህም መልካም

እሴቶች እየተሸረሸሩ በአገራችን ለሚታዩ ህገ-ወጥ እና ኢሰብአዊ ድርጊቶች መበራከት ምክንያት መሆናቸውን መጋቢ ታምራት ያሰምሩበታል፡፡

ኢህአዴግም የሀይማኖቶችን ነፃነት በማረጋገጥ ትውልዱ በመልካም ስነምግባር እንዲገነባ በመሰረታዊነት ታላቅ ድል ቢያስመዘግብም ከወታደራዊ ስርአት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በተደረገው ሽግግር ልክ ዜጎች ከመብቶቻቸው ባለፈ ግዴታዎቻቸውንም በቅጡ ተገንዝበው ለህግ የበላይነት መስፈን የድርሻቸውን እንዲወጡ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ባለመስራቱ ‹‹መብቴ እንጅ ግዴታዬ›› የማይል ብዙ ትውልድ መፈጠሩም ለእሴቶቻችን መሸርሸር ምክንያት ነው ሲሉ መጋቢ ታምራት ያስረዳሉ፡፡

ዓለምን አንድ መንደር እያደረጋት የሚገኘው ሉላዊነት የትየለሌ ከሆኑ ጥቅሞቹ ጎን ለጎን በተለይም በኢኮኖሚ የፈረጠሙ አገሮች ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫና ከባህል ወረራ ጋር ተደማምሮ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገሮች በርካታ ተግዳሮቶችንም መደቀኑ አልቀረም፡፡ የኢትዮጵያውያንን የጠበቀ ማህበራዊ ህይወት እና የአንድነት እሴቶች የሚያላሉ ግላዊነቶች በአገራችንም በተለይም በከተሞች ስር እየሰደዱ መሄዳቸው አሳሳቢ ሆኗል፡፡

ሽሻ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች፣ ማስቃሚያ ቤቶች ከትምህርት ቤቶች መሳለመሳ እያቆጠቆጡ መምጣታቸውም በአዲሱ ትውልድ ስነምግባር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ አታጭሱ፣ አትቃሙ፣ አትጠጡ ሲል ቆይቶ በተግባር ግን እያጨሰ፣ እየቃመና እየጠጣ የሚያስተምር አስተማሪ መበራከቱም ለመልካም እሴቶቻችን መሸርሸር እንደ ዋና ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡

በኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ የስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር መምህር ናቸው፡፡ የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪያቸውንም በአንትሮፖሎጂ በማጠናቀቅ ላይ መሆናቸውን የነገሩን መምህር ግርማ በላቸው ለእሴቶቻችን መሸርሸር ባለፉት ዓመታት ብሄራዊ ማንነት ገንኖ ኢትዮጵያዊነት ችላ መባሉ እንደ ዋና ምክንያት ይጠቅሳሉ፡፡ ‹‹ባለፉት 27 ዓመታት ብሄራዊ ማንነትና ኢትዮጵያዊ አንድነትን በእኩል ማስተናገድ ሲገባን ብሔርን ማስቀደማችን የአንድነት ትስስራችንን አላልቶታል፡፡ ማንነትን ማክበር፣ ቋንቋን ማሳደግ፣ ባህልን ማስፋት በራሱ ችግር ባይሆንም የጋራነትን ከማጠናከር ይልቅ በብሔር አጥር ውስጥ መገባቱ እየታየ ላለው አገራዊ ቀውስ ምክንያት ነው፡፡›› ሲሉ ምሁራዊ ትዝብታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን ከሌሎች አፍሪካውያን በተለየ ለነፃነታቸው ቀናኢ ናቸው፡፡ በተለያዩ ዘመናት የተቃጡባቸውን የውጭ ወረራዎችም አሳፍረው መልሰዋል፡፡ ‹‹ኢትዮጵያ ሉአላዊነቷን፣ ህዝቦቿም ነፃነታቸውን ለዘመናት አስጠብቀው የቀጠሉት በደስታ ብቻም ሳይሆን በጦርነት ወቅትም በጋራ የሚያስተሳስሯቸው አገራዊ እሴቶች ስላሏቸው ነው፡፡›› የሚሉት አቶ ግርማ አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ቁልፉ እየተሸረሸሩ የሚገኙ የጋራ እሴቶችን መጠበቅና መንከባከብ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ዜጎችን አስተሳስሮ ያቆየ እሴት ያላቸው የሀይማኖት ተቋማትም በውስጣቸውም ጭምር ክፍፍል ተፈጥሮ መቆየቱም አገራዊ አንድነታችን ላይ ተፅዕኖ አልነበረውም አይባልም፡፡

ዘመን አመጣሹን ማህበራዊ ሚዲያም ለአንድነት ሳይሆን ለክፍፍል የሚጠቀሙበት ሚዛን በመድፋታቸው እሴቶቻችን እንዲሸረሸሩ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ቀላል አለመሆኑን በርካታ ምሁራን ይስማማሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን ድርና ማግ አድርገው ያኖሯቸው በርካታ የጋራ እሴቶች እንዳሉ እየታወቀ ታሪኮቻቸውን ሁሉ የጦርነት አድርገው በሚያናፍሱ የሀሰት ትርክት ተራኪዎች አንድነታቸው እየተፈተነ እንደሚገኝ ‹‹ታሪክ እውቀት ነው፡፡ እኛ ግን ፖለቲካ አድርገነዋል፡፡ ታሪክን የኋላውን ለማስታወስ፣ ዛሬን የተሻለ ለማድረግና ነገን ወደ ተሻለ ለመራመድ መጠቀም ይገባል፡፡›› በማለት

መምህር ግርማ ያሳስባሉ፡፡ ታሪክን በወንዝ የሚመስሉት መምህሩ ከመነሻው የጠራ ቢሆንም በየቦታው በሚገቡ ቆሻሻዎች ጅረቶች እንደሚደፈርሱት ሁሉ ታሪክም ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ በተወሰነ መልኩ እንደሚበረዝ በመገንዘብ ለመማሪያ ብቻ መጠቀም እንደሚገባ ምሁራዊ ምክራቸውን ይለግሳሉ፡፡

በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል እንዲሉ አባቶቻቸው በጋራ እሴቶቻቸው ያቆዩትን ነፃነት ችላ በማለት ‹‹ጣሊያን ገዝታን በሆነ›› እስከማለት የሚዳፈሩ ግለሰቦችም አሉ፡፡ ይህም አስተሳሰብ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብትን ለይቶ ካለማወቅ እንደሚመነጭ ‹‹እኛ መንፈሳዊ ሀብት ማለትም የራሳችን ፊደል፣ ቋንቋ፣ ያልተበረዘ ማንነት ስላለን ትክክለኛ የአፍሪካውያን ወኪሎች ሆነናል፡፡ ሌሎቹ ግን በቁሳዊ ሀብት ከእኛ ቢሻሉም መንፈሳዊ ሀብታቸውን አጥተዋል፡፡›› በማለት ትወልዱ በታሪኩ ሊኮራ እንደሚገባ ምሁሩ ያስገነዝባሉ፡፡

ቅኝ ገዥዎች የአፍሪካውያንን እምቅ ሀብት ለመዝረፍ እንዲያመቻቸው መንገድ ሰርተዋል፣ ህንፃ ገንብተዋል፡፡ ሆኖም ማንነታቸውን አሳጥተው የራሳቸውን ማንነት ጭነውባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን በተሟላ ስነ ልቦና አንገታቸውን ቀና ደረታቸውን ነፋ አድርገው እንዲሄዱ አባቶቻቸው የህይወት መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡

ተደናግረው የሚያደናግሩና የነፃነት ትርጉም የማይገባቸው ግለሰቦች ወንዝ የማያሻግሩ ቋንቋዎች፣ ኋላቀር አለባበሶች፣ ባህላዊ አመጋገቦች፣ በዓለም የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ለመወዳደር የማያስችሉ ሙዚቃዎች፣ ከኢትዮጵያውያን አልፈው የማይታዩ ፊልሞች ወዘተ በማለት በህይወት መስዋዕትነት ተጠብቀው የዘለቁ ማንነቶችን ሲያንኳስሷቸው ይስተዋላሉ፡፡ በእርግጥ የራሳቸውን ቋንቋ እና ባህል እና መሰል መንፈሳዊ ሀብቶቻቸውን አጥተው በቅኝ ገዢ ሀይሎቻቸው የሚገለገሉ፣ ነገር ግን የተሻለ ቁሳዊ ሀብት ያላቸው አገሮች አሉ፡፡ ከድህነት ጋር እንዲቆራረጡና በዕድገት ጎዳና እንዲገቡ ያስቻላቸው በሌሎች መንፈሳዊ ሀብት ስለተገለገሉ ነው የሚለው ግን ውሀ አያነሳም፡፡ ምን አልባትም መንፈሳዊ ሀብቶቻቸው ተጠብቀውላቸው ቢሆን ኖሮ ከቁሳዊ ሀብቶቻቸው ጋር ተደምረው የኩራት ምንጮቻቸውና የተጨማሪ ዕድገታቸው በር ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡

በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው በዓለም ቁንጮ ላይ የተቀመጡ አገራት የራሳቸውን ወደው የሌሎችንም ለራሳቸው በሚመች መልኩ በመጠቀማቸው አሁን ከደረሱበት መድረስ ችለዋል፡፡ ምሳሌ የእኛ ግዕዝ እዚህ እያጣጣረ በደረቱ ሲሳብ ጀርመኖች የዶክትሬት ዲግሪ ይሰጡበታል፡፡ ምዕራባውያኑ ቋንቋዎቻቸው ድንበር ሳይገድባቸው በተለያዩ አገራት መስፋፋት የቻሉት ከሌሎች በላይ ሆነው በመፈጠራቸው ሳይሆን ቅድሚያ ራሳቸው ልዩ ትኩረት ስለሰጧቸው ነው፡፡ ‹‹ባለቤቱ የናቀውን አሞሌ ባለእዳ አይቀበለውም›› እንዲሉ እንግሊዘኛ ቋንቋ በተለያዩ የዓለም አገራት ይነገር ዘንድ መጀመሪያ በእንግሊዞች መወደድና መዳበር ነበረበት፡፡

ምዕራባውያን አሁን ላይ ትልቁ የገቢ ምንጫቸው እየሆነ በመጣው የቱሪዝም ዘርፉ አመጋገባቸውን፣ አለባበሳቸውንና አጠቃላይ የኑሮ ዘይቤአቸውን ከዘመናዊነታቸው ጋር እያስተሳሰሩ ለዓለም ገበያ እንደሚያቀርቡ ልብ ይሏል፡፡ የሌለ ነገር /ዜሮ ዲግሪ የሀሳብ መስመር/ እንኳን የቱሪስት መስህብ ሆኖ ለንደን ላይ ይጎበኝም አይደል?!

ቅኝ ግዛት ያልተገዛችው ኢትዮጵያ የራሷን ማንነት ይዛ ለዘመናት መዝለቋ ‹‹ወንዝ አያሻግሩም›› የሚያስብሏት ሳይሆኑ ሌሎች የዓላም ህዝቦች ወንዝ ተሻግረው እንዲመጡ የሚያስችሉ እንቁ መንፈሳዊ ሀብቶቿ ናቸው፡፡ ያሉን መንፈሳዊ ሀብቶች ወንዝ የማያሻግሩ ሆነው ሳይሆን ችግሩ የሚመጣው ያለንን አውቀን በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላችን ነው፡፡

ከምዝበራ የተረፉ ጥንታዊ የብራና መፅሀፍትን ፍለጋ አውሮፓውያን በየጊዜው ደጅ የሚጠኑት

ቋንቋችንን ለማሳደግ አስበው አይደለም፡፡ ይልቁንም የአባቶቻችንን ተዝቀው የማያልቁ ዘርፈ ብዙ እውቀቶች ለማፈስ እንጅ፡፡ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚገኙ አለባበሶች አመጋገቦች እና ሌሎችም የኑሮ ዘይቤዎች የኋላቀርነታችን ማሳያ ሳይሆኑ የነፃነታችን ቋሚ ምስክሮች ናቸው፡፡

መጠቀም ከቻልንም በተለይም ‹‹ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ›› በመባል በሚታወቀው የቱሪዝም ዘርፍ ዋነኛ የገቢ ምንጮቻችን እንደሚሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ መስቀል፣ ጥምቀት፣ ረመዳንና አረፋን በመሳሰሉት ሀይማኖታዊ በዓላት በኢሬቻ እና በፊቼ ጨምበላላ፣ በኢትዮጵያውያን ሴቶች የልጃገረዶች ጨዋታ /አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል እና ሻደይ/፣ በቡሄ እና በሌሎችም ባህላዊና ሀይማኖታዊ እሴቶቻችን የሚማረኩ እና መንፈሳዊ ቅናት የሚያድርባቸው አፍሪካውያን ወንድም እህቶቻችን እና የሌሎችም የዓለም አገራት ዜጎች ቁጥር ከዓመት ዓመት እየጨመረ መምጣቱ ለዚህ ማሳያ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን በርካታ የሚወራረሱ ባህሎች፣ የሚጋሯቸው አሻራዎች፣ የጋራ ታሪኮች፣ ችግሮችን በጋራ ተጋፍጠው ያስመዘገቧቸው የጋራ ድሎች፣ ቤተሰብ ማህበረሰብ የማይለዩ የጋራ ሀይማኖቶች፣ ቀዬ የማይገድባቸው የጋራ ቋንቋዎች ያሏቸው በመሆናቸው በርካታ ምሁራን በሰርገኛ ጤፍ ይመስሏቸዋል፡፡ እንዱውም መምህር ታዬ ቦጋለ የተባሉ የታሪክ ምሁር ደግሞ የኢትዮጵያውያንን የጠበቀ ትስስር ከሰርገኛ ጤፍም በላይ መሆኑን ሲገልፁ ሰምተናል፡፡

አማራው ከኦሮሞው፣ ትግሬው ከወላይታው፣ አፋሩ ከአርጎባው፣ ስልጤው ከጉራጌው፣ ሶማሌው ከሲዳማው፣ ጉምዙ ከከምባታው አንዱ ከአንዱ እየተሳሰረ በባህል ብቻም ሳይሆን በደምም እየተዋሀደ በመሆኑ ሰርገኛ ጤፍን ከዘመን ብዛት መለየት ቢቻል እንኳን ኢትዮጵያውያንን ግን አንዱን ከአንዱ መለየት እንደማይቻል መምህር ታዬ ቦጋለን ጨምሮ ሌሎችም ምሁራን በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይደመጣል፡፡

ኢትዮጵያውያን በርካታ አንድ የሚያደርጓቸው የጋራ እሴቶች ቢኖሯቸውም የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ ማንነቶችም እንዳሏቸው እሙን ነው፡፡ ሆኖም እነዚህም ቢሆኑ ህብር የሆኑ ድምቀቶቻቸው እንጅ የሚከፋፍሉና ትልቁን ኢትዮጵያዊነት እሴትን የሚሸረሽሩ አይደሉም፡፡

አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ የሚለውን የመተሳሰብና የመረዳዳት እሴት የተለያዩ የፖለቲካ ፍላጎቶች ያሏቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ከራስ ወዳድ መሰሪ ፍላጎቶቻቸው አንፃር በመቃኘት ሲበርዙት ይስተዋላል፡፡ ‹‹ፖለቲካ እያሸነፈ እየተሸነፈ ይፈራረቃል፡፡ አገር እና ህዝብ እንዲሁም እምነት ግን ሁሌም ይኖራሉ፡፡ ለፖለቲካቸው እስከተመቻቸው ብቻ መደረግ የሌለበትን ማድረግ ለፖለቲከኞች አይበጅም›› የሚሉት የአዲስ አበባ ሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ ዋና ፀሀፊ መጋቢ ታምራት ዜጎች በአገር ጉዳይ ሊደራደሩ እንደማይገባ ያስገነዝባሉ፡፡

ትውልዱ የአገሩን ትክክለኛ ታሪክ እንዲያውቅ የተሰሩ ስራዎች ውስንነት አሁን ላይ እየታዩ ላሉት የአገራችን ነባር እሴቶች መሸርሸር እንደ አንድ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡ በአንጋፋው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጭምር የታሪክ ትምህርት መታጠፉ ይታወቃል፡፡ ሀሉንም ኢትዮጵያውያን ያማከለ የታሪክ ትምህርት መስጠት ተገቢና ትክክለኛ ሀሳብ ነው፡፡ ተዘርዝረው የማያልቁ የአንድነት እሴቶች፣ እንደ ተራራ የገዘፉ የጋራ ድሎች፣ እንደ ሰርገኛ ጤፍ የተዋሀደ የጋራ ማንነት፣ የጥንታዊ ታሪኮች ባለቤት ሆነን እያለ ተተኪው ትውልድ የአገሩን ታሪክ የሚያውቅበትን እድል መንፈግ ሁሉም የመሰለውን መላምት እንዲወስድ መፍቀድ ነው፤ አሁንም ቢሆን ከሞላ ጎደል እየሆነ ያለው ይኸው ነው፡፡ በመሆኑም የታሪክ ነገር ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

እንደ መረዳዳቱ፣ መከባበሩ፣ መቻቻሉ ሁሉ አለመግባባቶችን በውይይት መፍታትም የኢትዮጵያውያን የጋራ እሴት ነው፡፡ ስሙ ይለያይ እንጅ በሁሉም አካባቢዎች የበደለ ክሶ የተበደለ ተክሶ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸው ቱባ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች አሉን፡፡

የእድሜ ባለፀጋዎችንና የሀይማኖት አባቶችን ማክበር አንዱ የኢትዮጵያውያን የጋራ እሴት በመሆኑ ተደማጭነታቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

ባለፈው ዓመት በቡራዩ ከተማና በአካባቢው ተከስቶ በነበረው ሁከት በአርባ ምንጭ ከተማ ሰልፍ የወጡ ልጆቻቸውን እና ወንድሞቻቸውን ለጥፋት፣ ለበቀልና ለክፋት እንዳይነሳሱ የጋሞ አባቶች የወሰዱት እርምጃ ነባር እሴቶቻችን አገራችንን እንዴት አድርገው ከጥፋት እንደሚታደጉ ፍንትው አድርጎ ያሳየ ነው፡፡ የጋሞ ሽማግሌዎች እንደ ጋሞ ማኀበረሰብ ባህል ለምለም ሳርና ቅጠል ይዘው በስሜት ተነሳስተው ወደ ጥፋት ከሚገሰግሱ ወጣቶች ፊት ተደቀኑ፡፡ በሌለ ወገባቸው አጎነበሱ፣ ታላቅ ሆነው እያለም ከታናናሽ ወንድሞቻቸውና ልጆቻቸው ፊት ተንበረከኩ፡፡ ሕዝባቸውን ስለ ፍቅር፣ ስለ ምሕረትና ይቅርታ በአንድነት ተማፀኑ፡፡ ወጣቶችም የአገራቸውን እና የማህበረሰባቸውን ነባር እሴት ጠንቅቀው የሚረዱ ነበሩ፡፡ ለጥፋት ሲገሰግሱ የነበሩ እግሮቻቸው ወደ ምህረት ጎዳና አመራ፡፡ በጥላቻ ተሞልቶ የነበረው ልቦናቸው በአባቶች ፍቅር ወደቀ፡፡ ለበቀል ተነሳስቶ የነበረው አዕምሯቸው ለይቅርታ እራራ፡፡ በዚህም ይከሰት የነበረው የጥፋት ድግስ በሰላም ማዕድ ተለወጠ፡፡ በዚህም የጋሞ አባቶች እና ወጣቶች ብቻም ሳይሆኑ በአኩሪ እሴቷ ኢትዮጵያም አሸናፊ ሆነች፡፡ በወቅቱ የጋሞዎችን አኩሪ ተግባር በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ሚዲያዎች ያየና የሰማ ሁሉ ነባር እሴቶቻችንን አድንቋል፡፡ የጋሞ አባቶችና ሽማግሌዎች የፈፀሙት አኩሪ ተግባር የኢትዮጵያዊ አንድነት የፍቅር ቃል ኪዳን ውል ሕያው ምስክር ሆነው እስከ ዘላለሙ ይታወሳሉ፡፡ የጋሞ ሽማግሌዎች በፈፀሙት አኩሪ ተግባር የ2011 ዓ.ም ልዩ የበጎ ሰው ሽልማት እንደተበረከተላቸውም አይዘነጋም፡፡

በሌሎች የአገራችን አካባቢዎችም የእድሜ ባለፀጎች እና ተደማጭነት ያላቸው ግለሰቦች ፍቅርን ይሰብካሉ፡፡ ይቅር ባይነትን ያውጃሉ፡፡ ቂም በቀልን ያወግዛሉ፡፡ መደማመጥን ያሰፍናሉ፡፡ የኢትዮጵያዊነትን የአንድነት ቃል ኪዳንም ከፍ ያደርጋሉ፡፡ ሽምግልናን የመሳሰሉ ነባር እሴቶቻችንን መንከባከብና መጠበቅ የተገመደ አንድነታችንን ማጥበቅ ነውና በትኩረት ሊሰራበት ይገባል፡፡

ባህላዊ የግጭት አፈታት እሴቶቻችን በዘመናዊው ፍርድ ቤት የሚጠፋውን ገንዘብ እና የሚባክነውን ገንዘብ እና ጉልበት በማስቀረትም ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንዳላቸው አሌ የማይባል ነው፡፡

በዳይም ተበዳይም በአሸናፊነት የሚወጡበት ባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ስርዓት ከሀይማኖታዊ እሴቶችም አንዱ መሆኑን ‹‹መባህን ለእግዚያብሔር ለማቅረብ ብትነሳ ነገር ግን አንዳች በወንድምህ ላይ በደል ብታገኝበት መሰውያየን አስቀምጥና ሂድና ከወንድምህ ጋር ታርቀህ ተመልሰህ መስዋዕቴን አቅርብ›› እንደሚል መጋቢ ታምራት መፅሀፍ ቅዱስን ያጣቅሳሉ፡፡ ጥል በቅዱስ ቁራንም በመፅሀፍ ቅዱስም የተወገዘ መሆኑን ያወጉን ዋና ፀሀፊው አገር አቀፍ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤም በመላ አገሪቷ እርቀ ሰላም እንዲሰፍን ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙ ያስረዳሉ፡፡

በተለይም ከለውጡ በኊላ በብልፅግና ፓርቲ ሊቀመንበር በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ ፊት አውራሪነት በመንግስት ደረጃ ታሪክ የማይረሳው የእርቅ ስርዓት ተፈፅሟል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በውጭ ሀገር ይኖሩ በነበሩት የቀድሞው ፓትሪያርክ እና በአሁኑ ፓትሪያርክ መካከል የነበረው ክፍተት በእርቀ ሰላም ተቋጭቷል፡፡ በእስልምናው ውስጥም የነበሩ ችግሮች እልባት እንዲያገኙ ጠቅላይ ሚኒስትራችን የተጫዎቱትን አኩሪ ተግባር በመፅሀፍ ቅዱስ ‹‹የሚያስታርቁ ብፁአን ናቸው የእግዚያብሔርን መንግስት ይወርሳሉና›› እንደተባለው ሁሉ እንደ እምነት ተቋማትም በዚህ ዘመን ትልቅ ስራ ተሰርቷል ብለው ከሚያስቡት

መልካም ተግባር አንዱና ዋነኛው መሆኑን መጋቢ ታምራት አጫውተውናል፡፡

የአገራችንን የአንድነት እሴት የሚሸረሽሩ ድርጊቶች እልባት እንዲያገኙ ከሀይማኖት አባቶችና ከአገር ሽማግሌዎች በተጨማሪ አንዳንድ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችም ከመንግስት ጋር በመቀናጀት እየተረባረቡ ይገኛሉ፡፡ ለአብነትም በአለፉት 30 ዓመታት የሰላም ግንባታና የግጭት አፈታት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ የድርሻውን ሲወጣ የቆዬውን ሰላምና ልማት ማዕከልን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በአምባገነኑ የደርግ ስርዓት ወቅት ተፈጥሮ የነበረውን የእርስ በእርስ ግጭት ለመፍታት በውጭ አገር ይኖሩ በነበሩ ኢትዮጵያውያን እንደተመሰረተ የሚነገርለት ይህ ድርጅት በደርግ እና ኢህአዴግን ጨምሮ በወቅቱ በነበሩ በሌሎችም የፖለቲካ ሀይሎች መካከል የነበረው አለመግባባት እልባት እንዲያገኝ እንቅስቃሴ ማድረጉ ይወሳል፡፡ በኋላም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተከሰተውን ግጭት በአፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኝ የሁለቱን አገራት መንግስታት ለመሸምገል ሰላምና ልማት ማዕከል ብርቱ ጥረት አድርጎ እንደነበር ከድርጅቱ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

አሁን ላይ ከትግራይና ከሀረሪ ክልል በስተቀር በሁሉም ክልሎች የሰላም ግንባታና የግጭት አፈታት ፕሮጀክት ቀርፆ ለአገራችን እሴቶች መጠበቅ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡ ድርጅቱ በመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ሀይማኖትንና ብሔርን መሰረት አድርገው ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን ለተማሪዎች ግንዛቤ በመፍጠር አስቀድሞ ለመከላከልም በባህር ዳር፣ በጎንደር፣ በአምቦ፣ በሀረሚያ እና በጅማ ዩኒቨርስቲዎች በእያንዳንዳቸው በዓመት እስከ 600 የሚደርሱ ተማሪዎች ጥልቅ ውይይቶችን የሚያደርጉባቸው የውይይት መድረኮችን እየፈጠረ እንደሚገኝና ወደ ሌሎችም የማስፋት ውጥን እንዳለው ከተቋሙ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

በክልሎች በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል የሚታዩ የግጭት ዝንባሌዎችንም ህዝቡን ባሳተፈ መልኩ እልባት እንዲያገኙ የድርሻውን ለመወጣት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ከማዕከሉ አረጋግጠናል፡፡

ለአገራችን ሉአላዊነት ዘር ሀይማኖት ብሔር ቀለም ሳይለዩ በጋራ በመነሳታቸው ዛሬ ላይ እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻም ሳንሆን መላው ጥቁር ህዝብ በአባቶቻችን ድል ይኮራል፡፡ ኢትዮጵያውያን በአንድነት እሴቶቻቸው ተጋምደው ሉዓላዊነታቸውን አስጠብቀው ዘልቀዋል፡፡ በዚህም በቅኝ ግዛት እና በአፓርታይድ ስርዓት ሲማቅቁ ለነበሩ አፍሪካውያን ወንድሞቻችን ጥቁሮች አሸናፊ መሆን እንደሚችሉ በተደጋጋሚ በተግባር በማሳየት የሞራል ስንቅ ሆነዋቸዋል፡፡ ምን ይሄ ብቻ የዲፕሎማሲና የቁሳቁስ ድጋፍም በማድረግ ታላቅነታቸውን አስመስክረዋል፡፡ ለደቡብ አፍሪካ ለዚምባብዌና ለናምቢያ ደግሞ የነፃነት ትግል ወታደራዊ ስልጠና በመስጠት አሁን ላለነውና ለመጭውም ትውልድ የኩራት ምንጭ ሆነዋል፡፡

አፍሪካውያን በቅኝ አገዛዝ ቀምበር ሲማቅቁ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ መድረኮች ለራሷ ብቻም ሳይሆን ለአፍሪካውያን ፍትህ ስትሞግት እንደነበርም ዓለም የሚያውቀው እውነታ ነው፡፡

ኢትዮጵያ 6 ሺ.ህ 37 ጠንካራ ጦር በቀዝቃዛው ጦርነት ስትታመስ ወደነበረችው ደቡብ ኮሪያ እኤአ ከ1950-53 ልካ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ‹‹እልም አለ ባቡሩ፣ እልም አለ ባቡሩ ወጣት ይዞ በሙሉ፡፡›› በሚለው የካሳ ተሰማ ዘፈን የታጀቡት ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ከአገራቸው አልፈው የዓለምን ሰላም ለማስከበር በምድርና በሰማይ ገስግሰው በኮሪያ ልሳነ ምድር ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ደማቅ ታሪክ ፅፈው ተመልሰዋል፡፡ በዚህ በአምስት ዙር በተደረገው ዘመቻ 122 ኢትዮጵያውያን ለዓለም ሰላም ሲሉ ህይወታቸውን ሰውተዋል፤ አንዳቸውም ባለመማረካቸው የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት ዳግም ለዓለም አስመስክረዋል፡፡ በዚህ የቃኘው ጦር በመባል በሚጠራው የኢትዮጵያ ወታደራዊ ክንፍ ገድል ኢትዮጵያውያን ብቻም ሳይሆኑ ዓለምም ይደነቃል፡፡

እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ1990ዎቹ በሩዋንዳ በተከሰተው የእርስ በእርስ እልቂትም መፍትሄ እንዲሰጡ የጥቁር ህዝቦች ሁሉ ኩራት ለሆኑት ኢትዮጵያውያን አለም እጇን ዘርግታላቸዋለች፡፡ በዚህ ዓለምን ባስደነገጠና ባሳዘነ የእርስ በእርስ ግጭት ወቅት ኢትዮጵያውያኑ ለአፍሪካውያን ወንድም እህቶቻቸው ፈጥነው በመድረስ የሰላም አየር እንዲነፍስ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በአሁኗ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ /ዲአርሲ/ በያኔዋ ቤልጅዬም ኮንጎ የነበረውን ችግር ለመፍታት የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሀይል እኤአ ከ1960 እስከ 1964 ግዳጁን ስነምግባር በተሞላ መልኩ በስኬት መወጣቱም የሁላችንም ኩራት ሆኖ በታሪክ ይወሳል፡፡ በከፍተኛ የእርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ገብታ ስታምጥ በነበረችዋ ላይቤሪያ የሰላም አየር እንዲነፍስና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የኢትዮጵያ የሰላም አስከባሪ ሀይል የፈፀመው አኩሪ ድልስ እንዴት ይረሳል?

በጎረቤት አገር ሱዳን ዳርፉር ግዛት ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር በመሆን በሱዳን እና በደቡብ ሱዳን ይሁንታ ደግሞ የአብዬ ግዛትን ሰላም በብቸኝነት እንዲያረጋግጥ የተመረጠ የኢትዮጵያውያን ኩራት ነው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሀይል፡፡

በሱማሊያ መንግስት አልባነትንና አክራሪነትን ከሌሎች ሰላም አስከባሪ ሀይሎች ጋር በመሆን ኢትዮጵያውያኑ ጉልህ ድርሻ አበርክተዋል እያበረከቱም ነው፡፡ ቡሩንዲም ብትሆን የሰላም አስከባሪ ሀይላችን አሻራ እንዳረፈባት አይዘነጋም፡፡ የጎረቤት አገራችን ሰላም የኛም ሰላም ነውና ተግባሩ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡

በቅርቡ እንኳን ሱዳንን ለ30 ዓመት አካባቢ የመሯት ፕሬዝዳንት አልበሽር በመፈንቅለ መንግስት ከስልጣን መውረዳቸውን ተከትሎ አገሪቷ መንታ መንገድ ላይ ስትወድቅ በጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር አብይ አህመድ መሪነት አገራችን አለሁ ማለቷ በሱዳናዊያን ‹‹የችግራችን ደራሾች›› እስከመባል ደርሰናል፡፡ ይህም እኛ ኢትዮጵያውያን ከተባበርን በሁሉም መስክ ለሌሎች አገሮችም አለኝታ መሆናችንን ጠቋሚ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን በአፍሪካ እና በዓለም ሰላም ላይ እየተጫወቱት ያለው ላቅ ያለ ሚና ከማንም የተቸራቸው ሳይሆን በጠንካራ የአንድነት እሴቶቻቸው ሉዓላዊነታቸውን የማረጋገጣቸው ውጤት ነው ብሎ በልበ ሙሉነት መናገር ይቻላል፡፡ ያ ባይሆንማ ኖሮ ለሰላም ማስከበር ዓለምም እጇን ባልዘረጋች ነበር፡፡

ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ያስመዘገቡትና እያስመዘገቡት ያሉት ድል የአንድነት እሴቶቻችን ከራሳችን አልፈው ለዓለም ሰላምም ድርሻቸው የጎላ መሆኑን ያረጋግጡልናል፡፡ በመሆኑም መንግስት ብቻም ሳይሆን የሀይማኖት ተቋማት፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች እየተሸረሸሩ ለሚገኙ ከሀገራችን አልፈው ዓለምን ለሚጠቅሙ ታላላቅ እሴቶቻችን መረባረብ ግድ ይላል፡፡

የመሸርሸር አደጋ የተጋረጠባቸው አገራዊ እሴቶቻችን ወደነበሩበት እንዲመለሱ ከመሰረቱ መስራት ለነገ የማይባል ነው፡፡ ቤተሰብ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሁሉ መሰረት ነው፡፡ በበቤተሰብ ደረጃ በሞራል እና በስነምግባር ተኮትኩቶ ያላደገ ህፃን ለማህበረሰቡ፣ ለአገሩ እና ለዓለም ሰላም የሚጠበቅበትን ሊወጣ አይችልም፡፡ በመሆኑም የሰላምን፣ የፍቅርንና የመደመርን ፍሬ የሚሹ ወላጆች ለልጆቻቸው ከልዩነት ይልቅ አንድነትን፣ ቂምንና ጥልን ሳይሆን ይቅር ባይነትንና ፍቅርን እየመገቡ ሊያሳድጓቸው ይገባል፡፡ ነብዩ መሀመድ ‹‹ዘረኝነት ጥንብ ናት›› እንዳሉት ኢትዮጵያውያን ወላጆች የዘረኝነትን አስከፊነት ለልጆቻቸው እየነገሩ ሊያሳድጓቸው ይገባል፡፡

ተተኪውን ትውልድ በስነምግባር የመኮትኮቱ ጉዳይ ችላ ማለቱ ከቀጠለ የተዘራው መብቀሉ አይቀርምና ሁሉን በሚቀበለው የልጆች አዕምሮ ላይ የሚገባው አሉታዊ አስተሳሰብ ዋጋ

እንደሚያስከፍለን ጥርጥር የለውም፡፡

ኢትዮጵያውያን ልጆቻቸውን በጋራ የማሳደግ ባህል አላቸው፡፡ እናት አባቱ ሳያዩት ጥፋት የሚያጠፉን ታዳጊ ቆንጥጦና ገስፆ ማረም አሁን ላይ እየላላ ቢመጣም የጎረቤትም ሀላፊነት ነው፡፡ በመሆኑም ከገባንበት ችግር ለመውጣት ይህን መሰል መልካም እሴቶቻችን ችላ ሊባሉ አይገባም፡፡

ተተኪው ትውልድ አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፍባቸው ትምህርት ቤቶች የእውቀት እራቡን ብቻም ሳይሆን የስነምግባር ጥሙን ካላረኩለት የተሻለች አገር እና የተሻለች ዓለም ለመፍጠር ማሰብ ከንቱ ምኞት ይሆናል፡፡ የትምህርት ጥራት መለኪያውም ተማሪዎች ምን ያህል አውቀዋል በሚለው ብቻ ሳይሆን ምን ያህል በስነ-ምግባር ተገንብተዋል የሚለው ጉዳይ በተለይም እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ በሚገኝበት በዚህ ሰዓት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

አገራችን የሀይማኖተኞች አገር እንደመሆኗ የሀይማኖት አባቶች ተሰሚነት ከፍ ያለ ነው፡፡ ከማስተማር እስከ ማውገዝ ስልጣን ያላቸው የሀይማኖት አባቶች ራሳቸውን አርአያ አድርገው እየተንቀሳቀሱ የትውልዱን ሞራል በመመለስና በመልካም ስነምግባር በማነፅ እየተሸረሸሩ የሚገኙ አገራዊ እሴቶችን ዳግም ማንሰራራት እንደሚጠበቅባቸው መጋቢ ታምራት አባታዊ ምክራቸውን ይለግሳሉ፡፡

ሰው ከሚሰማው ይልቅ የሚያየውን ማመን ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ሳምንቱን ሙሉ አትስከሩ ብሎ ሲያስተምር የቆየ መምህር እግር ጥሎት በሳምንቱ መጨረሻ ወዲ ዘመም ወዲያ ጠመም ሲል ከታየ ከተማሪዎቹ ጭንቅላት የሚመዘገበው መጠጣት የሚለው ቃል በመሆኑ በተግባር ማስተማር በሁሉም ሊለመድ ይገባል፡፡

ልጆቹን በመልካም ስነ-ምግባር ኮትኩቶ ማሳደግ ያልቻለ አባትም በባህላችን ለአቅመ ምክር እና ለአቅመ ማስታረቅ እንደማይሆን የምንገነዘበው እውነታ ነው፡፡ በመሆኑም አርአያነት ከማንም የምንጠብቀው ሳይሆን ከራሳችን ጀምሮ በቤተሰባችን አሽቶ ለማህበረሰባችን የሚጎመራ እንዲሁም ለአገራችን የሚያፈራ መልካም ዘር ሊሆን ይገባል፡፡

‹‹ሁላችንም ያለችን አንዲት አገር ናት፡፡ በመጀመሪያ ሰው እንደመሆናችን ሰውነት ሊያስተሳስረን ቢገባም ዓለም በአገራት ስለተከፋፈለች እኛም ኢትዮጵያ የምንላት አንዲት ምትክ የለሽ አገር አለችን፡፡ ከዚህ ወርደን ወደ መንደር ዝቅ ካልን ግን ወደ እንስሳነት መውረድ ነው›› የሚሉት የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ መምህር ግርማ ሆኖም ለረጅም ዓመታት ከኢትዮጵያዊነት በላይ ስለ ብሔር በመሰራቱ ይህንን ለማስተካከል ጊዜ መውሰዱ እንደማይቀር ያስረዳሉ፡፡

ምሁራን አገር ወደፊት እንድትራመድና የአስተማራቸው ማህበረሰብ የተሻለ ህይወት እንዲኖር የድርሻቸውን የመወጣት ድርብርብ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ በመሆኑም ከተራው ዜጋ በተሻለ መልኩ ሀሳቦችን ከአንድ አቅጣጫ ሳይሆን ከብዙ አውዳቸው መመልከት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገሮችን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ በተመራማሪነት በአካባቢ በመታጠር ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ እይታን በማዳበር ለአገራዊ እሴቶች መጠበቅ ሊረባረቡ እንደሚገባ መምህር ግርማ ያሳስባሉ፡፡

እኔ ያልኩት ካልተፈፀመ በማለት የህዝብን ፍላጎት እና ጥቅም ጥያቄ ውስጥ ማስገባት፣ በጥናት እና ምርምር ለችግሮች መፍትሄ ማፈላለግ ሲገባ ነገሮችን ከአንድ አቅጣጫ ብቻ በማየት ችግር ፈጣሪ መሆን የምሁርነትን ደረጃ እያወረደው እንደሚገኝ መምህር ግርማ አጫውተውናል፡፡

የሀሳብ ልዕልና ማሸነፍን ብቻም ሳይሆን መሸነፍንም በፀጋ መቀበል ነው፡፡ መደማመጥ ሀሳብን በሀሳብ ማሸነፍ እንጅ ግትርነት ልክ እንደ ሀሳቡ አገራችንንም አንድ እርምጃ ወደፊት አንድ እርምጃ ወደ ኋላ እየወሰደ ባለችበት የሚያስቀር በመሆኑ በማህበረሰባችን ዘንድ ያለው ማሸነፍን ከዱላ እና ከሁከት እንዲሁም ከሀይል ጋር የማያያዝ ኋላ ቀር እሳቤ ሊቀረፍ እንደሚገባም

ምሁራን ይመክራሉ፡፡

መረጃ ለአገራችን ግንባታ ወይም ለማፈራረስ ሊውል የሚችል መዶሻ በመሆኑ አጠቃቀማችንን በመፈተሽ ማስተካከል ለነገ የሚባል አይደለም፡፡ ዜጎች ብስሉን ከጥሬው ለይተው መመገብ የሚገባቸው ቢሆንም መሪው ፓርቲያችን እና መንግስት ግልፅነት በሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ ፈጣን ማብራሪያ በመስጠት ከመደናገር የመጠበቅ ሀላፊነትም እንዳለባቸው መዘንጋት የለበትም፡፡

‹‹የሰው ልጅ በመሰረታዊነት ፍትህ፣ እኩልነትና ሰብአዊ ክብሩ እንዲጠበቁለት ይፈልጋል፡፡›› የሚሉት መምህር ግርማ እነዚህን መብቶች ለራሳቸው እኩይ አላማ ማስፈፀሚያ ለማዋል ከብሄርና ከሀይማኖት ጋር እያገናኙ ‹‹አንተ እንደዚህ የሆንከው እንዲህ በመሆንህ ነው›› በማለት ህዝብን የሚከፋፍሉ ግለሰቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ የህግ የበላይነትን ማስፈን እየተሸረሸሩ የሚገኙ እሴቶቻችንን ለመጠበቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ያስምሩበታል፡፡

ኢትዮጵያችን እንደ ቆዳ እየተወጠረች የምትገኘው ‹‹ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው›› እንደሚባለው እንደሰደድ እሳት የሚናፈሱ መሰረተ ቢስ ወሬዎች እንጅ ለሌሎችም ትበቃለች፡፡ በተበደለ ጎን መቆምና ማስካስ የአበው አባቶቻችን ነባር እሴት ነው፡፡ አሁን ላይ ይህ እሴት እጅግ ከመሸርሸሩ የተነሳ አንድ ግለሰብ ጉዳት ሲደርስበት እንኳን ለግለሰቡ ማዘንና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ሲገባ ‹‹ከየት ነው፣ የማን ነው›› የሚለው ጥያቄ ሲቀድም እየሰማ ልቦናው የማያለቅስ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ትውልዱ አንዱ በአንዱ እየተተካ ይቀጥላል እንጅ ኢትዮጵያ ግን በማንም የማትተካ ምንግዜም የምትኖር የሁላችን እናት የሁላችን ቤት ናት፡፡ በእምነት ደረጃ አይሁዳዊውም፣ ኦርታዊውም፣ ወንጌላዊውም፣ እስልምናውም ወደዚች የተባረከች አገር በሰላም ገብቶ ለረጅም ዘመናት በመከባበር ዘልቋል፡፡

ኢትዮጵያችን ሀይማኖቶችን እና ሀይማኖተኞችን ብቻም ሳይሆን ወደ አፈሯ መምጣት የፈለጉትን ሁሉ በክብር ተቀብላ አላምዳ ያኖረች እና እያኖረች ያለች ተፈጥሮ አብዝታ የቸረቻት ናት፡፡ ቤተ እስራኤላዊያን ለረጅም ዘመናት ኢትዮጵያ ላይ ሲኖሩ አንድም ቀን የባይተዋርነት ስሜት ተሰምቷቸው አያውቁም፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ምን አልባትም ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ እስራኤል የሄዱትም ልቦናቸውም መንፈሳቸውም ኢትዮጵያ ላይ መሆኑን በተለያየ መልኩ የምንገነዘበው እውነታ ነው፡፡ በቴላቪብ አደባባይ በሌጣ ከበሮ እና በሌሎች ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎቻችን ጭፈራውን ሲያስነኩት ስንመለከት በእርግጥም ከኢትዮጵያ ወጡ እንጅ ኢትዮጵያዊነት ምንግዜም ከውስጣቸው ታትሞ እንደሚኖር ያረጋግጥልናል፡፡

በባርነት የሄዱ አፍሪካውያን መሆናቸው የሚነገርላቸውና እ.ኤ.አ በ1930ዎቹ ከጃማይካ ተነስቶ አለምን ባዳረሰው የራስታፋራይ እምነትና አኗኗር በስፋት የሚታወቁት ባለ ድሬድሎኮች /ጉንጉን ጽጉር አሠራር/ሁሉም ራስታዎች ባለ ጉንጉን ፀጉሮች፣ ሁሉም ባለ ጉንጉን ፀጉሮች ራስታዎች ናቸው ማለት ግን አይደለም/ ጃማይካዎችም ከዓለም አገራት መርጠው ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚሉት አገራችን ለሁሉ የምትበቃ ሁሉንም የምትስብ እንጅ የማትገፋ መሆኗን በተጨባጭም ስለሚያውቁ ነው፡፡

ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ንግስናን 10 ዓመታት በፊት በጃማይካዊው የመብት ተሟጋች ማርከስ ጋርቬይ ተከታዮቹን ‹‹ወደ አፍሪካ ተመልከቱ፤ ጥቁር ንጉስ ይነግሳል፤ የመሰጠት ዓመትም ይመጣል›› በማለት በነገራቸው ትንቢታዊ ቃል መሰረት ንጉሰ ነገስት ሀይለስላሴን እንደ ፈጣሪ የሚቆጥሯቸው ጃማይካዎች ለኢትዮጵያ ያላቸው ፍቅር በቃላት የሚገለፅ አይደለም፡፡ ጃማይካውያን ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ምድር እንደሆነች ያምናሉ፡፡

በተለይም አፄኃይለ ስላሴ 1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ ጃማይካን መጎብኘታቸውን ተከትሎ በርካታ ጃማይካውያን ደማቅ አቀባበል እንዳደረጉላቸውና እስከ አሁን ድረስም እለቱን እንደ አንድ በዓል እንደሚያከብሩት ይነገራል፡፡

በንጉስ ነገስቱ ውሳኔ ሻሸመኔ ላይ መኖሪያ ቦታ የተሰጣቸው ጃማይካውያን የአገራችንን ታላቅነት የህዝቦቿን እንግዳ አክባሪነት እየሰሙ በመምጣታቸው ቁጥራቸው በየገዜው እያደገ መጥቷል፡፡

የሬጌ ሙዚቃ ንጉሡ በመባል የሚታወቀው ቦብ ማርሌ በሙዚቃው አፍሪካን እና ኢትዮጵያን እንዲሁም ንጉሡን ያወድሳቸው የነበረው አገራችን ለእኛ ብቻም ሳይሆን ለመላው ጥቁር ህዝብ አለኝታ መሆኗን በመገንዘቡ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡

ፓርቲያችንም በሚመራው መንግስት በኩል ቤተ-እሥራኤላውያን፣ ራስ ተፈሪያን እና ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉ ሌሎች የውጭ ሀገር ዜጎች፣ የትውልደ ኢትዮጵያ መታወቂያ እንዲሰጣቸው በማድረግ አገራችን እንደድሮው ሁሉ ዛሬም ለሁሉም የምትበቃ መሆኗን ዳግም ካስመሰከረ ቆይቷል፡፡ የዚህ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ቪዛ አይጠየቁም፣ ለመቆየትም የመኖሪያ ፈቃድም እንደማያስፈልጋቸው በአንድ ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መግለፁ ይታወሳል፡፡ አገራችን ስደተኞችን በመቀበልም ቢሆን በዓለም ደረጃ ቀዳሚ ናት፡፡ በእርስ በርስ ግጭት፣ በረሀብ፣ በጦርነት እና በመሳሰሉት ምክንያቶች መጠጊያ ያጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የውጭ አገር ዜጎችን ተቀብላ እያኖረች ትገኛለች፡፡ አንዳንዶችም የትምህርት እድልም ጭምር እየተፈጠረላቸው ከአገራችን ዜጎች ጋር እየተማሩ የሚገኙ እንዳሉም ይታወቃል፡፡ ስደተኞቹ ኢትዮጵያን ወደውና ፈቅደው በመምጣታቸው ኢትዮጵያውያንም በአቃፊ እሴታቸው ተቀብለው በሰላም እንዲኖሩ እያደረጉ ነው፡፡

አገራችን ሁሉን አቃፊ በተለይም መላውን ጥቁር እና አፍሪካውያንን ሰብሳቢ ሆና እያለ ዜጎች በተለያዩ አካባቢዎች ለረጅም ዘመናት በቆዩበትና በተወለዱበት አካባቢ እንደ መጤ ተቆጥረው ሲፈናቀሉ ማየት ነገሩን እንቆቅልሽ ያደርገዋል፡፡ ፓርቲያችን የብሔር ብሔረሰቦች መብት እንዲከበር ባደረገው ጥረት ልክ ለአገራዊ እሴቶች መዳበር አለመስራቱ አሁን ላይ እየተከሰቱ ላሉ ተግዳሮቶች እንደምክንያት የሚጠቅሱት ብዙዎች ናቸው፡፡ በእርግጥ ፓርቲያችንም ቢሆን ባለፉት ዓመታት ለኢትዮጵያዊነት መስራት በሚገባው ልክ አለመስራቱን በተለያየ አጋጣሚ ሲገልፅ ቆይቷል፡፡

ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያዊነት እሴት መሸርሸራቸውን እየተጠቀሰ የበለጠ እንዲዳከሙ እየተደረገበት ያለውን የወቅቱን ሁኔታ አለመኮነንም ተገቢ አይደለም፡፡ ብልፅግና ፓርቲ በተለይም ከለውጡ በኋላ የፖለቲካ ምህዳሩን በረጋግዶታል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የዴሞክራሲ ምህዳሩ መስፋት የትችት አጀንዳቸውን የሚያጠፋባቸው ሀይሎች ግን የፓርቲውን ቁርጠኛ ውሳኔ የወደዱት አይመስልም፡፡ የተፈጠረውን ምቹ አገራዊ ሁኔታ አገራቸውንና ህዝቦቿን ወደፊት ለማራመድ ሊጠቀሙበት ሲገባ ወደኋላ ለመመለስ የሴራ ፖለቲካን የሚያራምዱት ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡

ከዛም ከዚም እየተከሰቱ የሚገኙ ነባር እሴቶቻችንን የሚበርዙ አመለካከትና ድርጊቶችን በአፋጣኝ እልባት ከመስጠት ላይ ፓርቲው መንግስት የት አሉ የሚሉ ድምፆች ተበራክተዋል፡፡ ሆደ ሰፊነቱ የፖለቲካ ነጋዴዎችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከህዝብ ልብ እንዲወጡ በማድረግ በኩል የጎላ አስተዋፅኦ እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም ‹‹ከቅርብ ያልመለሰ እረኛ ሲሮጥ ይውላል›› ነውና ነገሩ የህግ የበላይነትን እያስከበሩ አገራዊ እሴቶቻችንን በማስጠበቅ የዜጎችን ስጋት መቀነስ በየደረጃው ከሚገኙ አመራሮች፣ አባላት እና ከሁሉም ዜጎች ይጠበቃል፡፡

# በፈረንጆቹ 2019 በበርካታ ዘርፎች ዜጎቻችን ዓለም አቀፍ ተሸላሚዎች በመሆን አገራችንንና ህዝቦቻዋን አኩርተዋል፡፡

* *ክቡር ጠ/ሚ/ር ዶ/ር አብይ አህመድ* - የ2019 100ኛው የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ
* *ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ* - በፎርቢስ መፅሔት የ2019 ከአለማችን 100 ተፅዕኖ ፈጣሪ ሴቶች አንዷ ሆነዋል፡፡
* *ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም* (የኢሰመጉ መስራች) - የአደረጉት የሰብዓዊ መብት ተጋድሎ ድንቅ ነው ሲል ዴፌንድ ዲፊንደር የተሰኘ ዓለም አቀፍ የሰበዓዊ መብት ተከራካሪዎች ቡድን ዕውቅና ሰጥቷቸዋል፡፡
* *አቶ ተወልደ ገ/ማርያም* - የአመቱ የአየር መንገዶች ዋና ስራ አስፈፃሚዎች ሽልማት አሸናፊ የኢትዮጵያ አየር መንገድም የአፍሪካ የላቀ አትራፊ ተቋም ተብሎም ተወድሷል፡፡
* *አቶ አህመድ ሺዴ* (የፋይናንስ ሚኒስትር) - በአፍሪካ ፋይናንሺያል መፅሔት የዓመቱ ምርጥ የአፋሪካ ፋይናንስ ሚኒስትር ሽልማትን አሸንፈዋል፡፡
* *አትሌት ሻለቃ ደራርቱ ቱሉ* - በአለም ዓቀፍ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን አወዳዳሪነት በተካሄደው የዓመቱ ምርጥ ሴት ምርጫ በቀደመው የትራክ ሩጫ ስኬትዋ እና በአሁኑ ወቅት በአላት ስፖርቱን የመምራት ብቃት አሸናፊ ሆናለች፡፡
* *የህግ ባለሙያና የህግ ጠበቃ አቶ አመሃ መኮነን* - የ2019 ዓ/ም የፈረንሳይ ጀርመን የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ሽልማት አሸናፊ ሆነዋል፡፡
* *ስራ ፈጣሪዋ ወ/ሮ ፍሬወይኒ መብርሃቱ* - የሲ ኤን ኤን ቴሌቪዥን ጣቢያ የ2019 የስራ ፈጠራ ጀግና እና ሰብዓዊነት የተሞላበት ተግባር እመቤትነት ሽልማት ሸልሟታል፡፡
* *ዶ/ር መሃመድ አባ ኦሊ* - የ2019 በተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ጉዳይ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሚል ሽልማትን ዓለም አቀፍ የደረጃዎችና ምዘና ኤጀንሲ ሸልሟቸዋል፡፡
* *ማርታ ገበየሁ* - የ2019 አለም ዓቀፍ የውሃ ሽልማት ተሸላሚ ሆነዋል፡፡
* *ዶ/ር ሃረገወይን አሰፋ* - በአሜሪካ ኬሚስትሪ ማህበር የ2019 የኬሚስትሪ ጀግና ተበለው ተሸልመዋል፡፡
* *ፕሮፌሰር አታላይ ዓለም* - በሳይካትሪክ ኢፒደሞሎጂ እና ባዮስታትስቲክስ የ2019 የሃርቫርድ ሽልማት አሸናፊ ሆነዋል፡፡
* *ዶ/ር አረጋዊ ግርማይ* - የስሜን ካሮላይና የሃኪሞች አካዳሚ የዓመቱ ምርጥ የቤተሰብ ሃኪም ሽልማት አሸናፊ ሆነዋል፡፡
* *ዶ/ር ዘቢብ የኑስ* - የፊቸር ሊደርስ አፍሪካን ኢንዲፐንደንት ሪሰርቸርነት ሽልማትን ከ30 ተመራማሪዎች ጋር ተወዳድረው የዓመቱ አሸናፊ ሆነዋል፡፡
* *አትሌት ሰለሞን ባረጋ* - በአለም ዓቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማህበር የዓመቱ ምርጥ ወንድ አትሌት
* *አርቲስት አብርሃም በላይነህ* - የ2019 የአፍሪካ ባህላዊ ሙዚቃ ዘርፍ አሸናፊ
* *አርቲስት አቡሽ ዘለቀ* - በስታር ኦፍ ዘጀኔሪሽን ሽልማት አሸናፊ
* *በፍቃዱ ሃይሉ* - የኢንተርናሽናል ራይተርስ ኦፍ ክሬጅ አዋርድ ሽልማት አሸናፊ ሆኗል
* *ሄኖክ ስዩም* - የሆቴል ሾው አፍሪካ ምርጥ የቱሪዝም ጋዜጠኛ ሽልማት አሸናፊ ሆኗል

**የፈረንጆቹን 2019ን ድምቀቶች በማስቀጠል ጉድለቶቻችንን በመደመር እሳቤ በማስተካከል በብልፅግና መንገድ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ፡፡**

## "ሳይዋሀድና ሳይደመር የጣፈጠ፣ ያማረም ነገር የለም፡፡"

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ

# ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ ለሶስት አስርት ዓመታት የዘለቀው የግንባርነት ጉዞው በዓለም ላይ ስልጣን ይዘው ረጅም አመታትን ካስቆጠሩ ጥቂት የፖለቲካ ድርጅቶች ተርታ አሰልፎታል፡፡

ድርጅቱን ያዋቀሩት አራቱ ፓርቲዎች በሐዋሳው 11ኛው ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ አጋር ፓርቲዎችን ጨምሮ መዋሀድ በተለያዩ አካባቢዎች እየተፈጠሩ ላሉ የሰላም መደፍረስና ቀውሶች መፍትሄ ሊሆን እንደሚችል ብቻ ሳይሆን አገሪቷንና ህዝቧን ወደ ብልጽግና እንደሚያሸጋግርም በማመን ውህደቱ ቢዘገይም ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ አካሄድን ሳይስት ዕውን እንዲሆን ወስነው ወጥተዋል፡፡ ከጉባኤው ማግስት ጀምሮም ኢህአዴግ የውህደቱን ዕውን መሆን ጉባኤው በአስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በማካሄድ ጥናቱንምለምክር ቤቱ በማቅረብ ሰፋ ያለ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ውህደቱን እውን ለማድረግ ሲሰራ መቆየቱ እሙን ነው፡፡

በ2000 ዓመተ ምህረት የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ “ውህደት” (union) ማለት “ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ በህግ መሠረት ተመዝግበው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ላይ ተዋህደው ውህድ የፖለቲካ ፓርቲ ይመሰርታሉ” በማለት ይገልፀዋል፡፡ በ2011 በጸደቀው የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንደተደነገገው “ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተዋህደው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት ይችላሉ” ይላል፡፡ በዚህም እሳቤ ስለ ኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ውህደት ስናነሳ ድርጅቶቹ እራሳቸውን ሙሉ በሙሉ አፍርሰው፣ አርማዎቻቸውንና ማህተሞቻቸውን ለምርጫ ቦርድ አስረክበው አባሎቻቸውን በቀጥታ የአዲሱ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲ አባል ያደርጋሉ ማለት ነው፡፡ ይሄም ሆኗል፡፡ የግንባሩ ድርጅቶች የነበሩ አዴፓ፣ኦዲፒና ደኢህዴን እንዲሁም አምስቱ አጋር ድርጅቶች ራሳቸውን በማፍረስ ተዋህደው ብልጽግና ፓርቲን እውን ማድረግ ችለዋል፡፡ በእዚህም ኢትዮጵያዊነት እና ብሄራዊ ማንነት በእኩል ደረጃ ከፍ ያለ ቦታ በሕግ ጭምር የተሰጣቸው በመሆኑ በህዝቦች ዘንድ ተስፋን አሰንቋል፡፡

ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ ከሐረሪ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አፋርና ሶማሌ ክልል ከተውጣጡ የማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት አንድ ጠንካራ አገራዊ ፓርቲ መመሥረት ለሁለንተናዊ ብልጽግና አስፈላጊና የማይተካ ሚና እንደሚወጣ ገልጸውላቸው ነበር፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል የሚነጋገርበት፣ የሚወስንበት፣ ድምፁ የሚሰማበት ሥርዓት ለመፍጠር ውህደቱ ወሳኝ መሆኑንም አስምረውበታል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ ሐሳቡ ‘የምር ነው ወይስ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የአፍ ወለምታ?’ ሲሉ በርካቶች መነጋጋሪያ አድርገውት ቆይተዋል፡፡ የብልጽግና ጽህፈት ቤት ምክትል ሀላፊ አቶ መለስ ዓለሙም ኢህአዴግ ወደ አንድ አገራዊ ፓርቲ እመጣለሁ ብሎ በርካታ ስራዎችን ሲሰራ መቆየቱንና በመጨረሻም እውን ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ፓርቲዎቹ ተመሳሳይ ፕሮግራም ስላላቸው፣ በልማት፣ በዲሞክራሲና ሰላምን በማስፈን በጋራ ሲሠሩ በመቆየታቸው ወደ አንድ አገራዊ ፓርቲ ለመሸጋገር ያገዳቸው ነገር እንዳልነበረ የሚጠቅሱት አቶ መለስ ድርጅቱ አጋሮችንም አካትቶ የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ‹‹የእንዋሃድ›› ጥያቄን ሲያጤነው እንደቆየና ጊዜው ሲደርስም እውን ማድረግ መቻሉን ያስረዳሉ፡፡

“ኢህአዴግ ውስጥ የተለመደ አሠራርና ልምድ በመኖሩ ድርጅቱም የትግል ፓርቲ በመሆኑ

የመሠረቱት ፓርቲዎች የተለያዩ ክርክሮችና ሐሳቦችን ቢያቀርቡም ኢህአዴግ ክርክሮችና ሐሳቦችን እንደ ልዩነት ሳይሆን እንደ ባህል ወስዶ በመስራት ውህደቱን በስኬት በማጠናቀቅ የብልጽግና ፓርቲን እውን ማድረጉን የብልጽግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ምክትል ሃላፊ አቶ መለሰ ዓለሙ ያስረዳሉ፡፡

ይሁን እንጂ አገሪቱ በለውጥ ጎዳና ላይ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በተለይም ኢትዮጵያዊነት በድርጅቱ ሊቀመንበር ጎልቶ በሚቀነቀንበት ወቅት ከውሕደት ሐሳብ ጀምሮ እስከ ብልጽግና ፓርቲ እውቅና ማግኘት ለአንዳንዶች በብሔር አደረጃጀትና በፌዴራሊዝም ላይ ለውጥ የሚያመጣ ነው ብለው ሲያደናግሩ ይስተዋላል፡፡

"ውህደቱ ሁሉም ፓርቲዎች የጋራ አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት እንጂ በፌደራል ሥርዓቱ ሆነ በማንነት ላይ የሚፈጥረው ለውጥ እንደሌለና ግምባሩን ወደ ብልጽግና ፓርቲ ማምጣትም አሃዳዊ ሥርዓትን መከተል አይደለም" ሲሉ አቶ መለሰ ያስገነዝባሉ፡፡

ኢህአዴግ በጉባዔው ውህደቱን እውን ለማድረግ በጥናት ላይ የተመሰረተ ስራ እንዲሰራ ወስኖ መውጣቱ ይታወቃል፡፡ በወቅቱም የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶክተር ዐብይ አህመድም የኢህአዴግን ውህደት አይቀሬነት ደጋግመው ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ በተቃራኒው ኢህአዴግን ከመሰረቱት ድርጅቶች መካከል ህወሓት ውህደት ለማድረግ የሚያስችል ቁመና ላይ እንዳልሆኑና እንደማይዋሃዱ አቋማቸውን ይፋ ማድረጋቸውን ተከትሎ በውህደቱ ላይ አሉታዊ ጫና ሊያሳርፍ ይችላል የሚል ሥጋት ፈጥሮ ቢቆይም ውህደቱን እውን ከማድረግ ያገደው ነገር እንደሌለ ከኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚና ከምክር ቤቱ አቋም መገንዘብ ይቻላል፡፡

የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ከመጋቢት 30 እስከ ሚያዝያ 03 ቀን 2011 ዓ.ም ያካሄደውን መደበኛ ስብሰባ ሲያጠቃልል ባወጣው መግለጫ እንዲህ ብሏል፡፡ «…ኢህአዴግ ጀምሮት የነበረውና ተኮላሽቶ የቀረው በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲመለስ ከማድረግ ይልቅ፣ በቅርብ ጊዜያት አማራጭ የመፍትሔ አቅጣጫ ተብሎ እየቀረበ ያለው ጉዳይ፣ ኢህአዴግን በማዋሀድ አንድ ሀገራዊ ፓርቲ ለማድረግ የሚል ሩጫ ትክክለኛና መርህ አልባ ነውም ብሎታል ህወሐት፡፡ የፓርቲ ውህደት ጥያቄ በተለያዩ ጊዜያት ሲነሳ የነበረና በጥናት እንዲመለስ አቅጣጫ ተቀምጦ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ ይህ አቅጣጫ የተቀመጠው ደግሞ ኢህአዴግ ጤናማ በነበረበት ወቅት፣ በመሠረታዊ የድርጅቱ እምነቶችና መስመር ላይ ፅኑ እምነት በነበረበት እና ምንም መሸራረፎች ባልነበረበት ወቅት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የደፈረሰና ጉራማይሌ አመለካከትና እምነት የያዘ ኢህአዴግ፣ አይደለም ለውህደት ከዚህ ከቀደም ለነበረው አደረጃጀቱም የሚሆን የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት የሌለው ኢህአዴግ ነው ያለው፡፡ በሁሉም መሠረታዊ ጥያቄዎች የፕሮግራም፣ ስትራቴጂ፣ መለያ እምነቶች በእህት ድርጅቶች መካከል አንድ የሚያደርግ አመለካከትና እምነት በሌለበት፣ ሁሉም ወደተለያየ አቅጣጫዎች በሚሳጋበት ውህድ አንድ ፓርቲ ሊታሰብ የሚችል አይደለም» በማለት ህውሃት አቋሙን ግልጽ ማድረጉ ያታወሳል፡፡

የህወሓት ስራ አስፈጻሚ አባል አቶ ጌታቸው ረዳም ወደ ውህደት ከመሄዱ በፊት ብዙ የቤት ሥራዎች መሠራት ይኖርባቸዋል በማለት የህወሃትን አቋም በተለያዩ ሚዲያዎች ሲገልጹ ቆይተዋል፡፡ በዋና ዋና የፓርቲው ምሰሶ በሆኑት፤የህገ-መንግሥትና የልማት ሁኔታዎች ላይ ተመሳሳይ ካልሆነም እጅግ ተቀራራቢ አረዳድ መኖር እንደአለበት ጠቁመው፤ እነዚህ ጉዳዮች ሳይሟሉ ኢህአዴግን አፍርሶ ሌላ ህጋዊ ያልሆነ አዲስ ፓርቲ መመስረት ህገወጥነት ነው ሲሉ መደመጣቸው የሁላችንም የቅርብ ትዝታ ነው፡፡ በቅርቡም ህወሃት ባካሄደው አስቸኳይ ጉባኤ ውህደቱ ህገወጥና ተቀባይነት እንደሌለው አቋሙን ገልጾ ከብልጽግና ፓርቲ ጋር እንደማይዋሀድም

አሳውቋል፡፡

የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የአጋር ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ የነበሩት አቶ ፍቃዱ ተሰማ በሃላፊነት በነበሩበት ወቅት ለዚህ የህወሃት የተሳሳተ አስተሳሰብና እንቅስቃሴ ቀጣዩን ምላሽ ሰጥተው ነበር፡፡ ውህደቱ ቀደም በአሉት አመታት ጥያቄ ሲቀርብበት እንደቆየና ሁሉም የኢህአዴግ ድርጅቶች አምነውበት በርካታ ስራ ሲሰራ መቆየቱን በወቅቱ አውስተዋል፡፡ ውህደቱ ለህዝቡና ለሀገሪቷ የሚበጅ መሆኑም ታምኖበት በስምምነት ወደ ስራ መገባቱን ገልጸው ነበር፡፡

እስካሁንም የመጣነው የትኛውም ድርጅት ቢሆን ሙሉ በሙሉ በስምምነት እንደነበረና ከአጋሮች ጋርም በዛው አግባብ እንደተሄደበት ያወሱት ሀላፊው በወቅቱ አንድም ድርጅት ተቃውሞ እንዳላቀረበና ሊፋጠን እንደሚገባ ነበር አቋም የተያዘው ብለውናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ማንኛውም ድርጅት በውህደቱ አግባብ ላይ ነጻ ፍላጎቱ የሚጠየቅ እንደመሆኑ፤ መዋሃድም ሆነ አለመዋሃድ መብቱ ተጠብቆለት ህወሃት ውህደቱን ባትቀበልም ከልብ የተቀበሉ ድርጅቶችና አጋር ፓርቲዎች ግን ለሃገሪቷና ለህዝቡ ብልጽግና ሲሉ እውን ማድረግ መቻሉን ይናገራሉ፡፡

በኢህአዴግ ሕገ-ደንብ መሠረት "ማንኛውም የድርጅቱ እህት ፓርቲ በማንኛውም ጊዜ ከግንባሩ ሊወጣ የሚችልበት ዕድል እንዳለው አስፍሯል፡፡ ወይንም በሌሎች አባል ፓርቲዎች ከግንባሩ እንዲወጣ ሊወሰንበት ይችላል" ይላል፡፡ ህወሓትም ከውህድ ከ(ብልጽግና) ፓርቲው ጋር አልዋሀድም ብሎ ካለ እንደ አንድ ፓርቲ የሚከለክለው አይኖርም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወደዚህም በተግባር ህወሃት ከውህደቱ ራሱን ማግለሉን ለኢህአዴግ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት በደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም የተቀሩት ሶስቱ የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች ማለትም አዴፓ፣ ኦዴፓ እና ደኢህዴን አጋር ፓርቲዎችን በማካተት ውህደቱን እውን ማድረግ ችለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድም ለህብረ ብሄራዊው የብልጽግና ፓርቲም እውቅና ሰጥቶታል፡፡ ፓርቲውም ለአባላቱ በፓርቲው ፕሮግራምና ህገደንብ ዙሪያ ስልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡ በዚህም አባል ፓርቲዎቹ ከግልና ከፓርቲ ጥቅሞቻቸውና ፍላጎቶቻቸው በበለጠ የአገርን ጥቅም በማስቀደም በሰለጠነ መንገድ አገሪቷን ከቀውስ ይታደጓታል የሚል ተስፋን በብዙዎች ዘንድ አሰንቋል፡፡

እንደሚታወቀው ከመጠን በላይ የከረረው የብሄር ፌደራሊዝም ኢትዮጵያዊያን እንደልባቸው ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው እንዳይሰሩ አድርጓቸዋል፡፡ በጋብቻ ትስስር፣ በስራ፣ በመንደር ሰፈራ ወይም በፍልሰት ምክንያት ፌደራሊዝሙ ካሰመረላቸው ክልሎች ውጭ የተገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችም ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቻቸው ለመጨፍለቁም ምክንያት ሆኗል፡ ፡ በብሄር ተኮር ድርጅቶች የሚመሩት ክልሎች በአንድ ውህድ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲ ቢመሩ ኖሮ ግን ችግሩ ሙሉ በሙሉ ባይቀረፍም እንኳ መሻሻል ያሳይ እንደነበር አስተያየት የሰጡን ምሁራንና አባላት ይገልጻሉ፡፡ አሁንም በኢህአዴግ በኩል የተደረገው የውህደት ፓርቲ ችግሩን እንደሚቀርፍ አምነውበታል፡፡

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የሚነሱ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ለመመለስና ለማስቀጠል ዕውነተኛ የፌዴራል ሥርዓት መገንባት አማራጭ የሌለው መፍትሄ እንደሆነና የኢህአዴግ ውህደት ዋነኛ ዓላማም የፌዴራል ስርዓቱን ማጠናከር እንደሆነ ምሁራኑ ይገልጻሉ፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አንተነህ ሙሉ የፌዴራሊዝም ሥርዓት እንደ አገር የምንከተለው አካሄድ ነው፡፡ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ባለፉት ሩብ ምዕተዓመት ጉልህ ሚና የተጫወተ ፓርቲ ነው፡፡ ነገር ግን በየጊዜው ራሱን እየፈተሸ፣ ጉድለቶቹን እያረመ ትክክለኛ ፌደራሊዝምን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ብዙ እንደሚቀረው በጥናቱ መመለሱን አረጋግጠዋል፡፡ የፌዴራል ሥርዓቱ ኢህአዴግ ስለከሰመ ብልጽግና ፓርቲ ስለፈቀደ ወይም ስለጠላ የሚፈርስና

የሚቀጥል አይሆንም የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አንተነህ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የሚነሱ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ለመመለስ እና ለማስቀጠል የፌዴራል ሥርዓቱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ በጥናቱ የተደመደመ መሆኑንም ያስገነዝባሉ።

የፌዴራል ሥርዓቱን በማጠናከር ሂደት ውስጥ ህብረብሄራዊ አንድነታችንን በመሸርሸር የፅንፈኝነት አዝማሚያዎች በመኖራቸው ብሄራዊ ማንነት ሳይጓደል ይህንን ማስተካከል እንደሚገባ፤በህዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ከማጠናከር አንጻርም ውህዱ ፓርቲ (የብልጽግና ፓርቲ) ተገቢውን ሚና መጫወት እንዳለበትና ጠንካራ ትስስር ሊፈጠር እንደሚገባ ረዳት ፕሮፌሰር አንተነህ በጥናቱ ላይ አመላክተዋል።

ከኢህአዴግ ጋር በአጋርነት የቆዩት አምስቱ ድርጅቶችም ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ክልላቸውን ሲያስተዳድሩ እኩል ተሳታፊ ለመሆን ጥያቄ ቢያነሱም ሰሚ በማጣታቸው በአገራቸው ጉዳይ ላይ በጋራ ለመወሰን እድሉን ሳያገኙ መቆየታቸውንና አሁን ላይ ግን በብልጽግና ፓርቲ ውህድ መሆናቸው ለጥያቄያቸው መፍትሄ ሆኖ መቅረቡንም ረዳት ፕሮፌሰር አንተነህ ያስረዳሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቅድመ ምረቃ መርሐ ግብር አስተባባሪ፣ ተመራማሪና መምህር ዶክተር ታደሰ ጃለታ ኢህአዴግ ውህደት ለመፈፀም ካቀደ ቢቆይም ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ሁለት ዓመት እንደፈጀ ይገልጻሉ። ጥናቱ አሳታፊ መሆኑን የሚያስረዱት ዶክተሩ፤ ይህ የፖለቲካ ድርጅት ጥናት በመሆኑ የየብሄራዊ ድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች፣ መካከለኛ አመራሮችና አባላት የተሳተፉበት እንደሆነና የማህበራዊ ዘርፍ ላይ ያተኮረ ጉዳይ ሊጠና በሚችልበት የጥናት ደረጃ ሳይንሳዊ ደረጃውን ጠብቆ እንደተከናወነም ያስገነዝባሉ።

የፌዴራል ሥርዓትን ከሚከተሉና ብዝሃነት ካለባቸው 28 የአፍሪካና ሌሎች አገራት ልምድ መቀሰሙን የሚያስረዱት ዶክተር ታደሰ፤ ከዚህ ባሻገር ኢህአዴግ በተለያዩ ጊዜያት ባደረጋቸው ውይይቶች የነበሩትን ቃለጉባኤዎች ለጥናቱ ማዳበሪያነት መጠቀማቸውንም ይናገራሉ።

‹‹በኢህአዴግ ውስጥ ሶስት ዋና ዋና ችግሮች እንደነበሩ በጥናቱ ታይቷል›› ያሉት ዶክተር ታደሰ፤ አንደኛው የአመለካከት ችግር ሲሆን፤ ኢህአዴግ ይህንን ችግሩን ለመቅረፍ በየጊዜው ግምገማ ሲያደርግ እንደነበር፣ ነገር ግን ችግሩ አለመቀረፉንና ለዚህም ዋናው ምክንያት የአደረጃጀት ችግር ስለነበረበትና ኢህአዴግ አቃፊ ባለመሆኑ የመጣ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኢህአዴግ የተመሰረተው ከአራት ክልሎች ከተውጣጡ ፓርቲዎች ሆኖ አገር የሚመራ ቢሆንም ሌሎቹ ፓርቲዎች በአገሪቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም አይነት ተሳትፎም ሆነ ሚና እንዳልነበራቸው ያወሱት ዶክተር ታደሰ፤ እነዚህን ችግሮች ሙሉ በሙሉ ለመፍታት አጠቃላይ ችግሮቹን መሰረት ያደረጉ ለውጦችን ማካሄድ አስፈላጊ በመሆኑ ጥናቱ መካሄዱንና በጥናቱም መሰረት ወደ ውህድ ፓርቲ መመጣቱን አስገንዝበዋል። አጋር ድርጅቶች ከእንግዲህ በኂላ ውሳኔ ተቀብለው የሚተገብሩ ሳይሆን ወሳኝ አካል መሆናቸውንም ይገልጻሉ።

ውህደቱ የብሄር ፓርቲዎችን ይጨፈልቃል፣ አሃዳዊ ሥርዓት ይፈጥራል፣ የፌዴራል ሥርዓትን ይቃረናል በሚል በህወሃት የሚነሱ ሃሳቦች የተሳሳቱ መሆናቸውንም ዶክተር ታደሰ ያስገነዝባሉ። በጥናቱም መሰረት የተዋሃደው ብልጽግና ፓርቲ አገሪቷን መምሰል አለበት ይላል። አገሪቷ ምን ትመስላለች ካልን ደግሞ ብዝሃነት ያላት አገር። የባህል፣ የማንነት፣ የቋንቋ ወዘተ ብዝሃነት አለ። ስለዚህ ብዝሃነትን የሚያከብርና የሚያንፀባርቅ ሊሆን እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። የብልጽግና ፓርቲ በብዝሃነት ላይ የተመሰረተ አገራዊ አንድነትን በመገንባት ብዝሃነትን የሚያከብር የፌዴራል አወቃቀር ያለው ነው።

‹‹ውህደቱ ፌዴራል ሥርዓትን ለማጠናከር እንጂ ለማደብዘዝ አይደለም›› ያሉት ዶክተር ታደሰ ‹‹እስካሁን ድረስ በተለያዩ ሥርዓቶች ውስጥ ያልታዩና በፌዴራል ሥርዓት ውስጥ ያሉ በጎ

ነገሮችን ይዞ ስኬቶችን የሚያስቀጥል ጉድለቶችን የሚያርም ይሆናል›› ይላሉ። የተለያዩ ቋንቋዎች በሚነገሩባቸውና የፌዴራል ሥርዓትን በሚከተሉ አገራት ከአንድ በላይ ቋንቋ በብሄራዊ ቋንቋነት እንደሚያገለግል፣ በኢህአዴግ ጥናትም ይህ መመላከቱን ዶክተር ታደሰ ገልጸው ጥናቱም ቢያንስ አራት ቋንቋዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ማሳየቱንና በኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚና ምክር ቤትም ማጽደቁን ያስታውሳሉ። በብልጽግና ፓርቲም መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ አምስት ላይ ሁሉም የሀገራችን ቋንቋዎች ሙሉ እውቅና እንደተሰጣቸው፣ የፓርቲው የስራ ቋንቋ ክልሎች በህገ መንግስታቸው የስራ ቋንቋ ይሆናሉ ብለው ያጸደቋቸው ቋንቋዎች እንደሚሆኑ እና ክልሎችና የአካባቢ ቅርንጫፍ ፓርቲ ጽ/ቤቶች እንደየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ቢያንስ ቢያንስ አንድ የፓርቲውን የስራ ቋንቋ በተጨማሪነት መጠቀም እንዳለባቸው አስቀምጧል።

አጋር ፓርቲዎች ስለ ውህደቱ

ግንባርን በትግል ስልትነት ተጠቅመው ስልጣን ከጨበጡ በኋላ ወደ ፓርቲነት መቀየር ሀገር ለማስተዳደር የተሻለ አማራጭ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከሩብ ምእተ አመታት በኋላ ኢህአዴግም ከግንባር ወደ ፓርቲነት የሚቀየርበትን ስልት ነድፎ አሁን ላይ እውን ማድረጉ ተገቢና ትክክለኛ ውሳኔ ነው። አጋር በሚል ስያሜ ተገድቦ የቆየውም የህዝቦች የስልጣን ባለቤትነትና ውሳኔ ሰጭነት መልስ አግኝቷል። አምስቱም አጋር ድርጅቶች ድጋፋቸውን አሳይተው ወደ አዲሱ የብልጽግና ፓርቲም ተዋህደዋል። ከተዋሀዱ ድርጅቶች መካከል የሶማሌ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ አንዱ ነው።

የፓርቲው ስራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት አቶ ሙስጠፌ መሀመድ “የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን የኢህአዴግ አባል መሆን ግድ ይል ነበር” ይላሉ። የአራቱ ፓርቲዎች አባል ያልሆነ የትኛውም ኢትዮጵያዊ ከዚህ ሀሳብ ውጭ በመሆኑ በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት ዜጋ እንዲኖሩ አድርጓል በማለት ኢህአዴግ ወደ አንድ ውህድ ፓርቲ መጥቶ የብልጽግና ፓርቲን እውን ማድረጉ ትክክለኛና ተገቢ ነው በማለት በብሄራዊ ምርጫ ቦርድም እውቅና ማግኘቱ እንዳስደሰታቸው ይገልጻሉ።

በውህደት ውስጥ ሌላው መልስ ያገኘው ጉዳይ ለምን ብሄርን ብቻ መሰረት ያደረገ አካሄድ ይኖራል የሚለው ነው። የአስተሳሰብ ልዕልና በኢህአዴግ ውስጥ ዋጋ እንዳልነበረው የሚናገሩት አቶ ሙስጠፌ ከዘር ባለፈ ሀሳባዊ አንድነት የሚስተናገድበትና በሀሳብ ልዕልና ውሳኔዎች የሚወሰኑበት እንዳልነበረም ያስታውሳሉ።

አሁን ላይ እውን የሆነው የብልጽግና ፓርቲ ግን ይሄን በተጨባጭ የሚመልስ ተራማጅ ሀሳብ መሆኑንም አቶ ሙስጠፌ ያነሳሉ። ብልጽግና ፓርቲ ሁሉም እኩል የሚስተናገድበት የሀሳብ ልዕልና ከፍ የሚልበት እንደሆነ እምነታቸውን የገለጹት አቶ ሙስጠፌ መሀመድ፤ በጥናት የተደገፈው የውህደት ጉዞ ተገቢ ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር በመገባቱ የጋራ ጥቅምን የሚያረጋግጥ እንደሆነ እምነታቸውን አስቀምጠዋል።

የብልጽግና ፓርቲ መመስረት ብዙሃኑን ያረካ ቢሆንም ለመቃወም የሚሞክሩ አካላትም አልጠፉም ያሉት አቶ ሙስጠፌ፤ ተቃውሞ ያላቸው አካላት እንደመከራከሪያ ከሚያቀርቧቸው ነጥቦች መካከል አንዱ የመጨፍለቅ አላማን ያነገበ ነው ብለው ያነሳሉ። ኢህአዴግ ይተች ከተባለ የአጋር ድርጅቶቹን ህልውናም ሆነ መብት እንደተቋም ሲገድብ የቆየበትን ነው በማለት ውህደቱ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች ውሃ እንደማይቋጥሩ ይገልጻሉ። ሁሉም ክልል በፌደራል ስርዓቱ የራሱ ነፃነት አለው ያሉት አቶ ሙስጠፌ ይህንን ሀሳብ የሚደግፉ ተራማጆች ወደ ላይ እንዲወጡ ያግዛል እንጂ ይጨፈልቃል የሚል እምነት እንደሌላቸው አስገንዝበዋል።

የአፋር ብልጽግና ፓርቲም በበኩሉ ኢህአዴግን ወደ ውህድ ፓርቲ ማምጣት በመቻሉ

የአጋር ፓርቲዎችን የዘመናት ጥያቄ የመለሰና የሀገር ግንባታን የሚቀይርና የዜጎችንም ህይዎት በመለወጥ ወደ ብልጽግና የሚያሸጋግር መሆኑን የፓርቲው ስራ አስፈጻሚ አባል አቶ አወል አርባ ይገልጻሉ፡፡

አቶ አወል በገለጻቸው የኢህአዴግ አራቱ አባል ፓርቲዎች ማህበራዊ መሰረታቸውን ከአርሶ አደሩ ጋር አድርገው በመቆየታቸው እንደ ሀገር የሚወስኑት ውሳኔ አርብቶ አደሩን ታሳቢ ያላደረገ ነበር ይላሉ፡፡ በትናንትና አስተሳሰብ አሁን አገርን መምራት አይቻልም ያሉት አቶ አወል ኃላቀር፣ የተረሱ፣ አጋር የሚሉ የማጽናኛ ስሞችን ሲሰጡ ቢቆዩም ስያሜው እውነታውን እንዳልቀየረና ለውህደቱም መፋጠን ቁልፍ ሚና መጫወታቸውንም አስረድተዋል፡፡

ከአጋርነት ወጥተው የግንባሩ አባል እንዲሆኑም ረጅም ዓመታት ያስቆጠረ ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርቡ መቆየታቸውን አቶ አወል አስታውሰው "ጎሳዊ አደረጃጀት ነው ያላችሁ" የሚል ተስፋ አስቆራጭ ምላሽ ሲሰጡ እንደቆዩና ጥያቄያቸው ውሀ ሳይቋጥር መዝለቁን ያስረዳሉ፡፡ አጋር የሚለው ቃል አንድ ሀገር ላይ የጋራ ድምፅ እንዳይኖር ከማድረጉም ባለፈ ሀገሪቷን አንዱን ባለቤት አንዱን ጎረቤት የሚያደርግ አሰራር መሆኑንም አብራርተዋል፡፡ በዚህም በሀገር ጉዳይ ላይ ሁሉም ተሣታፊ መሆን አለበት ያሉት አቶ አወል አርባ በማንኪያ ከሚሰጥ ፌዴራሊዝም ወደ እውነተኛ ፌዴራሊዝም ለመሸጋገር ውህደቱን ዕውን ማድረግ ለነገ የሚባል ጉዳይ ባለመሆኑ ተረባርበን እውን ማድረግ ችለናል ብለዋል፡፡

የግንባሩ አባላት ብቻቸውን የወሰኑትን ውሳኔና አቅጣጫ ተቀብሎ ስራ መሥራት ከባድ ነበር የሚሉት ደግሞ የሐረሪ ብልጽግና ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ አቶ ኦርዲን በድሪ ናቸው፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ "አጋር የሆንንበት ምክንያት እራሱ ግልፅ አልነበረም፡፡ የሚሰጠን መልስ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነበር፡፡ ፓርቲው ራሱ ተወያይቶ የወሰነውን ውሳኔ መተግበር አይችልም፡፡" የሚሉት አቶ ኦርዲን "ዜጎች የመረጡት ሀይል ወሳኝ ሳይሆን በሌላ አካል ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ መሥራቱ የመራጭ ዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

አሁን ላይ ግን ከአጋርነትና አባልነት ተላቅቀው ሁሉችም ተዋህደው ብልጽግና ፓርቲን ዕውን ማድረጋቸው ሲያጋጥሟቸው የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት አመቺ ሁኔታ እንደተፈጠረ ይገልጻሉ፡፡

ቀደም ሲል የነበረው የኢህአዴግ አደረጃጀት በብሔራዊ ማንነት ላይ ተመስርቶ ስራዎች ሲሰራ ቢቆይም በዚሁ ልክ በኢትዮጵያዊነት፣ ሀገራዊ ማንነትና አንድነት ላይ አመርቂ ስራ ባለመስራቱ አሁን ላይ በየአካባቢው ችግሮች እየተባባሱ እንዲመጡ እንዳደረገም ያስረዳሉ፡፡

ለዚህም በአራት ድርጅቶች ላይ ብቻ በመመስረቱ የአምስቱን ክልሎች ድምጽና ውሳኔ ባለመያዙ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ መፍጠሩን አስረድተው አሁን ላይ ግን ብልጽግና ፓርቲ አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክርና ለሀገር ግንባታ የሚያነሳሳ ነው ብለዋል፡፡

"ኢህአዴግ ከስሞ ብልጽግና ፓርቲ ዕውን መሆኑ በኢትዮጵያዊነትና በብሔራዊ ማንነት ላይ የሚሰሩ ስራዎችን ያጎለብታል፡፡ የመጠራጠርና ያለመተማመን ችግር ይቀርፋል፡፡

በተጨማሪም በሀገሪቱ በየትኛውም ጫፍ ላይ ያለ ኢትዮጵያዊ በሁሉም እርከኖች ላይ ተሳትፎ የመምራት እድል የሚያገኝበትና መገለልን የሚያስቀር አካታች አሰራርን የሚያሰፍን ነው ሲሉ የቀድሞ የአጋር ፓርቲዎች አመራሮች ይገልጻሉ፡፡

የብልጽግና ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ አባልና በጋምቤላ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አቶ ኡመድ ኡጁሉ እንደገለጹት "ለውጡን ተከትሎ ኢህአዴግ ወደ አንድ ውህድ ፓርቲ ለመምጣት ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ ጋህዴን ድጋፉ ሲያደርግ መቆየቱን ይናገራሉ፡፡ አጋር ድርጅቶች የተካተቱበት አንድ ፓርቲ ለመመስረት የተቀየሰው አቅጣጫ ለሁሉም ህዝቦች በሀገራቸው ጉዳይ

ላይ እኩል የመወሰን መብትን የሚያጎናጽፍ በመሆኑም የብልጽግና ፓርቲን አቅጣጫ ተከትለው በመስራት ለስኬታማነቱ እንደሚረባረቡ አስገንዝበዋል፡፡

እስካሁንም የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርን ለመሰየም ከግንባሩ አራት ድርጅቶች በስተቀር አምስቱ አጋር ድርጅቶችን ሳያካትት እንደቆየ አቶ ኡመድ ገልጸው "አዲሱ የብልጽግና ፓርቲ ግን ሁሉንም የሚያሳትፍና አቅምን መሰረት ያደረገ አካታች ፓርቲ እንዲሆን እንሰራለን" ብለዋል።

በዚህም ባለፉት 28 ዓመታት አጋር ድርጅቶች ያልተሳተፉበትን ሀገራዊ ውሳኔ እንዲተገብሩ ሲደረግ መቆየቱን ያነሱት አቶ ኡመድ በሀገሪቱ እየተተገበረ ያለው ፌዴራሊዝም አጋር ድርጅቶች ጭምር የመሰረቱት እንደመሆኑ መጠን ውህደቱ በፌዴራል ስርዓቱና በህገ-መንግስቱ የተቀመጡ መብቶችን ይበልጥ የሚያጠናክር እንጂ የሚሸራርፍ እንዳልሆነም አብራርተዋል።

የብልጽግና ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ አባልና በቤንሻንጉል ጉምዝ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አቶ አድጎ አምሳያ በበኩላቸው የኢህአዴግ አባል እና አጋር ድርጅቶች ተዋህደው የፈጠሩት የብልጽግና ፓርቲ ለሁሉም እኩል የመወሰን እድልን የሰጠ በመሆኑ ከመሰባሰብ የሚገኝ አንድነትና ጥንካሬን ማጎናጸፍ ያስቻለ ነው ብለዋል፡፡

"የኢህአዴግ እህትና አጋር ድርጅቶች ያደረጉት ውህደት ለሀገርና ለዜጎች ጥቅም እንደሚያስገኝ እምነታቸው እንደሆነና ለህብረ ብሔራዊ አንድነት መጎልበትና የመደመር እሳቤን በአግባቡ ለመተግበር የሚያግዝ እንዲሁም የዜጎችና የሀገርን ሁለንተናዊ ብልጽግና አጠናክሮ ለማስቀጠል ፋይዳው የጎላ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡፡

ያለፉትን ጠንካራ ጎኖችን በማስቀጠል ስህተቶችንም በማረም ወደሚቀጥው የትግል ምዕራፍ ለመሸጋገር የብልጽግና ፓርቲን ዕውን መሆኑ መሳካቱም እንዳስደሰታቸው  አብራርተዋል፡፡

ታዳጊ ክልል እየተባለ በከፍተኛ መጠን የአርብቶ አደሩን አካባቢ ጎድቶታል። አንድ ሰው ብሔራዊ ድርጅት ባለመሆኑ የፈለገ አዋቂ የተማረ እና የተመራመረ ቢሆን ለመምራት አይታጭም ነበር። "ታዳጊ ክልሎች" በሚል ተፈርጆ እንደ አራቱ የኢህአዴግ ብሔራዊ ድርጅቶች አቅም ያለው ሰው ቢኖር እንኳ አይሾምም ነበር። አሁን በመደመር እሳቤ አጋር ድርጅቶችም የብልጽግና ፓርቲው አካል በመሆናቸው ጥቅማቸው ይከበራል፣ በጉባኤዎች ሲሳተፉ እንደሌሎቹ ክልሎች መናገርና ድምፅ መስጠት ይችላሉ። ስለዚህ ለብልጽግና ፓርቲ ስኬት ተግተን እንሰራለን ብለዋል አቶ አድጎ አምሳያ፡፡

አባላት ስለ ውህደቱ

በጉለሌና አራዳ ክፍለ ከተማ በምሁራን አደረጃጀት ውስጥ ታቅፈው የሚገኙ የብልጽግና አባላትም ስለ ፓርቲው ውህደት ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ሰራተኛ የሆኑት አቶ በሰላም ነጋ ብልጽግና ፓርቲ አገራዊ ፋይዳ ያለውና የአስተሳሰብ አንድነት የሚያመጣ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ የአንድነት መንፈስ ተላብሶ ሀገር ለመምራት ውህደቱ አገርንም ያድናል የዜጎችንም ጥያቄ ይመልሳል ብለውም ያምናሉ፡፡ ኢህአዴግ ራሱን አክስሞ በአዲስ የብልጽግና ፓርቲ ከአጋር ፓርቲዎች ጋር ውህደት መፈጸሙ ትክክለኛና አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክር ነው ብለዋል፡፡

ውህደቱ ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ በመመራቱና በመጠናቀቁም አጋሮችን ከምንግዜውም በላይ አስደስቷቸዋል ያሉት አስተያየት ሰጭው ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ከኢህአዴግ ውህደት በመማር ተሰባስበው አማራጭ ፓርቲ ሆነው እንዲቀርቡ የሚያነሳሳ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

"ካሳለፍናቸው አመታት ተነስተን በአጠቃላይ በሀገራችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት በአራቱም ብሔራዊ ድርጅቶች የታየው ክፍፍል አገሪቱን አላስፈላጊ ችግር ላይ ጥሏታል" የሚል እምነት ያላቸው ደግሞ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ፈጻሚ የሆኑት አቶ ቢልልኝ ተማም

ናቸው። ከኢህአዴግ ግንባርነት ይልቅ ውህደት ይሻላል ብለው ወደ ውህደት የመጡት ድርጅቶች ታላቅነታቸውንና አስተዋይነታቸውን አመላካች ነው ብለዋል።

ድርጅቶቹ ከፓርቲ ጥቅም ይልቅ ሀገራዊ ጥቅምን በማሰብ ወደፊት የሚያራምደንንና አብረን ተያይዘን የምናድግበትን ሂደትን በመከተል ውህድ የብልጽግና ፓርቲውን እውን ማድረጋቸው በየአካባቢው ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ ነውም ይላሉ። ኢህአዴግ ራሱን አውራ ፓርቲ ከሚለው አስተሳሰብ ወጥቶ አካታች ስርዓትን ለመዘርጋት ውህደት ማካሄዱ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው አቶ ቢልልኝ ያስረዳሉ።

በአራዳ ክፍለ ከተማ የፓርቲው አመራር የሆኑት አቶ ከድር የሱፍ በበኩላቸው" በአሁኑ ሰዓት ሃገሪቷን በአንድ አይነት መንገድ ለመምራት ወይም የተወሰነ ብሔርን ብቻ ያካተተ ኢትዮጵያዊነት የትም አያደርስም" ይላሉ። ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝቦች ያማከለ ለሁሉም ህብረተሰብ ተቆርቋሪ የሆነና አካታች የብልጽግና ፓርቲ መመስረቱ የግንባሩን ቁርጠኝነት ያሳየ ነው ብለዋል።

ኢህአዴግ እንደሚታወቀው በአራት ብሔራዊ ድርጅቶች የተመሰረተ ግንባር ሲሆን ሌሎች አምስት አጋር ድጅቶችንም ያቀፈ መሆኑን አቶ ከድር ጠቅሰው ድርጅቱ በነበረበት ቁመናና ቅርፅ ቢቀጥል ኖሮ በየጊዜው በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የህዝብ ቁጣ እየተቀሰቀሰ አላስፈላጊ ችግር ውስጥ እንገባ ነበር ብለዋል። ስለሆነም ሃገር አቀፍና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ ህብረ ብሔራዊ የብልጽግና ፓርቲ መመስረቱ ሁለንተናዊ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አመላክተዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት ፈጻሚ አቶ ታምራት ጊቻሞ ኢህአዴግ ቀደም ባሉት ዓመታት ከግንባር ይልቅ ፓርቲ ሆኖ ብሄራዊ ማንነትንና አገራዊ አንድነትን አመጣጥኖ እየሰራ ቢመጣ ኖሮ አሁን ላይ በየአካባቢው የሚስተዋለው የብሄርተኝነት ጽንፍና የሰላም መደፍረስ ባልተከሰተ ነበር ይላሉ። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አጋር ፓርቲዎችን ወደ ውህደት ለማምጣት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እያሳተፋቸው መምጣቱና ውህደቱን በማጠናቀቅ ብልጽግና ፓርቲን እውን ማድረጉ የህዝቡን ጥያቄ በተደራጀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ቁርጠኛ መሆኑን ያሳየበት ነውም ብለዋል። ውህደቱ ጠቃሚ ቢሆንም ውህደቱን ለማጠልሸት የሚሮጡ እንዳሉም አቶ ታምራት ጠቅሰው ሁሉም የድርጅቱ አባላት ችግሮችን በመነጋገር እየፈቱ የታሪክ ተወቃሽ ላለመሆን የብልጽግናን ፓርቲ ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

ሌላውና የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ነዋሪው አቶ ጌታቸር አንተነህም የኢህአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ተዋህደው ወደ ብልጽግና ፓርቲ መሸጋገራቸው በህዝቦች መካካል ያለውን ግንኙነት የበለጠ እንደሚያጠናክር ያብራራሉ። የብልጽግና ፓርቲም የዜጎችን የዘመናት ጥያቄን በተደራጀ መልኩ ለመፍታት የሚያስችል እንደሆነ አመላክተዋል።

በውህደቱ ዋዜማና ማግስት የኢህአዴግን ውህደት ለማፋጠን መሯሯጥ የግለሰቦችን ስልጣን ለማርካት ነው የሚሉ አካላት እንዳሉ የጠቆሙት አቶ ጌታቸር እውነታው ግን የግለሰቦችን የስልጣን ፍላጎት የሚገድብና የሀገርንና የዜጎችን ብልጽግና የሚያጎናጽፍ እንደሆነ ያብራራሉ። ግንባርነት ችግር የፈጠረውም፣ የዘረፈውም፣ ያጭበረበረውም በየብሄራዊ ድርጅቱ እንዲደበቅና ተጠያቂ እንዳይሆን ሲያደርገው መቆየቱን ይገልጻሉ። በዚህም ኢህአዴግን አክስሞ ወደ ብልጽግና ፓርቲ መሸጋገር መቻላችን ለእንደዚህ አይነት ችግሮች መፍትሄ መሆኑን ይናገራሉ።

መሪዎች አንድ ከሆኑ ህዝቡ አንድ የማይሆንበት ምክንያት የለም። በዚች ደሀ አገር ውስጥ አራት አምስት ግንባር እና 100 ፓርቲ ሆኖ መቀጠል የለብንም። ሀያላን አገሮች ውስጥ

እንኳ ሁለት ሶስት ፓርቲ ነው ያለው፡፡ በዚያው ልክ 100 የሀሳብ ልዩነት፣ ርእዮተ ዓለም እና ፕሮግራም ልዩነትም የለም፡፡ ጊዜው አንድ የምንሆንበት ነው፡፡ ጊዜው የባላንጣነት ሳይሆን በውይይት የመቀራራብ ስለሆነ የፖለቲካ ሃይሎች በዚህ ደረጃ ለመወያየት እና ለመግባባት መስራት አለባቸው ብለዋል፡፡

የውህደት ጉዞው ብልፅግና ፓርቲን እውን በማድረግ ስኬታማነቱን አረጋግጧል፡፡ ህብረ ብሄራዊው ውህድ ፓርቲው ብልፅግና በሰፋ ማህበራዊ መሰረት ላይ ሆኖ ለለውጡ ስኬት ይተጋል፡፡ ብልጽግና ብሄራዊ ማንነትንና ኢትዮጵያዊ አንድነትን በአግባቡ በማስተናገድ ጠንካራ የመሪነት ሚናውን የሚወጣ ሲሆን የተነሳበትን ዓላማም ማሳካት የሚያስችል የፓርቲውን የ10 ዓመት ዕቅዱን አዘጋጅቶ ይፋ በማድረግ ለተግባራዊነቱ አባላቱና ደጋፊዎች እንዲረባረቡ ጥሪ አቅርቧል፡፡

የብልፅግና ፓርቲን ለማጠናከር ለውጡንም በብቃት ለመምራት የፓርቲው ስራ አስፈፃሚ የቀጣይ የርብርብ አቅጣጫዎችንም አስቀምጧል፡፡

የፓርቲውን አቅም ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ከማጎልበት አንስቶ የተጀመሩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎችን በለውጡ መንፈስ በመምራት በሙሉ አቅም በቁርጠኝነት መረባረብ እንደሚያስፈልግም አስምሮበታል፡፡

እንደ አዲስ አበባም እየተከናወኑ ያሉ የለውጥ ስራዎች ወደኋላ እንዳይመለሱም ትኩረት ሰጥቶ አመራሩንና ፐብሊክ ሰርቪሱን አነቃቅቶ ወደ ስራ ማስገባት ተጀምሯል፡፡

ህዝቡም በየደረጃው ለውጡን በባለቤትነት የሚመራበትን ሁኔታ በመፍጠር ከዚህ ቀደም ይዞት የመጣውን ኢትዮጵያዊ አንድነትን ከብሄራዊ ማንነት ጋር አዋድዶ በማጎልበት የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተለይ ብልፅግና ፓርቲ በመጪው ሃገራዊ ምርጫ ላይ ብቁ ተወዳዳሪና አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ የምርጫ ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በብቃት መምራት እንደሚያስፈልግና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና አባላት እንዲሁም ደጋፊዎች የሚጠበቅባቸውን ድርጅታዊ ኃላፊነትና ግዴታ በአግባቡ መወጣት አለባቸው፡፡

ፓርቲው ሃገሪቱንና ህዝቡን ወደላቀ ብልፅግና ለማሸጋገርም ከወዲሁ የድርጅትና የመንግስት ስራዎችን ከተደረሰበት የትግል ምዕራፍ ጋር በማጣጣም ወደ ስራ የገባ ሲሆን ስራ አስፈፃሚው ባስቀመጠው አቅጣጫም የፓርቲው አባላት እና ደጋፊዎች ወደ ስራ ገብተዋል፡፡

**"መደመርን በየእለቱ እናቶች ከሚሰሩት፣ ከእናቶች ውሎ፣ ከእናቶች ቀን ሀሳብ በመውሰድ ለኢትዮጵያ የሚያዋጣው የእናቶች መንገድ ነው የሚል ሀሳብ ነው ብልፅግና የአለው፡፡"**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ